አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤

በ
ምንውየለት ደነቀው

ሰኔ /2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

ለ ተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ምንውየለት ደነቀው

ሰኔ /2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤

በ

ምንውየለት ደነቀው

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም	ፊርማ
ፅጌ ሄኖክ (ዶ/ር)	
የውስጥ ፈታኝ ስም	ፊርማ
ገዛኸኝ አመጋር (ዶ/ር)	
የውጭ ፈታኝ ስም	ፊርማ
ሀርመላ ገላኸኝ (ዶ/ር)	

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ. ጥ. ተ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድርስ የአሰራር አቅጣጫን በማመልከት፣ የጥናቱን ረቂቅ በማረም ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠትና በማበረታታት ጥናቱ የአሁኑን ቅርፅ እንዲይዝ ለረዱኝ ለአማካሪዬ ለአቶ ጌታቸው እንዳላማው (ረ/ፕሮፌሰር) ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በትምህርት ቆይታዬ ዘወትር ደጋፋችሁ ላልተለየኝና ከጎኔ ሁናችሁ ላበረታታችሁኝ እንዲሁም የሞራል ብርታት ለሆናችሁኝ ቤተሰቦቼ ምስጋናዬ ከልብ ነው። ጥናቱን በማካሄድበት ጊዜ አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠትና በማበረታታት ከጎኔ ያልተለያችሁት ጓደኞቼ የምስራች አያሌው፣ ኃይሉ መላክ፣ ነብዩ ጋሹ እና ፍፁም ኩራባቸው አመሰግናችኋለው።

በመጨረሻም መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት ጊዜ በጥሩ መስተንግዶ በመቀበልና አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የመፅሀፎቹ አዘጋጆች ለአቶ ትንሳኤ ብርሀኔ እና ለአቶ አለማየሁ ፀጋዬ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና i

ማውጫ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ v

አጠቃሎ iv

ምዕራፍ አንድ 1

መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 4

1.3 የጥናቱ ዓላማ 4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 5

1.5 የጥናቱ ወሰን 5

ምዕራፍ ሁለት 7

ክለሳ ድርሳናት 7

2.1 የቃላት ትምህርት ምንነት 7

2.2 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት 8

2.3 የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ 11

2.3.1 የቃላት የድግግሞሽ መጠን (frequency) 12

2.3.2. ለትምህርት ምቹነት (Learnability) 14

2.3.3 የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ 15

2.3.4 የቃላት የፍቺ ሽፋን 15

2.4 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት 16

2.4.1 ቃላት በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት 17

2.4.2 ቃላትን በፍቺ ማደራጀት 18

2.4.3 ቃላትን በቅርፅ ማደራጀት 18

2.5 የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች 19

2.5.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ 20

2.5.2 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ 22
2.5.2.1 ቃላትን በተመሳስሎና በተቃርኖ ፍቺያቸው ማቅረብ 23
2.5.2.2 የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት 24
2.5.2.3 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት 25
2.5.3 የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ 27
2.5.4 ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ 28
2.5.5 ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅርብ 31
2.5.6 የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ 32
2.5.7 የቃላት ትምህርቱን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ 34
2.6 የመልመጃ አቀራረብ 34
2.7 የቀደሙ ጥናቶች ቅኝት 36
ምዕራፍ ሶስት 40
የጥናቱ ዘዴ እና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 40
3.1 የጥናቱ ዘዴ 40
3.2 የመረጃ ምንጮች 40
3.3 የናሙናዎች አመራረጥ 40
3.3.1 የመፅሀፎቹ አመራረጥ 40
3.3.2 የመማሪያ መፃህፎቹ አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ 41
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች 41
3.4.1 የይዘት ትንተና (Content analysis) 41
3.4.2 ቃለመጠይቅ 42
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴዎች 43
ምዕራፍ አራት 44
የመረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 44
4.1 የተተኳሪ መፃህፍቱ አጭር ቅኝት 44
4.2 የመማሪያ መፃህፎቹ አዘጋጆች ዳራ 45
4.3 የቃላት ትምህርቶችን ይዘት አመራረጥ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና 46
4.4 የቃላት ትምህርቶችን አደረጃጀት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና 51

4.5 የቃላት ትምህርቱን አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና 57
4.5.1 የቃላት ትምህርቶቹን አውዳዊ አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.....57
4.5.2 የቃላትን የፍቺ ዝምድና አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.....64
4.5.3 የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.....68
4.5.3.1 የ7ኛ ክፍል መጽሀፍ የቃላት እርባታና ምስረታ ስርዓት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና 69
4.5.3.2 የ8ኛን ክፍል መፅሀፍ የቃላት እርባታና ምስረታ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.....73
4.5.4 የፊሊጦች፣ የጥምር ቃላትና የአያያዥ ቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና....75
4.5.5 ቃላት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.....79
4.5.6 የቃላት ትምህርቱን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.....84
4.5.7 የመልመጃ መመሪያዎችና ምሳሌዎችን ግልፅነት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.....85
ምዕራፍ አምስት.....87
ማጠቃልያና አስተያየት.....87
5.1 ማጠቃልያ 87
5.2 አስተያየት.....90
ዋቢ ፅሁፎች.....92
መዳዩ ቃላት.....98
አባሪ ‹‹ሀ››.....99
አባሪ ‹‹ለ››.....106

የሰንጠረዥ ማውጫ

ገፅ

ሰንጠረዥ 1፡- የ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት 53

ሰንጠረዥ 2፡- የ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት 55

ሰንጠረዥ 3፡- የ7ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት ትምህርቱን አውዳዊ አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች 59

ሰንጠረዥ 4፡- የ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ 60

ሰንጠረዥ 5፡- ስለቃላት ፍቻዊ ዝምድና አቀራረብ ከ7ኛ ክፍል መፅሀፍ የተገኙ መረጃዎች ተንተና 65

ሰንጠረዥ 6፡- ስለቃላት ፍቻዊ ዝምድና አቀራረብ ከ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የተገኙ መረጃዎች ትንተና 66

ሰንጠረዥ 7፡- የ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት አመሰራረትን የተመለከቱ መረጃዎች 73

ሰንጠረዥ 8፡- በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህረቶች ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት የተመለከቱ መረጃዎች ተንተና 81

ሰንጠረዥ 9፡- በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት ትምህርቶች መካከል ከክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት የተመለከቱ መረጃዎች 83

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በአማራ ክልል ለመጀመሪያ ደረጃ ለሁለተኛ እርከን የተዘጋጁት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፎች የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ቃላትን ከማስተማር አኳያ ያላቸውን ብቃት መፈተሽ ነው። ጥናቱን ከግብ ለማድረስም የተለያዩ ምሁራን ስለቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ባነሷቸው ንድፈሀሳባዊ መሰረቶችና መርሆች ላይ በመመርኮዝ አጥኝው በመማሪያ መፅሀፎቹ ላይ የሰነድ ፍተሻ ማድረግ እና በአጋዥነትም የመፅሀፎቹን አዘጋጆች ቃለ መጠይቅ ማድረግን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል።

የጥናቱ ውጤት እንደጠቆመው ለትምህርት እርከኑ የሚመጥኑ ቃላት መረጣ የተከናወነው በመስኩ ምሁራን ለዚህ ተግባር እንዲውሉ ከተሰነዘሩ መስፈርቶች ሁለቱን ብቻ በመጠቀም ነው። እነዚህም አንደኛው አንድ ቃል ሰፊ አገልግሎት ሽፋንና ስርጭት ባይኖረውም እንኳ ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርብ ውህድ አሀድ ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሲገኝ የሚመረጥበት በቅርብ የመገኘት መስፈርት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቃሉን ተስተማሪነት የተመለከተ ነው። ሌሎቹ የቃላት ድግግሞሽ፣ የቃላት የፍቺ ሽፋን፣ የቃላት የስርጭት ባህሪ እና የተማሪዎችን ፍላጎት ከግምት በማስገባት መምረጥ ትኩረት አልተደረገባቸውም። ይህ ደግሞ በመፅሀፎቹ የቃላት ትምህርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ በጥናቱ ተደርሶበታል። በዚህም የቃላት የከታች ተከታች የፍቺ ግንኙነትን፣ ፊሊጣዊ ቃላትን፣ አያያዥ ቃላትን የተመለከቱ ይዘቶች በተተኳሪ መፅሀፎቹ ውስጥ ምንም ይዘት አልተካተተም።

በሌላ በኩል በሁለቱም መማሪያ መፅሀፎች የጥምር ቃላት ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም በሚያስችል መልክ አለመቅረባቸውን፣ የቃላት ትምህርቱ በተለይ ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑንና ተማሪዎች የመዘገበ ቃላትን አጠቃቀም ጥበብ እንዲያውቁ የሚያግዙ መልመጃዎች በጥራትና በበቂ መጠን አለመካተታቸውን ጥናቱ ጠቁሟል። በመጨረሻም ጥናቱ የመማሪያ መፅሀፎቹ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ችግሮችን ለመቅረፍ ያስችላሉ ያላቸውን አስተያየቶች ሰንዝሯል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ መማሪያ መፃህፍት በትምህርትና በቋንቋ ሳይንስ መርሆች ላይ ተመስርተው በተገቢው መንገድ ከተዘጋጁ የመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ቀላል እንዲሆንና ፍሬያማ ውጤት እንዲያስገኝ በማድረግ በኩል ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። Hutchinson እና Torres (1994) እንደሚገልፁት ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ውይይት ሲያካሂዱ፣ መልመጃዎችን ሲሰሩ፣ የቋንቋ ተግባራትን ሲያከናውኑ፣ ሲያጠኑ፣ የቤት ስራ ሲሰሩ፣ ለፈተና ሲዘጋጁ ወዘተ መማሪያ መፃህፍትን ይጠቀማሉ። በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ትምህርታቸውን በማደራጀት በኩል እገዛ ስለሚያደርጉላቸውም እንደ መመሪያ አድርገው ይመለከቷቸዋል። መምህራኑም ቢሆን መማሪያ መፃህፍቱ ከተማሪዎቻቸው ፍላጎት ጋር የተስማሙ የትምህርት ይዘቶችን ስለሚያቀርቡ፣ ተማሪዎቻቸው ተምረው ያለፉትን፣ አሁን እየተማሩት ያለውንና ወደፊት የሚማሩትን ስለሚያሳዩ፣ የመማር ተግባሩና ሂደቱ ቀላልና ፈጣን እንዲሆን ስለሚያግዙ እንዲሁም ከጊዜና ከገንዘብ አንፃር ወጪ ቆጣቢ ስለሆኑ በነሱ በመገልገል ያስተምራሉ።

እንደ Dubin እና Olishtain (1992) ገለፃም ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው የሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት የታላሚውን ቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶችን አቀናብረው የያዙና የቋንቋውን ስነልሳናዊና ስነትምህርታዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል። ስነልሳናዊ ይዘቶች ስንል በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ድምፆች፣ ቃላት፣ ዓረፍተነገሮች፣ ወዘተ ይመለከታል። ይህም አንድ ድምፅ ከሌላ ድምፅ ጋር ሲቀናጅ ምን አይነት ባህሪ እንደሚያሳይ፣ አንድ ቃል በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያላውን አገባብና አገልግሎት ምን እንደሚመስልና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታል። ስለዚህ ስነልሳናዊ ይዘት ከምን ተነስተን ምን እንደምናስተምርና ምን ላይ ማተኮር እንዳለብን ለመወሰን ይረዳናል። ስነትምህርታዊ ይዘት ስንል ደግሞ ተማሪው ቀድሞ ምን ተምሯል?፣ አሁን

ምን አይነት ይዘት ይፈልጋል?፣ በቋንቋው ምን መጠቀም ይፈልጋል?፣ ይዘቶች እንዴት መቅረብ አለባቸው? እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታል። ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ ስነልሳናዊና ትምህርታዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው በማለት Dubin እና Olishtain (1992) ያስረዳሉ።

ከዚህ የምንረዳው ስነልሳናዊና ስነትምህርታዊ ግንዛቤዎችን ግምት ውስጥ አስገብተው የተዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካ ከማድረግ አንፃር ጉልህ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ነው። በዚህ ሁኔታ የተዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትም በውስጣቸው የተለያዩ ይዘቶችን አካተው ይይዛሉ። ከነዚህ ይዘቶች መካከል አንዱ ቃላትን የሚመለከት ይዘት ነው።

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በስፋት ከሚያካትታቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ውስጥ ቃላት ተጠቃሽ እንደሆኑ ከላይ ለመግለፅ ተሞክሯል። Seal (1991) እንደሚገልፁት የአንድ ቋንቋ ቃላት በህንፃ ጡብ ይመሰላሉ፤ በእነሱም ላይ በመመስረት የቋንቋ እውቀት ይገነባል። መሰረታዊ የቋንቋ አካላት በመሆናቸውም አንድ ሰው በቂ የቃላት እውቀት ከሌለው ሃሳቡን በተሳካ ሁኔታ ሊገልፅም ሆነ የሌሎችን ሃሳብ ሊቀበል አይችልም። እንዲሁም McCarthy (1990) እንደሚገልፁት የማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ወሳኝ አካላት ቃላት ናቸው። ቃላት ፍቺን የመሸከም ከፍተኛ ሀይል አላቸው። ተማሪው የቱንም ያህል ለትምህርት የቀረበለትን ቋንቋ ድምፆችና ሰዋስውን ቢያውቅ የቃላት እውቀት ከሌለው በቋንቋው ተጠቅሞ ስኬታማ ተግባቦታዊ ተግባራትን ለማከናወን ይሳነዋል። ይህ የቃላት ፍቺን የመሸከም ቅልፍ ሚና በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የቃላት ጥናት ዋነኛ ተተኳሪ ጉዳይ እንዲሆን አድርጎታል። በተጨማሪም ሞላ (2003) Batstone (1994b:231)ን በመጥቀስ ቃላት በልሳን ለሚከናወን ተግባቦት አስኳል ናቸው። በጥናት እንደተረጋገጠው በቋንቋ ለመዳ ሂደት ከስነ አገባብ እውቀት በፊት በቅድሚያ የሚዳብረው የቃላት እውቀት ነው። ከዚህም ለቋንቋ ትምህርት መሰረቱ የቃላት ትምህርት መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል በማለት ያስረዳሉ።

Richards (1985) የቃላትን ትምህርት በመማሪያ መፃህፍት በማካተቱ ሂደት የስነልሳን፣ የስነልቦናዊ ስነልሳንና የማህበራዊ ስነልሳን እውቀቶችን መሰረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ። በእነዚህ የጥናት መስኮች ምርኩዝነትም የቃላት እውቀት ምንድን ነው?

ቃላትን ማስታወስ የሚቻለው እንዴት ነው? የቃላት አጠቃቀም ማህበራዊ እይታ ምን ይመስላል? ቃላትን መረዳትና በተፈለጉ ጊዜ አፍልቆ መጠቀም የሚቻለው እንዴት ነው? ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ከማፈላለግ ጎን ለጎን ተማሪው እንዲኖረው የምንፈልገውን የቃላት እውቀት በትምህርት መርሀግብሩ እንዴት ማስጨበጥ እንደሚቻል በጥናት የተደገፉ መንገዶችን መቀየስ አስፈላጊ ነው።

Wallace (1988) እንደሚገልፁት የአንድን ቋንቋ ቃላት አወቀ ለመሰኘት የቃላቱን የንግግር ወይም የፅህፈት ቅርፅ መለየትን፣ በተፈለገ ጊዜ ማስታወስ መቻልን፣ እማሬያዊ (denotation) እና ፍክሬያዊ (connotation) ፍቺ መለየትን ይጠይቃል። እንዲሁም Gairns and Redman (1986) እና Harmer (1994) ደግሞ የታላሚ ቋንቋ ተማሪዎች ይሸንን እውቀት እንዲላበሱ ለማድረግ እንዲማሯቸው የሚቀርቡላቸው ቃላት አመራረጥ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ የቃላት ተጨባጭነት (concretness) ወይም ረቂቅነት (abstractness)፣ የድግግሞሽ መጠን (frecuency) ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።

የተመረጡት ቃላት ከሚማረው ሰው ተዋህደው እንዲቀሩ አቀራረባቸው የተደራጀ መሆን አለበት። የተደራጀ አቀራረብ እንዲኖር ቃላትን በፍቺ፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ እና በቅርፅ መመሳሰል ማቧደን ይቻላል። ቃላትን በተለያየ መስፈርት አቧድኖ ማቅረቡ ትምህርቱን ተያያዥነት ያለው ከማድረጉም በላይ ተቀራራቢ ፍቺ ባላቸው ቃላት መካከል ያለውንም ልዩነት ለማጤን ይረዳል (Gairns እና Redman□1986)። ቃላትን ለመማር ከመመቸታቸው፣ ከተፈላጊነታቸው፣ ጉልህ ውይም ረቂቅ ከመሆናቸው አንፃር ማደራጀት የቃላትን ትምህርት የተቀናበረ ያደርገዋል። የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተቀናበረ የቃላት ትምህርት እንዲይዙ በተለያየ ጊዜ ግምገማ በማካሄድ ድክመታቸውን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው።

Elley (1989) እንደሚገልፁት ግምገማ የቋንቋ ትምህርት መርሀግብር አካል ነው። በመሆኑም ተከታታይ ግምገማዎችን በማካሄድ የግምገማ ውጤቱን ተመርኩዞ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት የቋንቋ ትምህርት ደካማ ጎኖችን ለማስተካከልና የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ ያስችላል። ስለዚህ በየጊዜው የሚታተሙ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሚፈለገውን ዓላማ ከግብ እንዲያደርሱ ከተፈለገ የይዘት አመራረጣቸውን፣ አቀራረባቸውንና አደረጃጀታቸውን መገምገም ያስፈልጋል።

አሁን ባለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከ1ኛ-8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ነው። በክልሎች ከሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት መካከል በ1997ዓ.ም በአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የተዘጋጁት የአማራ ክልል የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ተጠቃሾች ናቸው። የዚህ ጥናት አብይ ትኩረትም በስራ ላይ ያለውን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በአማራ ክልል ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲያገለግሉ በ1997ዓ.ም የታተሙት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርትን በማስተማር ረገድ ያላቸውን ብቃት መፈተሽ ነው።

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝው ይህንን ጥናት ለማጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች ሁለት ናቸው። አንደኛው ምንም እንኳን የቃላት ትምህርትን አቀራረብ በተመለከተ የተወሰኑ ስራዎች ቢሰሩም በአማራ ክልል የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል አማርኛ መፃህፍትን በተመለከተ የተሰሩ ጥናቶች አጥኝው ባደረገው ዳሰሳ ባለማግኘቱ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ነው። ሁለተኛው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በሚዘጋጁበት ጊዜ በአደረጃጀታቸውም ሆነ በአቀራረባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ናቸው። አጥኝው የሰዋስው ኮርስ በሚማርበት ጊዜ በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ትንተና በሚል ርዕስ ፅሁፍ አቅርቦ ስለነበር ያኔ መማሪያ መፅሀፎቹን የማየት እድል አግኝቶ ነበር። በዚህም የቃላት ትምህርቱን በትኩረት ስላያቸውና ጥያቄም ስላጫረበት ለመስራት ተነሳስቷል። ስለዚህ በመፃህፍቱ ውስጥ ቃላትን ለማስተማር የተመረጡት የቃላት ትምህርቶች የዘርፉ ምሁራን በጠቆሟቸው የቃላት መምረጫ፣ ማደራጃና ማቅረቢያ መንገዶች በመጠቀም በመፅሀፎቹ ውስጥ ቀርበው ይሆን?፣ ቃላትን ለማስተማርስ ምን ያህል ብቃት አላቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ሌሎቹ አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው።

1.3 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማራ ክልል ለመጀመሪያ ደረጃ ለሁለተኛ እርከን የተዘጋጁት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ቃላትን ከማስተማር አኳያ ያላቸውን ብቃት መፈተሽ ነው። ከዚህም በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ንዑስ ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. የመማህፍቱን የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለመምረጥ በስራ ላይ የዋሉት መስፈርቶች ተገቢ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር፤
2. የመማሪያ መማህፍቱ የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ለቃላት ትምህርት አደረጃጀት ምሁራን የሚጠቅሷቸውን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ መደራጀት አለመደራጀታቸውን መፈተሽ፤
3. በመማሪያ መማህፍቱ ውስጥ የቃላት ትምህርቱ ተገቢ የሆኑትን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶች በመጠቀም መቅረብ አለመቅረባቸውን መመርመር፤
4. በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች የቃላቱን የተለያዩ የፍቺ ገፅታዎች ለመቃኘትና ቃላቱን አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችል አቀራረብ ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ፤ የሚሉት ናቸው።

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

የመማሪያ መማህፍቱን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ገንቢነት ባለው ሁኔታ ማጥናት የማስተማሪያ መሳሪያዎችንና የትምህርት ዘዴዎችን ለማሻሻል ይረዳል። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ በአጥኝው ይታመናል።

- ✓ በጥናቱ ከቋንቋና ከትምህርት ሳይንስ የተገኙ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥና አደረጃጀት መርሆችና በምርምር የተደገፉ የቃላት አቀራረብ ስልቶች ስለሚዳሰሱ የቃላት ትምህርትን መርጦና አደራጅቶ ስለማቅረብ የተሻለ ግንዛቤ ያስጨብጣል፤
- ✓ በመማህፍቱ የቃላት ትምህርት ይዘት ላይ ወደፊት ለሚደረግ መሻሻያ ጠቃሚ ሀሳቦችን ይጠቁማል፤
- ✓ ወደፊት በዚህ መስክ ለሚካሄዱ ጥናቶች መነሻ ሀሳብ ይሰጣል የሚሉት ናቸው።

1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱ የአማራ ክልል የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መማህፍት የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ቃላትን ከማስተማር አኳያ ያላቸውን ብቃት መፈተሽ ነው። በመሆኑም በመማህፍቱ የቀረቡ ሌሎች በቋንቋ ክሂሎች፣ በስነልሳንና በስነፅሁፍ ላይ ያተኮሩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ አይመለከትም። በሌላም በኩል በቃላት ትምህርት

አሰጣጥ የመምህር-ተማሪ መስተጋብር፣ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣ የመምህራን የቃላት ትምህርት አተገባበር ከዚህ ጥናት መጠነ ርዕይ ውጭ ናቸው።

ከዚህም ሌላ ጥናቱን ለማካሄድ በሚጠይቀው ከፍተኛ ወጭና ጊዜ ምክንያት የተተኳሪ መማህፍቱን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ለትምህርት እርከኑ ከተሰናዱ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መርሀ ትምህርቶች ጋር ያለውን ተያያዥነት አይመረምርም። ስለዚህም የመርሀ ትምህርቶቹ ዓላማና ይዘቶቹ በተተኳሪ መማህፍቱ የተንፀባረቁበትን አግባብ እንዲሁም የትምህርት መሳሪያዎቹ (መርሀ ትምህርቶች፣ የመምህሩ መምሪያዎች እና መማሪያ መማህፍቱ) ያላቸውን ተያያዥነት አይፈትሽም።

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት

2.1 የቃላት ትምህርት ምንነት

የቃልን ምንነት በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን የብያኔ ሀሳብ ሰንዝረዋል። ከነዚህም መካከል Ur (1996፣60) ቃል በጥሬው ሲታይ የተወሰነ ፅንሰ ሀሳብ የሚወክል የድምፆች ቅንጅት ነው። አፍፈቱ የሚለምደው ኢ-አፍፈቱ የሚማረው በማለት ያብራሩታል። ሌላው McCarthy (1990፣3) እንደሚገልፀትም ቃላት ትርጉም ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ የቋንቋ አሀዶች ናቸው። ሌላው ባየ (2000፣72-74) በበኩላቸው ስለቃል ምንነትና በቃልና በምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ እንደገለፁት መጀመሪያ ነገር ቃልም እንደምዕላድ ሁሉ ትርጉም አለው። ሁለተኛም ቃል ራሱን ችሎ ስለሚቆም ነፃ ነው፤ ጥገኛ አይደለም። በዚህ ባህሪው ከነፃ ምዕላድ ጋር ይመደባል። ሶስተኛም ቃል በውስጡ ብዙ ጥገኛ ምዕላዶችን ሊይዝ ይችላል። ትርጉም አዘል ወደሆኑ አነስተኛ ክፍሎች ሊሸነሸን ይችላል ማለት ነው። በዚህ ባህሪው ደግሞ ከምዕላድ ይለያል። ምክንያቱም ምዕላድ ወደ አነስተኛ ክፍሎች ሊሸነሸን አይችልም ብለናልና በማለት ያብራሩታል።

በተጨማሪም Ur (1996) እና Lewis እና Hill (1992) ቃል ከቃል ግንድና ቅጥያ ምዕላድ ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት ጥምረት ሊመሰረት ይችላል። ለምሳሌ /እንጀራ እናት/ የሚለውን ቃል ብንመለከት ከሁለት ምዕላዶች የተገነባ ሲሆን ምዕላዶቹ ራሳቸውን ችለው ሊቆሙ የሚችሉ ቃላት ናቸው። ይሁን እንጅ /እንጀራ እናት/ የሚለው የሁለት ቃላት ቅንጅት የቆመው ለአንድ ነጠላ ፍቺ በመሆኑ አንድ ቃል ነው። ከአንድ ቃል በላይ የሆኑ ቃላዊ ሀረጎች በቃላት ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉበት ሁኔታ አለ። እነዚህ ቃላዊ ሀረጋት ልክ እንደ ነጠላ ቃል ሁሉ በመዝገበ ቃላት ውስጥ በተደጋጋሚ ሊያጋጥሙ ይችላሉ። የአንዳንዶቹ ፍቺ ከተጣማሪ ቃላቱ ተናጥላዊ ፍቺ በመነሳት ወዲያውኑ ሊታወቅ የሚችል ሲሆን (ለምሳሌ ብረት ምጣድ)፣ የአንዳንዶቹ ደግሞ ከተዋቀሩባቸው ቃላት ነጠላ

ፍቺ በመነሳት ፍቺያቸው ሊደረስበት የማይችል (ለምሳሌ ደጀ ሰላም) አይነት ይሆናሉ፤ በማለት ይገልፃሉ።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ቃላት Carter እና McCarthy (1988፣19) በዝርዝር የገለጿቸው፣ ፍቺ ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ነጠላ ቃላት፣ በተለያዩ የእርባታና የምስረታ ቅጥያ ምዕላዶች የተመሰረቱና የረቡ ቃላት፣ በጥመራ የተመሰረቱ ቃላት፣ ፈሊጣዊ ቃላት(አነጋገሮች) እንዲሁም የተለመዱ አገላለፆች ናቸው።

2.2 የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት

በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በዚህም ምክንያት በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ለቃላት ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ምሁራን ይናገራሉ። ከነዚህም ውስጥ Candlin (1988፣vii) የቃላት ጥናት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ እንብርት ጉዳይ ነው፤ በማለት ያብራራሉ። እንዲሁም ደግሞ Harmer (1994፣53) የቃላትን ወሳኝነት የሚገልፁት የቋንቋ መዋቅር (structure) የቋንቋን አፅም የሚፈጥር ከሆነ መሰረታዊ ብልቶቹና ስጋው የሚደራጀው ከቃላት ነው፤ በማለት ነው።

Pikulski እና Templeton (2004) እንደሚገልፁት ቃላት እለት በእለት በምናደርገው አጠቃላይ መስተጋብር ማለትም ሀሳብ መለዋወጥን፣ መልዕክት ማስተላለፍን፣ ጥያቄ ማቅረብንና የመሳሰሉትን ነገሮች ለማሳከት የምንጠቀምባቸው ሁለገብ የቋንቋ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብና በመፃፍ ለመግባባት ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው። ተማሪዎች በቋንቋው የሚፈጥሩት ተግባቦት የጠራና የቀለጠፈ ይሆን ዘንድ ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው።

በቋንቋ መግባባት ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ከላይ ተገልጿል። በቋንቋው ከመግባባት አንፃር የቃላት እውቀትን ሚና ከሰዋስው እውቀት ጋር በማነፃፀር የላቀ መሆኑን የሚገልፁ ምሁራንም አሉ። ከነዚህም ዎላስ Wallace (1988፣9) የአንድ ቋንቋ ስርዓት እንዴት እንደሚሰራ በጥሩ ሁኔታ ማወቅ እየተቻለ በቋንቋው ለመግባባት የሚያስችል እውቀት ላይኖር ይችላል። የምንፈልጋቸው ቃላት

የሚኖሩን ከሆነ ግን ብዙውን ጊዜ እንደነገሩም ቢሆን በቋንቋው መግባባት ይቻላል፤ በማለት ይገልፃሉ። በማያያዝም Wallace (1988፣ 27) በቋንቋ ትምህርት ቃላት ያላቸውን ቁልፍ ሚና እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

- በንግግር ወቅት የቃላትን ትክክለኛ ቅላፄ እንዲጠቀሙ፤
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲገነዘቡ፤
- ቃላትን ከሚወክሉት ቁስና ዕንሰ ሃሳብ ጋር ማዛመድ እንዲችሉ፤
- ቃላትን በተገቢው ሰዋስዋዊ ቅርፅ እንዲጠቀሙባቸው፤
- የቃላትን ትክክለኛ ዘይቤያዊ አጠቃቀም እንዲገነዘቡ፤
- የቃላትን የንግግር ወይም የፅሀፈት ቅርፅ ለመለየት፤
- የቃላት ተገቢውን የመደበኛነት ደረጃ ጠብቀው እንዲጠቀሙ ይረዱዋቸዋል።

እንግዲህ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የቃላት ትምህርት ለቋንቋ እውቀት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው።

በሌላ በኩል የቃላት ትምህርት በቋንቋ መማሪያ መፃህፍ ውስጥ ተገቢው ቦታ ተሰጥቷቸዋል ለማለት አያስደፍርም። ይህንንም በተመለከተ Carter እና McCarthy (1988፣41) ላይ የቃላት ትምህርት በመርህትምህርት እየታቀፈ በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ስፍራ ተሰጥቶት በትምህርትነት ሲቀርብ ቢቆይም ቃላትን ለማስተማር ተገቢ የሚሆነውን ዘዴና ስልት ማፈላለግ ተዘንግቶ የቆየ ተግባር ነበር። በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተለይ ከ1970ዎቹ በፊት ቃላት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ራሳቸውን የቻሉ የቋንቋ ትምህርት አካላት ተደርገው አይታዩም ነበር። ስለዚህም የቋንቋ ትምህርት የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ጠንቅቆ በማወቅ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላትም የቋንቋውን መዋቅር ለማሳየት አስፈላጊ የሆኑት ብቻ ነበሩ፤ በማለት ይገልፃሉ።

በጊዜው የነበሩ የተግባራዊ ስነልሳን ምሁራንም ተማሪዎች መሰረታዊ የሆኑ የቋንቋ አወቃቀሮችን ከለዩ በኋላ ሰፋ ያለ የቃላት እውቀታቸው ቀስ በቀስ ሊገነባ ይችላል የሚል

እምነት ነበራቸው። ስለዚህም ትኩረታቸውን ያሳረፉት የቋንቋውን መዋቅር ለማስተማር አስፈላጊ በሆኑ ቃላት መረጣና የቋንቋ ለመዳውን ለማፋጠን ያግዛል ባሉት በንፅፅራዊ ጥናት ትንተና ላይ ነበር (Nunan 1998፤8)። ይሁን እንጂ ይህ የቃላት ትምህርትን አስፈላጊነት የመዘንጋት ሁኔታ ሊቀጥል አልቻለም። ይህንንም በተመለከተ Carter እና McCarthy (1988፤45) ከ1970ዎቹ በኋላ በነበሩት ጥቂት አመታት ውስጥ የቃላት ትምህርት በቋንቋ መማር ውስጥ ተገቢ ቦታውን እያገኘና እንደክሂል እየተቆጠረ የመምጣቱ ሁኔታ እውን ሆኖአል በማለት ይገልፃሉ።

የቃላት ትምህርት ትኩረት እንዲቸረውና አስፈላጊነቱ እንዲጎላ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የስነልሳን ምሁራን ብዙ ናቸው። ከነዚህም መካከል Wilkins እና Judd ተጠቃሾች እንደሆኑ የሺጥላ (1997) ላይ ይገልፃሉ። የሺጥላ (1997) ላይ Wilkins (1972)ን በመጥቀስ ያለ ሰዋስው በጣም ጥቂት መልዕክት ሊተላለፍ ይችላል፤ ያለ ቃላት ግን ምንም መልዕክት ሊተላለፍ አይችልም፤ በማለት ቃላት የቋንቋ ዋነኛ አካላት እንደሆኑና በቋንቋ መማር ሂደት ከሰዋስው ይልቅ ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ አመልክተዋል።

በተጨማሪም የሺጥላ (1997) Judd (1978)ን በመጥቀስ በጊዜው የነበረውን የቃላት ትምህርት ይዞታ በመገምገም ቃላት ለስነአገባብ ሲባል ከደረጃቸው ዝቅ እንዲሉ ተደርገዋል፤...የቃላት እውቀትም በራሱ እንደክሂል ተቆጥሮ በትምህርትነት እየተሰጠ አይደለም፤ ካሉ በኋላ የቃላት ትምህርት እንደ ሰዋስው ማስተማሪያ መሳሪያ እንጂ በራሱ ግብ ተደርጎ አለመሰጠቱ የቋንቋ መማርን እንደሚጎዳ አብራርተዋል። እንደመፍትሄም በቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ላይ ለውጥ መደረግ እንዳለበትና ቃላት ለተማሪዎች ትርጉም እንዲኖራቸውና የቋንቋ መማርም ስኬታማ እንዲሆን ከተፈለገ ቀጥተኛ የሆነ የቃላት ትምህርት ራሱን ችሎ ከጅማሪዎቹ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች በሰፊው ሊሰጥ እንደሚገባ ይመክራሉ። ይህ በጊዜው የነበሩ የመስኩ ምሁራን ለቃላት ትምህርት የሰጡት ትኩረት ቃላት ስነአገባብን ለማስተማር ባላቸው ንዑስ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን የቻሉ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተደርገው እንዲወሰዱ እንዲሁም በመርህ ትምህርት ቀረፃ የቃላት ትምህርት ዕንሰ ሀሳብ እንዲሰርፅ ረድቷል።

በአጠቃላይ ቃላት በቋንቋ ለሚከናወን ተግባቦት አስኳል ናቸው። የቋንቋ ምሁራን እንደሚሉትም በቋንቋ ለመዳ ሂደት ከስነአገባብ እውቀት በፊት በቅድሚያ የሚዳብረው

የቃላት እውቀት ነው። ስለዚህም በቋንቋ ትምህርትም መሰረቱ የቃላት ትምህርት መሆን እንዳለበት ለመረዳት አያዳግትም።

2.3 የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ

በቋንቋ እውቀት ውስጥ የቃላት ሚና የላቀ ይሁን እንጂ የአንድን ቋንቋ ቃላት ባንድ ጊዜና ቦታ ሁሉንም አቅርቦ ማስጠናት ስለማይቻል መምረጥ አስፈላጊ ነው። በተለይም በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ለማቅረብ መምረጥ አስፈላጊ እንደሆነ አጠያያቂ አይደለም፤ አመራረጡ ላይ እንጂ። አመራረጡን በተመለከተ Hatch እና Brown (1995፣405) በመማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ሂደት ውስጥ የትኞቹ ቃላት ለተማሪዎች በመሰረታዊነት እንደሚያስፈልጉ መወሰን ዋና ጉዳይ ነው በማለት ይገልፃሉ። ከላይ መረዳት እንደሚቻለው መማሪያ መፅሀፎች በሚዘገጁበት ጊዜ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን መወሰንና መለየት አስፈላጊ መሆኑን ነው።

ነገር ግን አንድ የሚነሳ ጥያቄ አለ ይህም ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ቃላትን እንዴት እንምረጣቸው የሚለው ነው። ይህንንም Sinclair እና Renouf (1988፣148) በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ስለሚካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ሲነሳ ለተማሪዎች ባላቸው ጠቀሜታ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቃላት እንዴት ይመረጡ? የሚለው አብይ ጥያቄ ነው። የስነልሳን ምሁራንም ለጥያቄው ምላሽ የሚሆን የቃላት መምረጫ መስፈርት ለማዘጋጀት ለበርካታ አመታት የተለያዩ መከራዎችን አድርገዋል በማለት ያጠናክሩታል። ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት ከሞከሩት መካከልም Pikulski እና Templeton (2004፣61-62)፣ የቃላትን ትምህርት ለእለት ተእለት መግባቢያነት በሚያገለግሉ ቃላት መጀመር ያስፈልጋል። ይህም ቀስ በቀስ የቃላትን የአገልግሎት ደረጃና ተገቢነት ተከትሎ ለማስተማር ያግዛል በማለት ያብራሩትን መጥቀስ ይቻላል።

ለመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን ከአስፈላጊነታቸው በመነሳት መምርጥ እንዳለብንና ልንከተላቸው ስለሚገቡ መስፈርቶች የተለያዩ ምሁራን የሚዘረዝሯቸው ነጥቦች አሉ። ከነዚህም መካከል Gairns እና Redman (1986፣ 57-64) የቃላት የድግግሞሽ መጠንን (Frequency)፣ ባህላዊ ተላውጦን (Cultural factors)፣ የተማሪውን ፍላጎትና የብስለት ደረጃ (Need and Level) እና የቃላቱን አስፈላጊነት

(expendiency) ከግምት በማስገባት ተፈላጊዎችን መምረጥ እንደሚቻል ያስረዳሉ። እንዲሁም Harmer (1991፣ 154-156) ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የቃላትን የፍቺ ሽፋን እና የቃላትን ረቂቅነትና ተጨባጭነት ከግምት ማስገባት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ። McCarthy (1990፣79-90) ደግሞ ከተጠቀሱት የተለየ ተስተማሪነትን (learnability) በመጨመር የመምረጫ መስፈርቶችን ይዘረዝራሉ። እነዚህን መስፈርቶች ከሚያነሷቸው ነጥቦች አንፃር የቃላት የድግግሞሽ መጠን፣ ተስተማሪነት፣ የተማሪው ፍላጎትና የቃላት የፍቺ ሽፋን በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች በዝርዝር ለማየት እንሞክር።

2.3.1 የቃላት የድግግሞሽ መጠን (frequency)

እነ Biber et.al (1998፣53) ድግግሞሽ በውሀድ አሀድ ስብስቦች ላይ ያተኮረ የቃላት አጠቃቀም ጥናትን መሰረት በማድረግ በጣም ተደጋግመው የተከሰቱ ቃላትን መለየት የሚቻልበት ስልት ነው። የማስተማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁም የቃላት ትምህርት ይዘታቸውን ለመወሰን አንዱ ጠቃሚ መስፈርት በመሆን ያገለግላል፤ በማለት ይገልፃሉ። እንዲሁም Nunan (1998፣118)፣ በዕለት ከዕለት ተግባቦት ሂደት የሚያገለግሉ ተዘውታሪ ቃላትን ለይቶ ማስተማር ተማሪዎችን በቋንቋ ለመጠቀም የሚያስችል ውጤታማ የማስተማር ስልት እንደሆነ ያስረዳሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ McCarthy (1990፣66) በማንኛውም ቋንቋ በአጠቃቀም እጅግ በጣም ተደጋግመው የሚከሰቱ ቃላት ለዚያ ቋንቋ ጠቃሚዎች ናቸው። ስለሆነም የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ ተውታሪ ቃላትን አስቀድሞ ማስተማር ወሳኝ እንደሆነ ይገልፃሉ።

እንደ McCarten (2007፣4) ገለፃ፣ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርቡ ቃላት ተዝወታሪ ቃላት ሊሆኑ ይገባል። ተዘውታሪ ቃላትን መርጠ ቅደም ተከተላቸውን ለመወሰን በዕለት ከእለት በሚደረግ ተግባቦት ያላቸውን የድግግሞሽ መጠን (Frequency) ዝርዝር (Word list) አዘጋጅቶ መወሰን ይቻላል በማለት ያስረዳሉ። አያይዘውም McCarten (2007፣5-6) የአሀድ ስብስብ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላትን በመምረጥ ረገድ የትኖቹ ቃላት ወይም የተለመዱ አገላለፆች ተዘውታሪ እንደሆኑ፣ የንግግርና የፅሁፍ ቃላትን ለመለየት፣ የቃላትን አውዳዊ አጠቃቀምና የጠበቀ ቁርኝት ያላቸውን ቃላት ለመለየት ያስችላል፤ በማለት ያብራራሉ።

Nunan (1998፣119) ቋንቋን ለአጠቃላይ አላማ ማስተማር ሲፈለግ ተዘውታሪ ቃላትን በድግግሞሽ ቆጠራ ላይ ተመርኩዞ መምረጥ ተገቢ ሲሆን፣ ተዕዕኖ የሚያደርሱ ተላውጦዎችን በመቆጣጠር ከተከናወነም የቆጠራው ውጤት ከጠቃሚነት ጋር አውንታዊ የሆነ ግንኙነት ይኖረዋል፤ በማለት ያስረዳሉ። በድግግሞሽ ቆጠራ ውጤት ላይ ተዕእኖ የሚያሳድሩ በርከት ያሉ ተላውጦዎች እንዳሉ ምሁራን ያስገነዝባሉ። ከነዚህም መካካል McCarthy (1990፣66-68) እና Gairns እና Redman (1986፣55-59) የሚከተሉትን ይዘረዝራሉ።

1. የድግግሞሽ ቆጠራው የተካሄደበት የውህድ አሀድ ስብስብ መጠን፡- የስብስቡ መጠን መብዛት ውጤቱን በማስተማመን ረገድ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

2. የውህድ አሀድ ስብስቡ ከዕሁፍ፣ ከንግግር ወይም ከሁለቱም መገኘቱ፡- ስብስቡ ከዕሁፍ ብቻ ሳይሆን ከንግግርም የተወሰደ ቢሆን ይመረጣል።

3. ቆጠራው የአንድን ቃል የተለያዩ እርባታዎች እንደ አንድ ቃል አለመመልከቱ፡- ያንድን ቃል የተለያዩ እርባታዎች ነጣጥሎ መመልከት ሰፋ ያለ መረጃን እንደሚሰጥ ይታመናል።

4. የውህድ አሀድ ስብስቡ የተቀናበረበት የጊዜ ርዝማኔ፡- የውህድ አሀዱ የተፃፈበት ወይም የተነገረበት የጊዜ ርዝማኔ የራሱ ተዕዕኖ ይኖረዋል።

5. ተቆጣሪው የውህድ አሀድ ስብስብ ያካተታቸው የውህድ አሀድ አይነቶች፣ ርዕሰ ጉዳዮች፣ ወዘተ መጠን፡- ይህ ስብስቡ ሁሉንም የውህድ አሀድ አይነቶችን፣ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ የተለያዩ ስርዓተ አባባሎችን ወዘቱ አካቶ ማይዝን ይመለከታል።

6. ቆጠራው ተደጋጋሚ የሆኑ ቃላዊ ሀረጎችን መጠቅለል አለመጠቅለሉ፡- በንግግርም ሆነ በዕሁፍ ውስጥ ቃላዊ ሀረጎች (ድርብ ቃላት፣ በቃላት ጥምረት የሚፈጠሩ ፊሊጦች፣ የተለመዱ ውስን አገላለፆች) በተደጋጋሚ ያጋጥማሉ። ስለዚህም ቆጠራው እነዚህንና ከአንድ ቃል ጋር አብረው የሚሰለፉ ቃላትን ድግግሞሽ የሚያሳይ ቢሆን የይዘት መረጣውን ያስተማምናል።

በአጠቃላይ ድግግሞሽ እንደቃላት መምረጫ መስፈርትነት በስራ ላይ ሲውል ከላይ የተዘረዘሩትን ተላውጠዎች ተቆጣጥሮ ተግባሩን በጥንቃቄ ማከናወን እንደሚገባ ምሁራን ያስገነዝባሉ።

ሌላው ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚነሳው ጉዳይ የስርጭት ሽፋን ነው። McCarthy (1990፣66) ለተማሪዎች ጠቃሚ ቃላት የሚባሉት በተለያዩ አሃዶች ውስጥ በመከሰት በጣም ተደጋጋሚ የሆኑት ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድግግሞሻቸው ሰፊ የስርጭት ሽፋን ያለው ከሆነ ነው። በመሆኑም አንድ ቃል ወይም ቃላዊ ሀረግ በተለያዩ አሃዶች ውስጥ በተደጋጋሚ ከተገኘ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ በትምህርት ይዘትነት ሊመረጥ ይገበዋል በማለት ይገልፃሉ።

2.3.2. ለትምህርት ምቹነት (Learnability)

McCarthy (1990፣86) እንደጠቆሙት፣ ቃላትን ለመማር አስቸጋሪ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች አሉ። ለምሳሌ ቃላት ውስብስብ ባህሪ ሲኖራቸውና ቃላቱ ከተማሪዎች ህይወትና የህይወት ልምድ ሲርቁ እንዲሁም ተማሪዎች የተለያዩ ቃላት በፍቺ ተመሳሳይ እንደሆኑ ሲያስቡ ቃልን ለመማር ይቸገራሉ። በመሆኑም በጣም ተደጋግመው በአገልግሎት ላይ የሚውሉ ቃላት የተስተማሪነት ደረጃቸው ከፍተኛ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት ከተማሪዎች የህይወት ልምድ ጋር የማይገናኙ ከሆኑና የቃላቶቹ አገባባዊ ባህሪ ውስብስብ ከሆነ ተስተማሪነት ደረጃቸው ዝቅተኛ ይሆናል በማለት ያብራራሉ። በተጨማሪም ተስተማሪነት አንድ ቃል ወይም ቃላዊ ሀረግ ለመማር ቀላል ወይም ከባድ ሆኖ መገኘቱን የሚመለከት ነው። ለመማር ቀላል ሆኖ ሲገኝ የተስማሪነት ደረጃው ከፍ ሲል፣ በአንፃሩ ከባድ ሆኖ ሲገኝ የተስተማሪነት ደረጃው ዝቅ ያለ ይሆናል (የሽጥላ 1997፣14)።

Richards (2009፣5) እንደሚገልፀትም ቃላትን ለትምህርትነት ስናቀርብ በዋናነት የቃሉን ተስተማሪነት ማሰብ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ይህም ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት ተስተማሪነታቸው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ እንዲሄዱ ይረዳል። የቃላት ትምህርቱ በዚህ ሁኔታ የሚቀርቡ ከሆነ ተማሪው የቀረበለትን ትምህርት ላውቀው እችላለሁ የሚል ስሜት ስለሚፈጥርለት የመማር

ስሜቱን ከመቀስቀስ አንባር ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል በማለት ያብራራሉ። ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በትምህርት ይዘትነት የሚቀርቡ ቃላት ከተስተማሪነት አንባር ሲታዩ ከተማሪዎች ህይወት ጋር የተያያዙ፣ ለመማር የማያስቸግሩና የተነላሽነት ስሜት የሚቀሰቅሱ ሊሆኑ ይገባል።

2.3.3 የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ

ተማሪ እንዲማር የሚቀርቡለት ቃላት ሲመረጡ ሊስተዋሉ ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ አንዱ ነው። McCarthy (1990፣69) የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ የተማሪውን እድሜ፣ የትምህርት ደረጃና የቀድሞውን እውቀት ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ። እንዲሁም Atkins (1996፣33) የመማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች ቃላትን ለመምረጥ ሲነሱ በመምህራን የተካሄዱ የተማሪዎች ፍላጎት አሰሳዎችን፣ በግል ደረጃ እያንዳንዱ ተማሪ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበውን ፍላጎትን በመተንበይ ማካተት እንደሚኖርባቸው ያስረዳሉ።

Allen (1983፣108) የተማሪዎችን ፍላጎት የመተንበይ ተግባር ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ በመፈለግ ሊከናወን እንደሚችል ይታመናል። ጥያቄዎቹም ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስላሉ ሰዎች፣ ስለነገሮችና ስለክስተቶች መናገር እንዲችሉ የትኞቹ ቃላት ያስፈልጓቸዋል? ሲማሩ በተደጋጋሚ ለሚያጋጥሟቸው መመሪያዎች ምላሽ መስጠት እንዲችሉ የትኞቹን ቃላት ማወቅ ይኖርባቸዋል? የተወሰነ አካዳሚያዊ ብቃታቸውን ለማሟላት የትኞቹን ቃላት ማወቅ ያስፈልጋቸዋል? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመመለስ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተማሪዎችን ፍላጎት በመተንበይ በቃላት መረጣው ለማካተት እንደሚቻል ይታመናል በማለት ያብራራሉ።

2.3.4 የቃላት የፍቺ ሽፋን

Lewis (1993) እና Carter እና McCarthy (1988) እንደሚገልጹት በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ፍቺን በማስተላለፍ በኩል እኩል የአገልግሎት ሽፋን የላቸውም። አንዳንድ ቃላት በርካታ ፍቺን መሸከም በመቻላቸው በተለያዩ አውዶች ሰፋ ያለ ፍቺን ያስተላልፋሉ። በርካታ ፍቺን መሸከም የሚችሉ ቃላት በተለያዩ አውዶች በስፋት

ተገኝተው መልዕክት ማስተላለፍ ሲችሉ ጠባብ ፍቺ ያላቸው ደግሞ ሰፊ ፍቺ ባላቸው ቃላት ይተካሉ።

ከዚህ አንፃር Wallace (1982፣18-19) እንደሚገልፁት አንዳንድ ቃላት ሰፊ ፍቺ ስላላቸው ሃሳብን አምቀው የመያዝ ችሎታ ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ጠባብ ፍቺ ስላላቸው ሰፊ ፍቺ ባላቸው ቃላት ስር ይጠቃለላሉ። በመሆኑም ቃላት ከሚሰጡት ትርጉም አንፃር እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የኖራቸዋል። ሰፊ ፍቺ ያላቸው ቃላት ምስጢርን አምቆ የመያዝ፣ ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ የተለየ ትርጉም የመስጠት ባህሪያቸው ፍካሬዊ ትርጉም ሲሆን ምንም ስውር ትርጉም ሳይኖረው ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ ሁሉ የጋራ የሆነ ግልፅ ትርጉም የመስጠት ባህሪያቸው ደግሞ እማሬያዊ ትርጉም ይባላል። እንዲህ ያለ ሁለት ፍቺ ያላቸው ቃላት የሚኖራቸው የአገልግሎት ሽፋን ሰፊ ነው። ስለዚህ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ተግባቦታዊ አውድ ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱና ሰፊ የፍቺ ሽፋን ያላቸው ቃላት በቃላት ትምህርት ይዘትነት ተመርጠው ሊካተቱ ይገባል።

2.4 የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

ለቋንቋ ትምህርትነት የሚውሉ ቃላት በመምረጫ መስፈርት መመረጥ እንዳለባቸው ከላይ ተመልክተናል። ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተመረጡት ቃላት በምን መንገድ መደራጀት እንዳለባቸው በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን። Dubin እና Olshtain (1986፣46-47) እንደሚያስረዱት አደረጃጀትን የተመለከቱ የአዳዲስ ርዕሰ ጉዳዮች አቀራረብ፣ ክትትሎሽና መጠነ ርዕይ ውሳኔዎች የሚመሰረቱት በስነትምህርታዊና ስነልሳናዊ እሳቤዎች እንዲሁም በሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት ግንዛቤ ላይ ይሆናል። እነዚህንም በተመለከተ የሽጥላ (1997፣16) እንደሚገልፁት በስነልሳናዊ እሳቤዎች መሰረት ብዙውን ጊዜ ቋንቋ ከተነጣጠሉ ቅንጣቶች (ቃላት፣ ሀረጋት፣ ዓ.ነገሮች) የተገነባ ተደርጎ ይወሰዳል። በመሆኑም የተነጣጠሉት ቅንጣቶች በጥንቃቄ በሚታቀዱ ተከታታይ ደረጃዎች ተስማሚ በሚሆኑበት ስልት ይደራጃሉ። በሌላ አንፃር የመማር ንድፈሀሳቦች የትምህርቱ ክትትሎሽና እድገት ከቀላል የቋንቋ ቅርፆች ወደ ከባድ ቅርፆች፣ በጣም በተደጋጋሚ በአገልግሎት ላይ

ከሚውሉ ቅርፆች አነስተኛ ድግግሞሽ ወዳላቸው ቅርፆች፣ ተዘውታሪ ከሆኑት ቅርፆች ተዝወታሪ ወዳልሆኑት የሚሄድ አደረጃጀት ሊኖረው እንደሚገባ ያስረዳሉ።

Nation (2000፣6) በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ አሀዶች እድገታቸውን ጠብቀው በትምህርቱ ሊሸፈኑ ይገባል፤ ይህም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የቋንቋ አሀዶች እድገት ባለው አካሄድ፣ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲማሩ በሚያስችላቸው ሁኔታ፣ የቃላት ትምህርት ማስታወስን የሚፈልግ መሆኑን ባገናዘበ መንገድ፣ በተወሰነ በጊዜ ርቀት በመደጋገምና በተለያዩ አውዶች ለመማር እድል በሚሰጥ መንገድ መደራጀት ይኖርባቸዋል። ከዚህም ሌላ ቃላት በቋንቋ ክንውኖች ውስጥ የድግግሞሽ መጠናቸውና እድገታቸውን ጠብቀው መደራጀት አለባቸው፤ በማለት ያስረዳሉ።

McCarthy (1990) እንደሚያስረዱት ቃላትን በተለያዩ አሃዶች ከፋፍሎ ለማቅረብ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ (Topic) እና የቅርፅ መመሳሰል እንዲሁም በሚኖራቸው የፍቺ ዝምድና ማደራጀት ይቻላል በማለት ያስረዳሉ። በተያያዘም ሞላ (2003፣16) ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት በመልመጃ ለማዋቀር የቃላቱን የተለያዩ የፍቺ ይዘቶች፣ ስነድምፃዊና ሰዋስዋዊ አወቃቀሮች መሰረት አድርጎ ማቀናጀት ይቻላል፤ በማለት ያስረዳሉ። ከዚህ አንፃር የማደራጃ መስፈርቶችን በዝርዝር ለማየት እንሞክር።

2.4.1 ቃላት በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት

ቃላትን በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት የራሱ የሆነ ድክመትም ጥንካሬም አለው። ይህንንም Gairns እና Redman (1986፣69) እንደሚሉት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ለአንድ ደረጃ የተመረጡ ቃላት የሚያገናኛቸውን ርዕሰ ጉዳይ በመግለፅ እንዲያገለግሉ ከተደረገ በኋላ ቃላቱ በመልመጃ መልክ ተደራጅተው ይቀርባሉ። በሌላ በኩል McCarthy (1990፣91) እንደሚገልፁት፣ ቃላት በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አደራጅቶ ማቅረብ የራሱ የሆነ ችግር አለው። ይኸውም ርዕሰ ጉዳይን በተጨባጭ ለመለየት ማስቸገሩ፣ የትኛው ርዕሰ ጉዳይ ለተማሪ ጠቃሚ እንደሆነ ለመለየት ማስቸገሩ፣ የርዕሰ ጉዳዩን ምንነት ማወቅ የሚሉትና የመሳሰሉት ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። ይሁን እንጂ አደራጅቶ የማቅረብ ችግር ቢኖርም ቃላትን አቧድኖ ማቅረብ ጠቃሚ ዘዴ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፤ በማለት ያስረዳሉ።

2.4.2 ቃላትን በፍቺ ማደራጀት

Carter እና McCarthy (1988፣18) እንደሚገልፁት፣ አንዳንድ ቃላት በርካታ የፍቺ አካባቢዎችን ታሳቢ በማድረግ ፍቻቸውን ይዘው ይገኛሉ። ለምሳሌ ፍልስፍና፣ ስሜቶችን ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። በሌላ በኩል አንዳንዶቹ ደግሞ የሚወክሉትን በቀጥታ ሊጠቁሙ የሚችሉ ጠባብ ፍቺ ያላቸው ናቸው። ለምሳሌ ቀለማት፣ የአናሚ መገልገያ እቃዎች ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው አንዳንድ ቃላት ሰፊ ፍቺ ሽፋን ያላቸው መሆኑንና አንዳንዶቹ ቃላት ደግሞ ጠባብ ፍቺ ሽፋን እንዳላቸው ነው።

የሽጥላ (1997፣18) እንደሚሉት ቃላት በፍቺ የሚደራጁበት ዋነኛው ምክንያት በፍቺያቸው ተቀራራቢ በመሆናቸው ሳቢያ አንድ የሚመስሉ ግን መጠነኛ የፍቺ ልዩነት ያላቸው ቃላትን (ለምሳሌ መዕናት፣ መዕናናት) ተማሪዎች እንዲለዩ ማድረግ ነው። እንዲሁም Gairns እና Redman (1986፣69) ቃልን በሚገባ ለመረዳት ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸው ቃሉ የሚወክለውን ፍቺ ብቻ ሳይሆን ተዛማጅ ፍቺ ካላቸው ቃላት የሚለየውንም ጭምር ነው። መጀመሪያ ቃላቱ የሚቀርቡበትን ተገቢ አውድ መፍጠር ይኖርብናል። ሁለተኛው ቃላትን ከአውዳቸው ፍቺያቸውን ለመገመት የሚያስችሉ የትንብያ ስልቶችን ከግምት አስገብተው የተማሪዎቹን የመገመት ብቃት ሊያሳድግ በሚችል አኳኋን ትምህርቱን ማደራጀት አለብን። ስለዚህ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ቃላትን ማደራጀት ከቻልን ተማሪዎች በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው የቃላትን ፍቺ ከአውድ የመረዳት አቅም ያዳብራሉ፤ በማለት ያስረዳሉ።

2.4.3 ቃላትን በቅርፅ ማደራጀት

McCarthy (1990፣99) ቃላትን ለማስተማር ቃላቱ ያላቸውን ውስጣዊ አደረጃጀት ለማየት በሚያስችል አኳኋን ማደራጀት ሌላው የቃላት ማደራጃ ስልት ነው። የቃላት አመሰራረት ጥናት ግልፅ እንደሚያደርገው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላት ለመመስረት በመደበኛነት ጥቂት ቁጥር ያላቸው የአመሰራረት ሂደቶች በጥቅም ላይ ይውላሉ። በመሆኑም የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ የቃላቱን አወቃቀር ስልት ለማሳየት የሚያስችል አደረጃጀት መከተል አስፈላጊ ነው። ሌላው ትውስታን የተመለከቱ ጥናቶች እንደሚያስረዱት አፍራቶች ቃላትን በአእምሮአቸው በማከማቸት በፈለጉ ጊዜ

አስታውሰው የሚመዘንበት ሂደት ብዙ ነው። ይኸውም ከአእምሮ መድበለ ቃላት አንዱ ቃል ሲነሳ የሚታወሰው ብቻውን ሳይሆን ከሚመሰርታቸው ሌሎች ምስርትና ድርብ ቃላት ጋር መሆኑ ነው፤ በማለት ያስረዳሉ።

ስለዚህም ምስርትና ጥምር ቃላትን እንደ አንድ አሀድ ለመማርና የቃላቱን ምእላዳዊ አወቃቀር እየበታተኑ ለመመርመር እንዲሁም ፍቺን ከተዋቃሪ ቅርፆች ጋር ለማዛመድ የሚያስችል ቅርፃዊ አደረጃጀት መከተል፣ ለትምህርት የሚቀርቡትን ቃላት ለመረዳትና ለማፍለቅ አስተዋፅኦው የጎላ ነው።

2.5 የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች

ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት በተማሪዎች አዕምሮ የግንዛቤ አሻራ ሊተው በሚችሉበት አኳኋን መቅረብ አለባቸው። እንዲሁም ተማሪዎች እድሜያቸውን፣ የትምህርት ዳራቸውን፣ የትምህርቱን አላማ፣ ለትምህርት የቀረቡትን የአዳዲስ ቃላት ባህሪ ባገናዘቡና ቃላቱን ለመጠቀም በሚያስችሉ ስልቶች በዳበሩ የቋንቋ መልመጃዎች ውስጥ ማለፍ ይኖርባቸዋል። የቃላት ትምህርት ቃላት እንዴት እንደሚለመዱ እና እንደሚዳብሩ በሚያሳዩ ጠንካራ እሳቤዎች ላይ በመመስረት መቅረብ አለበት በማለት ምሁራን ያስረዳሉ። ለዚህም Morgan እና Reinvlucri (1986፣3) ቃላት አንድ ነጠላ ትርጉም ብቻ ይዘው የምናገኛቸው ብቻ ሳይሆኑ እርስበርሳቸው የተሳሰሩ፣ በትስስሮሽ ሳቢያም የተለያዩ ቅርፆችና ፍቺዎችን የሚይዙም ናቸው። ስለዚህም ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እያገናዘቡ፣ የማሰብና የመተንበይ ችሎታቸውን እየተጠቀሙ ቅርፃቸውን ከፍቺያቸው ጋር ማወቅ በሚችሉበት አኳኋን ሊቀርቡ ይገባል፤ በማለት ያብራራሉ።

Seal(1991) እንደገለፁት የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተነጣጠለ ሳይሆን አንዱ ክንውን ቀጥሎ ካለው ተቆራኝና ደረጃ በደረጃ የተዋቀረ ሊሆን ይገባል። ይኸውም በመጀመሪያ አዳዲስ ቃላት ለተማሪዎች የሚቀርቡበት ሁኔታ ላይ ያተኩራል። በመቀጠል ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት መረዳታቸውን የሚረጋገጥበት ሂደት ይሆናል።

ከላይ መረዳት እንደሚቻለው በሁሉም ደረጃዎች የሚዘጋጁ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት የሚያነሳሱ፣ ተሳትፎአቸውን የሚያጎለብቱ፣

በራሳቸው ጥረት ቃላቱን እንዲያውቁ የሚገፋፏቸው ሆነው መሰናዳት እንደለባቸው ነው። የቃላት ትምህርቱ ትርጉም የሚኖረውም ተማሪዎች በሳይንሳዊ መርህ በተደራጁ መልመጃዎች መሳሪያነት በሚፈጠርላቸው የመሳተፍ እድል የሚማሯቸውን ቃላት መገንዘብና ከራሳቸው ጋር ማዋሀድ እንዲሁም በአስፈላጊው ጊዜና ቦታ ቃላቱን ከትውስታ ማህደር መገዘዘው መጠቀም ሲችሉ ነው።

በቃላት የመማር ስልቶች ላይ እስከ ዛሬ የተካሄዱ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የቃላት ማቅረቢያ ዘዴዎችን አስተዋውቀዋል። ከነዚህ የቃላት ማቅረቢያ ስልቶች መካከልም ዋና ዋና የሚባሉት ቃላትን በአውድ ማቅረብ፣ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ፣ ቃላትን የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን ተመርኩዞ ማቅረብ፣ ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ፣ ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ፣ የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ እና የቃላት ትምህርቱን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ የሚሉት ናቸው። እነዚህንም እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንመልከታቸው።

2.5.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ

አውድን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ይሰጣሉ። ከነዚህም መካከል Nation እና Coady (1988፣102) አውድ በአጠቃላይ ገፅታዎች ሊከፋፈልና ሊገለፅ የሚችል ሆኖ በአንድ በተሰጠ ውህድ አሀድ ውስጥ እንደስነምዕላዳዊ፣ ስነአገባባዊና ዲስኩራዊ መረጃ ሊታይ ይችላል በማለት ያስረዳሉ። አያይዘውም የውህድ አሀዱ አንባቢ ወይም አድማጭ ውህድ አሀዱ ስለሚናገረው ጉዳይ የራሱ የሆነ ዳራዊ እውቀት ይኖረዋል። ያም በአጠቃላይ አውድ ውስጥ እንደሚጠቃለል ይገልፃሉ። Harmer (1991፣57) ደግሞ አውድ ቋንቋ በጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ የሚያመቻች ሁኔታ እንደሆነ ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል Lewis (1993፣8) እና Ellis (1995፣7) አውድ ቃሉ በቁመ- ከሚሰጠው ትርጉም በተለየ መልኩ በሌሎች ከነኑ በሚቆመ- ቃላት አማካኝነት ትርጉመ- ተወስኖ የሚቀርብበትን ሁኔታ ይመለከታል። እንዲሁም አውዱ ንግግሩ የተነገረበትን ሁኔታ እና

ንግግሩ የፈለቀበትን ስነልሳናዊ አካባቢ ያካትታል። ስለዚህ አውድ ስንል ሁኔታዊ አውድና ስነልሳናዊ አውድ በማለት በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል በማለት ያስረዳሉ።

ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው የአንድን ቃል ፍቺ መወሰን የሚቻለው ቃሉ በቀረበበት አውድ ነው። ይህም አንድ ሰው ለፍርድ ቤትና ለሚወዳት ባለቤቱ አንድን ጉዳይ በተመሳሳይ ቋንቋ አያብራራም። በሌላ በኩል ሀሳብን በመግለፅ ሂደት ቃላት ብቻቸውን አይከሰቱም በስነልሳናዊ አውድ ታጅበው (ከሌሎች ቃላትና ሀረጋት ጋር አብረው) እንጂ። ማስተላለፍ ለተፈለገው መልዕክት የተስማሚ ቃላት ምርጫም ፍቺን በመፍጠር ውስጥ የሚመጣ ይሆናል። እዚህ ላይ ስነልሳናዊ አውድ ምርጫን በመደገፍ ወይም በመገደብ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

በአጠቃላይ እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩት አውድ (ሁኔታዊም ሆነ ስነልሳናዊ) በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያለውን ብርቱ ተፅዕኖ ነው። ይህም ፍቺን ግልፅ ለማድረግ በስነልሳናዊ አውድ ውስጥ ከየትኛው ቃል ጋር አብሮ ይሰለፋል? ምን አይነት የዲስኩር አያያዥ ስራ ላይ ይውላል? የዲስኩር አያያዡን ተከትሎ ምን አይነት ፍቺ በምን አይነት ቃል ይተላለፋል? የሚሉትን ነጥቦች ሁሉ የሚመለከት ነው።

Lowson እና Hogben (1996፣106) እንደሚገልፁት አውድ ለቃላት ትምህርት ትልቅ ድርሻ አለው። ይኸውም ቃላት ከስነልሳናዊም ሆነ ከስነልቦናዊ እይታ አንፃር ፍቺያቸው ግልፅ የሚሆነው በተገቢው አውድ ውስጥ ሲገቡ በመሆኑ ነው። በተያያዘም River (1994፣131) እንደጠቆሙት፣ አንድን ቃል በተናጥል ከማቅረብ ይልቅ ተማሪዎች በድርጊት እየተሳተፉ በሚማሩበት አውድ ውስጥ ማቅረብ ትምህርቱን አይረሴ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ጉልህ ድርሻ አለው። በመሆኑም የቃላት ትምህርት አቀራረብ ቃላት በገቡበት አውድ ውስጥ መገመት በሚያስችል መንገድ መሆን አለበት በማለት ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል Curtis እና Longo (2001፣10) በጉርምስና እድሜ ላይ ላሉ ተማሪዎች መረዳትን ማሻሻል በሚያስችል የቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ ባካሄዱት ጥናት የሚከተለውን አስፍረዋል። ‹‹ለትምህርት የሚመረጡ ቃላት በተማሪዎች የንባብ ማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ ብቻ መወሰን የለባቸውም።›› ከዚህ የምንረዳው ትምህርቱ አውዳዊ አቀራረብ ይኑረው ሲባል፣ ቃላቱ በመማሪያ መፅሀፎቹ በሚካተቱ ምንባቦች

ውስጥ ብቻ ይቅረቡ ለማለት እንዳልሆነና ከምንባቡ ውጭም ቃላት ሊቀርቡ መቻላቸውን ነው። ዋናው ነገር ተገቢ ስነልሳናዊና ሁኔታዊ አውድ ሊፈጠርላቸው ይገባል የሚለው ነው። ማለትም ሌላቸውን ‹‹ይህ ቃል ምን ማለት ነው?›› በሚል ስልት መቅረብ የለባቸውም ለማለት ነው።

ከላይ መረዳት እንደሚቻለው ለቃላት ትምህርት አቀራረብ አውድ ትልቅ ድርሻ እንዳለው እና ለቋንቋ ተማሪዎች ተገቢ የሚሆነው የማስተማሪያ ዘዴም ተማሪዎች ለትምህርት ለቀረበው ቋንቋ የሚጋለጡበትን አውድ ማመቻቸትና የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውዳቸው መገመት እንዲችሉ መገፋፋት መሆኑን ነው። እንዲሁም በመፃህፎቹ ውስጥ ከቀረቡ ምንባቦች ውጭም ቃላትን በአውድ ማቅረብ ተገቢ መሆኑን ነው።

ሌላው ከቃላት አውዳዊ አቀራረብ ጋር ተያይዞ ሚነሳው ጉዳይ ቃላቱ የሚገኙባቸው ዓረፍተነገራዊ አውዶች መጠን (ርዝማኔ) ነው። ቃላት የሚቀርቡባቸው ዓረፍተነገራዊ አውዶች ከመጠን በላይ አጥረው ወይም ረዝመው የቃላቱን ፍቺ ለመገመት የሚያስቸግሩ መሆን የለባቸውም። በመሆንም ቃላት የሚቀርቡባቸው ዓረፍተነገራዊ አውዶች ከአምስት እስከ አስር ቃላትን የያዙ ቢሆኑ የቃላትን ፍቺ መገመት እንደሚያመቹ፤ በአንፃሩ ከአምስት በታች ወይም ከአስር በላይ ቃላት የሚይዙ ከሆነ የቃላቱ መጠን እያነሰ ወይም እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለትንበያ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እየቀነሰ ይሄዳል (Nation እና Cody 1988፣105)።

2.5.2 ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ

Richards (2009፣187) እና McCarthy (1990፣39) ተማሪዎች የቃላትን ንበት መመሳሰል መሰረት አድርገው ቃላት ቢያከማቹም፣ በኋላ በትምህርት እየገፉ ሲሄዱ ቃላትን በአእምሮ ሰሌዳቸው ቀርፀው የሚያስቀምጡት በፍቺያቸው አማካኝነት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው መነሻነት ማቅረብ በቀላሉ የቃሉን ፍቺ እንዲገነዘቡ ያደረጋል፤ በማለት ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል እንደ Wilkins (1982፣124) እና Bauer (1998፣31-34) ገለፃ ደግሞ፣ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የአዳዲስ ቃላት ፅንሰ

ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነቶችን በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ይገባል። በመሆኑም Bauer (1998፣31-34) እንደገለፁት ቃላትን በተመሳስሎአቸውና በተቃርኗቸው፣ በቃላት የክታች ተክታች ግንኙነት እንዲሁም በአብሮ ተሰላፊነታቸው ለይቶ ማቅረብ ተገቢ ነው። እነዚህ የቃላት የፍቺ ዝምድናዎችም ቀጥሎ ባጭር ባጭሩ ቀርበዋል።

2.5.2.1 ቃላትን በተመሳስሎና በተቃርኖ ፍቺያቸው ማቅረብ

በቃላት መካከል በጣም የታወቀው ትስስርሽ የቃላት በፍቺ መመሳሰልና መቃረን ነው። ሁለት ቃላት በአንድ በተወሰነ አውድ ገብተው ተመሳሳይ የሆነ ፍቺን ሲያስገኙ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ሲባሉ፣ በአንፃሩ ሁለቱ ቃላት በፍቺ ተፃራሪ ሆነው ሲገኙ ተቃራኒ ቃላት ይባላሉ። Allen (1983) በቃላት መካከል ፍፁም የሆነ ተመሳስሎ የለም። ምክንያቱም ቃላት በፍቺ ተመሳስሎ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም አውድ አንዱ ቃል ሌላውን ሊተካ አይችልም።

እንዲሁም ቃላት በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት መጠነኛ ባህሪ አላቸው። ይህም ማለት የአንዱ ቃል የሰፋ ፅንሰ ሀሳብ መያዝ፣ አንዱ በገባበት ሌላው አለመግባት፣ ሰዋስዋዊ ባህሪያቸው መለያየት ወዘተ የሚሉት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፣ በማለት ያስረዳሉ። በተያያዘም Gairns እና Redman (1986፣23) እንደሚገልፁት ሁለት ቃላት ፍፁም በሆነ ተመሳሳይነት ማገልገል የሚችሉ ቢሆን ኖሮ በቋንቋው ውስጥ የሚኖራቸው ተፈላጊነት አጠያያቂ ይሆን ነበር፣ በማለት ከላይ ያለውን ሀሳብ ያጠናክሩታል።

በሌላ በኩል የቃላትን ተቃርኖ በተመለከተ ደግሞ በአንድ ቋንቋ ውስጥ በቃላት መካከል የተለያዩ የተቃርኖ አይነቶች እንዳሉ ይታወቃል። ከነዚህ መካከል Carter እና McCarthy (1988፣23-24) እና Gairns እና Redman (1986፣25-27) የገለጿቸውን የተቃርኖ አይነቶች ቀጥለን እናያለን።

1. *የደረጃ ተቃርኖ*፦ የደረጃ ተቃርኖ የሚባለው እንደ ትንሽ/ ትልቅ የመሳሰሉ ተቃራኒ ግንኙነት ያላቸውን ቃላት ይመለከታል። ይህ የተቃርኖ አይነት ደረጃ ሊወጣለት ይችላል። ለምሳሌ ያህልም በጣም ትልቅ፣ ትልቅ፣ መካከለኛ፣ ትንሽ፣ ወዘተ የሚሉ እንደግለሰቡ ግላዊ እሳቤ ደረጃ የሚሰጣቸው መጠኖችን ያካትታል።

እንዲሁም የአንድ ነገር ትንሽ መሆን ወይም ትልቅ መሆን በተናጋሪው የግል እሳቤ ላይ ይመረኮዛል።

2. *የተገላቢጦሽ ተቃርኖ፦* የተገላቢጦሽ ተቃርኖ የሚባለው ሁለት ቃላት በተገላቢጦሽ የሚታይ ተቃራኒ ግንኙነት ያላቸው ከሆነ ነው። ለምሳሌ፦ እህት/ውንድም፣ ባል/ሚስት፣ ወዘተ በሚሉት ቃላት መካከል ያለውን ተቃርኖ ለመግለፅ እህቱ ነች ለሚለው ወንድሟ ነው ወይም ሚስቱ ናት ለማለት ባሏ ነው ማለት ይቻላል።

3. *ተፃራሪ ተቃርኖ፦* ይህ ጠንከር ያለ የቃላት ተቃርኖ የሚታይበት ነው። በመሆኑም ሁለቱ ቃላት በአንድ ጊዜ ለአንድ ነገር መግለጫነት ሊገቡ አይችሉም። እርስ በርሳቸውም ትይዩ ናቸው። ለምሳሌ አንድ እንስሳ ወንድ ከሆነ በምንም ተአምር ሴት ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ወንድና ሴት፣ ጧት እና ማታ ጥንድ ተቃርኖ ያላቸው ቃላት ናቸው።

4. *አቅጣጫ ጠቀስ ተቃርኖ፦* አቅጣጫ ጠቀስ ተቃርኖ የሚባለው እንደ መምጣት/መሄድ፣ መቀመጥ/መቆም የመሳሰሉ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አቅጣጫን የመጠቆም ባህሪ የሚታይባቸውን ተቃራኒ ቃላት የሚያጠቃልል ነው።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የቃላት ፍቺ ተቃርኖዎች በነጋንቃቄ በሚነደፉ መልመጃዎች አማካኝነት ማቅረብና ተማሪዎቹ እንዲመረምሯቸው ማድረግ ቃላቱ ያሏቸው የፍቺ ግንኙነት ገደብ እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመረዳት እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

2.5.2.2 የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት

ከፍቺ አንፃር የቃላት ዝምድና የሚገለፅበት ሌላው መንገድ የቃላት ተዋረዳዊ ቁርኝት ነው። አንድ ቃል ሰፋ ያለ ፅንሰ ሀሳብ በመወከሉ የተነሳ በስሩ በርካታ ቃላት የሚኖራቸውን ፍቺ ሊያቅፍ ይችላል። ይህንንም Yule (1996፣119) የአንድ ቃል ፍቺ በሌላ ቃል ፍቺ የሚጠቃለል ሆኖ ሲገኝ የሁለቱ ቃላት ዝምድና የከታችነትና የተከታችነት የፍቺ ግንኙነትን ያመላክታል፣ በማለት ያስረዳሉ። ይህንን ሁኔታ በምሳሌ ስናየው፣ ተክል

የሚለው ቃል በስሩ ፍራፍሬ፣ የምግብ ስብሎችን፣ አበባ፣ ዛፍ የሚሉ ቃላትን ፍቺ መጠቅለል ይችላል። እነዚህ ቃላት በተራቸው በስራቸው ሌሎች ቃላትን ሊያቅፉ ይችላሉ። ተክል የሚለው ቃል ከታች ቃል ሲሆን የቀሩት (ፍራፍሬ፣ የምግብ ስብል፣ አበባና ዛፍ) እያንዳንዳቸው ተክል በሚለው ቃል ውስጥ ተከታች ናቸው። እርስ በእርሳቸው ያላቸው ግንኙነት ደግሞ የአብሮ ተከታችነት ግንኙነት ነው። ሁለቱ ቃላት አብሮ ተከታች ሊባሉ የሚችሉት አንድ ለሁለቱም የበላይ የሆነ የጋራ ከታች ቃል የሚኖራቸው ከሆነ ነው።

ስለከታች ተከታች ቃላት የፍቺ ዝምድና ሲነሳ፣ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ያለው የፍቺ ዝምድና የሚታየው በስሞች መካከል ነው። ይሁን እንጂ ልክ እንደቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትምህርት ሁሉ ፍቺን መሰረት ያደረገ የቃላት ትምህርት ተደራጅቶ ከሚቀርብባቸው ስልቶች አንዱ ነው (Carter እና MacCarthy 1988፣26-27)። ስለዚህም ከታችና ተከታች ቃላትን ባንድ ላይ እያቀረቡ ተማሪዎች የቃላቱን የፍቺ ዝምድና እስከምን ድረስ እንደሆነ እንዲፈትሹ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ከታች ቃልን ሰጥቶ ተማሪዎች በስሩ ተከታች ቃላትን ተጠቅመው ንግግር ውይም ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ የሚጠይቁ መልመጃዎችን በመቅረፅና በሌሎችም ስልቶች ሊከናወን ይችላል።

2.5.2.3 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት

McCarthy (1990፣12) እንደሚያስረዱት ውስን ከሆነው የፊሊጤች እና ከሌሎች ቃላዊ ሀረጋት አገላለፆች በተለየ በአንድ ቋንቋ ቃላት መካከል መተሳሰርን የሚፈጥር ሌላው ዝምድና የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ነው። ይህ የቃላት ዝምድና አይነት በማንኛውም ቋንቋ የቃላት ጥናት ውስጥ ቃላትን አደራጅቶ ማቅረቢያ ዋና መርህ በመሆን ያገለግላል። ምንም እንኳ ፍቺ በተለያየ ደረጃ ሊታሰብ የሚችል ቢሆንም የቃላት አብሮ ተሰላፊነት በቃላት አውዳዊ ዝምድና ላይ የሚመሰረትና ፍቺ የሚተላለፍበት መንገድ ነው።

Nattinger (1988፣69-70) የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ቃላትን ለመረዳት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሁለት ባህሪያትን እንዳወረሰ ይጠቁማሉ። አንደኛው ባህሪ የአንድ ቃል ፍቺ አዝወትሮ አብሮት ከሚሰለፍ ቃል ፍቺ ጋር በመሆን ሰፋ ያለ ፍቺ እንደሚያስገኝ ማሳየት መቻሉ ነው። ይህም አብሮ ተሰላፊ ቃላቱን በትውስታ ማህደር ለማከማቸት የሚረዳ

ከመሆኑም በላይ የአንድ ቃል የፍቺ አካባቢን ለመለየት ያግዛል። ሁለተኛው ባህሪ ደግሞ ተማሪዎች ምን አይነት ቃላት በአንድ ላይ ተሰልፈው መገኘት እንደሚችሉ እንዲለዩና አንድ ቃል ሲመጣ ከሱ ጋር አብሮ ሊሰለፍ የሚችል ቃልን እንዲጠብቁ ማስቻሉ ነው።

እንዲሁም የሽጥላ (1997፣28) ሲያስረዱ፣ በስነልሳናዊ አውድ የአንድ ቃል መከሰት ሌሎች ቃላት አብረውት ሊመጡ እንደሚችሉ እንድንገምትና እንድንጠብቅ ያደርጋል። እዚህ ላይ ግን የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ደረጃቸው ሊለያይ እንደሚችል ማስታወስ ተገቢ ነው። ለምሳሌ ‹‹ክበድ ላም›› እና ‹‹የተንጣለለ ቤት›› የሚሉትን ብንወስድ ሁለቱም አሀዶች አብሮ ተሰላፊ ቃላት ቢሆኑም አብሮ የመሰለፍ የጥንካሬ ደረጃቸው ይለያያሉ። ‹‹ክበድ ላም›› ላይ የሚታየው ጠንካራ ቁርኝት ሲሆን፣ ‹‹የተንጣለለ ቤት›› ላይ ግን ቁርኝቱ እንደ ‹‹ክበድ ላም›› አይሆንም። ምክንያቱም ለላም እርጉዝ የሚለውን ቃል መጠቀም ያልተለመደ ሲሆን፣ ቤትን ግን ቀድመውት ሊገቡ የሚችሉ እንደሰፊ፣ ትልቅ ወዘተ የሚሉ ቅፅሎችን በመጠቀም ተመሳሳይ ሃሳብን ማስተላለፍ ይቻላልና ነው። ስለዚህ በቃላት የአብሮ ተሰላፊነት ያሉትን የጥንካሬ ደረጃዎች ከግምት በማስገባት ማቅረብ ተገቢ ነው።

በሌላ በኩል ቃላት እርስ በርሳቸው አውዳዊ ግንኙነት ለመፍጠር የግድ ጎን ለጎን መሰለፍ ላያስፈልጋቸው ይችላል (እነBiber 1998፣251)። ሁለት ቃላት በመካከላቸው ጥቂት ቃላት ካስገቡ በኋላ ጥምረት ፈጥረው ሊከሰቱ ይችላሉ። ለምሳሌ ‹‹አንበሳው በልቶ አገሳ›› በሚለው አውድ አንበሳ እና አገሳ የሚሉት ቃላት አብረው የተሰለፉ ናቸው። ምክንያቱም አንበሳ ጮኸ ማለት ያልተለመደ በመሆኑ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአማርኛ ቋንቋ ከሞት ጋር መርዶ፣ ከደስታ ጋር የምስራች አብረው የሚሰለፉ ቃላት ናቸው። እንዲህ ያለውን የቃላት የአብሮ ተሰላፊነት ግንኙነት ለተማሪዎች ማቅረብ የትኛው ቃል ከየትኛው ቃል ቀድሞ ወይም ተከትሎ ይገባል? የሚለውን እንዲለዩ ከማስቻሉም በላይ በተገቢው አውድ ተገቢውን ቃል መርጠው መጠቀም እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ስለዚህ የቃላት አብሮ ተሰላፊነትን ሊያሳዩ የሚችሉ መልመጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅሞ መቅረፅ አስፈላጊ ይሆናል።

2.5.3 የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ

Ur (1996፣62) እንደሚገልፁት የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ሌላው ስልት የሳላ ጠቀሜታ እንዳላቸው የሚታመንባቸውን ቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን በመከተል ማቅረብ ነው። በቋንቋ ውስጥ በአንፃራዊ አነጋገር ጥቂት ቁጥር ያላቸውን የቃላት አፈጣጠር ሂደቶች በመከተል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላት መፍጠር ይቻላል (McCarthy 1990፣99)። ቃላት የተለያዩ አርቢ ምዕላዶችን በመጨመር ልዩ ልዩ ቅርፆች ሊይዙ ይችላሉ።

ጌታሁን (1990፣50) እንደሚገልፁት በአማርኛ ቋንቋ ቅጥያዎች ቃላትን የማርባትና የመመስረት ተግባር አላቸው። የእርባታ ሂደት የቃሉ መሰረታዊ ባህሪ ሳይለወጥ በቅጥያዎች አማካኝነት የሚደረግ የቃላት የእርባታ ሂደት ሲሆን በቅጥያ አማካኝነት ከነበሩበት የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለዋወጡበት ሂደት ደግሞ ምስረታ ይባላል። በተያያዘም ባየ (2000፣108-109) እንደሚገልፁት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ቃላትን ለማርባትና ለመመስረት የሚያስችሉ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ቅጥያዎች አሉ። እነዚህ ቅጥያዎች በሰዋስዋዊ ተግባራቸው መነሻነት የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች በመባል በሁለት ይከፈላሉ።

የእርባታ ቅጥያዎች በቃል አምድ ላይ እየተቀጠሉ ቃሉ ለመደብ፣ ለቁጥር፣ ለሙያ፣ ለእምርነት ወዘተ በመርባት የተለያየ ቅርፅና ተጨማሪ ፍቺ እንዲኖረው ያደርጋሉ። ይህንንም ‹‹ልጅ›› የሚለውን ቃል እንደምሳሌ ወስደን ብንመለከት፣ ‹‹ልጅ›› ላይ/-ኡ/ የሚል ድህረ አምድ ቅጥያ ብናክልበት ‹‹ልጁ›› ይሆናል። ይህም ‹‹ልጅ›› የሚለው ቃል ለእምርነት ያደረገውን ለውጥ ያሳያል። በፍቺ ረገድም ማንኛውም ልጅ ሳይሆን ተናጋሪውና አድማጩ የሚያውቁት ልጅ መሆኑን ግልፅ ያደርጋል።

የምስረታ ቅጥዎችም እንዲሁ በቃል አምድ ላይ በመቀጠል በቃሉ ላይ የቅርፅ ለውጥ ብቻ ሳይሆን የነበረበትን የቃል ክፍል ወይም ንኡስ የቃል ክፍል ሊለውጡ ይችላሉ። ለምሳሌ /-ነት/ የሚለው ድህረ አምድ ቅጥያ ‹‹ሰው›› በሚለው ነባር ስም ላይ ሲቀጠል ‹‹ሰውነት›› የሚለውን ቃል ያስገኛል። ነገር ግን ‹‹ሰውነት›› የሚለው ምስርት ቃል ‹‹ሰው››

እንደሚለው ነባር ስም ሳይሆን ረቂቅ ስም ነው። ስለዚህ ሂደቱ ከአንድ ቃል ሌላ አዲስ ቃል መፈጠሩን ያሳያል (ባየ 2000፣ 154-155)።

Gairns እና Redman (1986፣48) በቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደት ላይ ያተኮረ ትምህርት ተማሪዎች ቃላትን ለመረዳትም ሆነ ለማፍለቅ እንዲችሉ መሰረት እንደሚጥልላቸው ይጠቁማሉ። እንዲሁም የቃላት ትምህርቱ ከመረዳት አንፃር ሲታይ፣ ተማሪዎች የማያውቁት ቃል ሲገጥማቸው የቃሉን ስነምዕላዳዊ አወቃቀር በመመርመር የቃሉን ፍቺ መመርመር እንዲችሉ ፍንጭ ይሰጣል (Ying 2001፣19)። ለምሳሌ፣ ‹‹ኢ-ፍትሀዊ›› የሚለውን ቃል ፍቺ በመነሻ ላይ የምትገኘው /ኢ-/ የተሰኘችው ምእላድ ቃሉ አፍራሽ ወይም አሉታዊ ፍቺ እንዳለው ስትጠቁም፣ በመድረሻ ላይ የሚገኘው /-ኣዊ/ የተሰኘው መስራች ምእላድ ደግሞ ቃሉ ቅፅል መሆኑን ይጠቁማል። ተማሪዎች የዚህን ቃል ስነምዕላዳዊ አወቃቀር ከፋፍሎ በማየት ‹‹ፍትህ›› የሚለውን ቃል ባያውቁ እንኳ፣ ቢያንስ ‹‹ኢ-ፍትሀዊ›› የሚለው ቃል ቅፅል መሆኑንና በአሉታ የተነገረ መሆኑን ሊረዱ ይችላሉ። በሌሎች አውዳዊ ፍንጮች በመታገዝም የቃሉን ሙሉ ፍቺ ሊደርሱበት ይችላሉ።

2.5.4 ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ

Scriverner (1998፣75) እንደሚገልፁት የቃላት ትምህርት ትኩረት ነጠላ የሆኑ ቃላትን ብቻ ሳይሆን ረጅምና ባለብዙ ሀረጎችንም ማካተት አለበት። እንዲሁም Lewis እና Hill (1992፣98) የቃላት ትምህርት ቃላዊ ሀረጋትን በቃላት ትምህርት ውስጥ ማካተት ከቻለ ተማሪዎች በቋንቋው በሚገባ ለመግባባት እንዲችሉ ከማገዝ አንፃር ትልቅ ድርሻ አለው። ቃላዊ ሀረጎችን በቃላት ትምህርቱ ማካተትና ማቅረብ ተማሪዎች በሚያጋጥማቸው የተግባቦት አውድ አንደበተ ርቱዕ ሆነው አላማቸውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችላቸውን መሳሪያ ያስታጥቃቸዋል፣ በማለት ያስረዳሉ።

እንዲሁም Nattinger (1988፣75) እንደሚገልፁት ብዙ የቋንቋ ብቃት ትምራዎች የሚጠቀሙት ቃላት በትውስታ ማህደር የሚቀመጡት ነጠላ ሆነው ብቻ ሳይሆን የሀረግ አካል ሆነው ጭምር እንደሆነ ያብራራሉ። እነዚህ ቃላዊ ሀረጎች በቀላሉ ሊታወሱ

ከመቻላቸውም በላይ ተናጋሪው በነጠላ ቃል ላይ እንዳያተኩርና ሃሳቡን በዲስኩር መዋቅር ላይ እንዲያሳርፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

ቃላዊ ሀረጎች በአይነታቸው የተለያዩ ናቸው። Nattinger እና Decarrico (1992፣37-47) ቃላዊ ሀረጎችን መዋቅራዊና አገልግሎታዊ ባህሪያቸውን በመመርኮዝ በተለያየ መንገድ የከፈሏቸው ሲሆን፣ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አላማ ሲባል በሶስት በመክፈል ለማየት ተሞክሯል።

1. ጥምር ስሞችና ጥምር ግሶች

ጥምር ግሶችና ጥምር ስሞች ቃላትን በማጣመር የሚፈጠሩ ቃላት ናቸው። የጥመራን ምንነት ጌታሁን (1990፣68) ‹‹ጥመራ ቃላትን በማጣመር ሌላ አዲስ ቃል የመፍጠር ዘዴ ወይም ስርዓት ነው።›› በማለት ይገልፁታል። የጥምር ቃል አፈጣጠር ሲመረመር በአጣማሪ ምዕላድ አማካኝነት ወይም ተጣማሪ ቃላቱን በአንድ ላይ በማሰለፍ(ያለ አጣማሪ) ሊከናወን ይችላል። ለዚህም ‹‹ዝም አለ›› የሚለውን ጥምር ግስና ‹‹ቤት-ኧ-ሰብ›› የሚለውን ጥምር ስም መመልከት በቂ ነው።

ጥምር ስሞችና ጥምር ግሶች በተለያዩ ስልቶች ሊቀርቡ መቻላቸው ሳይዘነጋ፣ የአመሰራረት ሂደታቸውን በመከተል ማቅረብና ተማሪዎች ሂደቱን ተከትለው ጥምር ቃላትን እንዲመሰርቱ በማድረግ እንዲሁም በአውድ አቅርቦ ጥምር ቃላቱን የሚተኩ ቃላት እንዲፈልጉ በማድረግ ማቅረብ ይቻላል (Wallace 1988፣ 89-91)።

2. ፈሊጣዊ አነጋገሮች

የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ምንነት በተመለከተ የአማርኛው መዝገበ ቃላት ‹‹ሁለት ቃላት ለየብቻቸው ሆነው ሲነገሩ ከሚሰጡት ሀሳብ ውጭ ባንድ ላይ ሲጣመሩ የሚሰጡት የተለየ ሀሳብ›› በማለት ይፈተዋል (የኢትየጵያ ጥናትና ምርምር ማዕከል 1993፣585)። Lewis (1993፣98) ደግሞ የቃሉ ጠቅላላ ፍቺ ቃሉን ከመሰረቱት ተጣማሪ ቃላት የማይገኝ የተለየ የቃላዊ ሀረግ አይነት ነው፤ በማለት ይበይኑታል። እንዲሁም ዳኛቸው ወርቁ እና አምሳሉ አክሊሉ (1993፣2) ፈሊጣዊ አነጋገር በቃላት ልዩ ልዩ ዘዴ የመጠቀም አንዱ

መንገድ ሲሆን ባጠቃላይ ይዘቱ እያንዳንዱ ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በሚቀናጅበት ጊዜ ቀድሞ ከነበረው ፍቺ የተለየ ፍቺ የሚሰጥበት ሁናቴ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ፈሊጣዊ ቃላትን ለትምህርት ማቅረብን በተመለከተ አንዳንድ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ከአንድ ቃል በተመሳሳይ ሁኔታ በጥምረት የሚፈጠሩ ፈሊጦችን ባንድ ላይ ማቅረብ የተለመደ መሆኑን Wallace (1988፣118) ይገልፃሉ። አያይዘውም እንዲህ ያለው ዘዴ ፍሬቢስ እንደሆነና ለዚህም ምክንያቱ ፈሊጦቹ የሚመሳሰሉት በቅርፅ እንጂ በፍቺ ባለመሆኑ እንደሆነ ስረዳሉ።

ፈሊጦችን በአፈጣጠራቸው ላይ በማተኮር የተገነቡባቸውን ቃላት በመነጣጠል ውስጣዊ አወቃቀራቸውን ለመመርመር በሚያስችል አኳኋን ማቅረብም እንዲሁ ተገቢ እንደማይሆን McCarthy (1990፣7-8) ይጠቁማሉ። ምክንያቱንም ሲገልፁ የፈሊጣዊ ቃላት አገባባዊ ባህሪ ከጥምር ቃላት አገባባዊ ባህሪ የተለየ እንደሆነ፣ ፍቺያቸውም ከተጣማሪ ቃላቱ የተናጥል ፍቺ ሊገኝ እንደማይችል ያስረዳሉ። ስለዚህም ፈሊጦችን ለማስተማር የተሻለው ዘዴ የተለየ የፍቺ ገፅታዎችን ያገናዘበ፣ ትርጉም ያለው አውድ በመፍጠር ቅርባቸውን፣ ፍቺያቸውንና አጠቃቀማቸውን ግልፅ በማድረግ መከናወን እንደሚገባው ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ይስማሙበታል።

3. የተለመዱ አገላለፆች

Lewis (1993፣94) እንደሚያስረዱት የተለመዱ አገላለፆች የሚባሉት በመስተጋብራዊ የተግባቦት ሂደት የቋንቋ ተጠቃሚው የመስተጋብሩ ትኩረት የሚመራባቸው አያያዥ ቃላት ናቸው። ዋና አገልግሎታቸው አድማጭ ወይም አንባቢ ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው ሊገልፅ የፈለገውን በፍጥነት መለየት ማስቻል ነው። የተናጋሪው ወይም የፀሀፊው ሀሳብ የተያያዘና ፍሰቱን የጠበቀ እንዲሆንም እገዛ ያደርጋሉ። መስተጋብሩ ሲካሄድ ምን እየተደረገ እንደሆነ አንዱ ከታወቀ ደግሞ አድማጩ ወይም አንባቢው ትኩረቱን በሚባለው ነገር ላይ እንዲያሳርፍ ያደርገዋል።

በዚህ ክፍል የሚካተቱ ቃላዊ ሀረጎች እጅግ በርካታ ናቸው። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ ነገር ግን፣ በሌላ አነጋገር፣ ከዚህም ሌላ፣ ከዚህ በመነሳት፣ በዚህ ረገድ፣ እንደእውነቱ ከሆነ፣ ከሁሉ በፊት፣ ለማጠቃለል ያህል፣ ይህንን በተመለከተ፣ አስቀድሞ እንደታሰበው፣ እኔ የምለው፣ በከፍተኛ ደረጃ፣ ከዚህ ውጪ፣ ወዘተ ይገኙበታል (የሽጥላ 1997፣33)።

McCarthy (1990፣9) እነዚህ ሀረጎች ፅሁፍንም ሆነ ንግግርን ለመክፈት፣ ሀሳብን ለማጉላት፣ ምሳሌ ለመስጠት፣ ሀሳብን ለማያያዝ፣ ርዕሰ ጉዳይን ለመቀየር አገልግሎት ይሰጣሉ። ተማሪዎች እነዚህን ቃላዊ ሀረጎች መማራቸው አንደበተ ርቱዕ እንዲሆኑ ከማገዙም በላይ፣ ሀረጎቹ ስንዱ በመሆናቸው በቀላሉ ለማስታወስና ለመገልገል የተመቹ ናቸው። ሰፊ የሆነ የቃላት ትምህርት እይታ እነዚህን ጠቃሚ ቃላዊ ሀረጎች ማጠቃለል እንዳለበት ይታመናል፣ በማለት ያስረዳሉ።

የተለመዱ አገላለጾችን ለማፍለቅም ሆነ ለመረዳት በሚያስችሉ የተለያዩ መንገዶች ማቅረብ እንደሚቻል Nattinger (1988፣78) ያስረዳሉ። ከማቅረቢያ መንገዶች አንዱ በጥቂት መሰረታዊ ሀረጎች መጀመርና ትምህርቱን ቀስ በቀስ በማሳደግ ማቅረብ ሲሆን የክፍት ቦታ መሙላትና የትክ መልመጃዎችን በመንደፍ አገባባቸውን ግልፅ ማድረግ ይቻላል። ከዚህም ሌላ ተማሪዎች ሲናገሩና ሲፅፉ ቃላቱን እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ የንግግርና የፅሀፈት መልመጃዎችን መቅረፅ ይቻላል።

2.5.5 ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅርብ

ተማሪዎች የተረዷቸውን አዳዲስ ቃላት አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ መጠቀም የሚጀምሩት የቅበላ ክሂሎቻቸውን ተጠቅመው ባገኙት እውቀት ነው። የተገነዘቧቸውን ቃላት አፍልቀው መጠቀም ማለት ደግሞ በተለያዩ አውዶች ስልታዊና ፈጠራ በተሞላበት መንገድ መገልገልን ይመለከታል (Ming 1993፣11-12)። እንዲሁም Lewis (1993፣114) እንደሚገልፁት ተማሪዎች መግባባት እንዲችሉ በተገቢ ሁኔታ በቃላት ትምህርት መታገዝ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ቃላትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ የመማር ሂደቱን የተቃና ያደርገዋል። ይህም የተማሪዎች የተግባቦት አቅም መጠኑን በጠበቀ የቃላት ትምህርት ክንውን እንዲታገዝ ያደርጋል።

Joe (1995፣1-2) እና Cumino (1990፣15) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች ቃላት የመረዳት ችሎታቸውን የሚያዳብሩት አቀባይ ክሂሎችን ተጠቅመው ነው። ቃላት ከአውድ ውጭ በተናጥል ሲታዩ፣ ከመረዳት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የላቸውም። ተማሪዎች ቃላትን እንዲረዱ ከተፈለገ ቃላት ፍቺን ግልፅ ለማድረግ ከሌሎች ቃላት ጋር አብረው የሚገኙባቸውን ውህድ አሀዶች እንዲያነቡ ወይም እንዲያዳምጡ መደረግ አለበት።

Eyraud K. (2000፣2) እንደሚገልፁት፣ አብዛኛው የቃላት እውቀት የሚጨበጠው በክሂሎች (በማንበብ፣ በማዳመጥ፣ በመናገርና በመፃፍ) ነው። በተለይ ከንባብ ጋር አጣምሮ ማቅረብ ከሁሉም የበለጠ ተስማሚ እንደሆነ የቀድሙ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በመሆኑም የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ተጣምሮ መቅረብ አለበት።

Simcock (1993፣1) እና Joe (1995፣1-4) እንደሚገልፁት ቃላትን እያፈለቁ የመጠቀም እውቀትን ለመገንባት የጥያቄና መልስ ስልትን እንዲሁም ያነበቡትንና የሰሙትን እንደገና መናገር ስልትን መጠቀም አስፈላጊ ነው። በዚህ ስልት በቅድሚያ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ያለበትን አንድ ታሪክ በየግላቸው ያነባሉ ወይም ያዳምጣሉ። በመቀጠል ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን መልሰው በጥያቄና መልስ መልክ እንዲናገሩ ይደረጋል። ለጥያቄዎቹ የሚሰጡ መልሶችም አዳዲሶቹን ቃላት እንዲጠቀሙ የሚያደርጉና በትረካው የተካተቱ ነጥቦች ጭምቅ ሀሳብ እንዲሆኑ አድርጎ ጥያቄዎቹን መቅረፅ ያስፈልጋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን የያዙ ውህድ አሀዶችን ካነበቡ ወይም ካዳመጡ በኋላ እንደገና እንዲናገሩ ወይም እንዲፅፉ ለማድረግ የሚያስችሉ መልመጃዎችን በጥንቃቄ በመቅረፅና በማቅረብ የቃላት ትምህርትን ከክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ ይቻላል።

2.5.6 የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

በመዝገበ ቃላት የተደገፈ የቃላት ትምህርትን በተመለከተ Gairns እና Redman (1986፣70-71) እንደሚያስረዱት በመማር ሁኔታ ውስጥ የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ትምህርት የማንኛውም መርሀ ትምህርት ዋና አካል መሆን አለበት ይላሉ። አያይዘውም ተማሪው መምህሩን ወይም ጓደኛውን ጠይቆ መረዳት በማይችልበት ወቅት መዝገበ

ቃላትን በመጠቀም ችግሩን ሊፈታ ይችላል። በመዝገበ ቃላት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሆኑት መካከል ንበትን፣ ሰዋስውንና ፍቺን ማስተማር እንደሚቻል ይገልፃሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘም Hunt እና Belgar (2002፣6) የቃላትን ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ተማሪዎች የአንድን ቃል የተለያየ ፍቺ እንዲረዱ ያግዛቸዋል፤ የአንድን ቃል ትክክለኛ ፍቺም ከአውድ እንዲገነዘቡ ጉልህ ድርሻ አለው፤ በማለት ይገልፃሉ።

ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሶስት አይነት መዝገበ ቃላት እንዳሉ Seal (1991፣308) ይገልፃሉ። የመጀመሪያው ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት ሲሆን የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ይተረጉማል። ሁለተኛው ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት ሲሆን የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በዚያው በታላሚው ቋንቋ የሚገልፅ ነው። ሶስተኛው ደረጃውን የጠበቀ መዝገበ ቃላት ሲሆን እንደ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት ሁሉ በአንድ ቋንቋ የሚዘጋጅ ነው። ልዩነታቸው ደረጃውን በመጠበቅ ረገድ ነው። እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ መዝገበ ቃላት ሲዘጋጅ አፍፈቶችን ታሳቢ አድርጎ የሚዘጋጅ በመሆኑ ከልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት ይለያል።

ከላይ ከተዘረዘሩት መዝገበ ቃላት ለማስተማር ተስማሚ የሚሆነው የትኛው ነው ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። Morley (1990፣21) እንደሚገልፁት አንድም ለተማሪዎች በተሰጡት ተግባራትና ባላቸው የቋንቋ እውቀት ይወሰናል። በሌላ መልኩ ደግሞ ፍፁም የሚባል መዝገበ ቃላት ባለመኖሩ ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው የሚመርጡትን መዝገበ ቃላት ሊጠቀሙ ይገባል።

Scrivener (1998፣73) እንደሚገልፁትም በመዝገበ ቃላት አስደግፎ የሚቀርብ ቃላት ትምህርት አቀራረብ በአጠቃቀም ብልሀት ላይ ትኩረት አድርጎ ከቀረበ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባስፈለጋቸው ጊዜ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትን የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አንፃር ድርሻው የጎላ ነው። ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተተው የቃላት ትምህርት መዝገበ ቃላትን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ማሳየትና የአጠቃቀም ጥበቡን በማለማመድ ላይ ትኩረት ማድረግ ያለበት መሆኑን ነው።

2.5.7 የቃላት ትምህርቱን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ

የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ተቀርፀውለት ለተማሪዎች ሲቀርብ ለመለማመድ እንዲያስችላቸው ግልፅ ሆኖ በተብራራ ሁኔታ የሰፈረ መመሪያ ሊኖረው ይገባል። እነAlderson (1995፣41) እንደሚገልፁት የቋንቋ መልመጃ መመሪያዎች በተማሪዎች ዘንድ የሚጠበቀውን የአመለካከትና የአሰራር (የባህሪ) ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ቋንቋ ነክ ተግባራትና መረጃዎች ለልምምድ የሚቀርቡባቸው በመሆናቸው ተማሪዎችን የማያሻሙ ሆነው መነደፍ ይኖርባቸዋል።

እንዲሁም Wallace (1988፣73) እንደሚገልፁት ግልፅ ማብራሪያ የታከለባቸው የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ለማዘጋጀት በቃላት ትምህርት ላይ ያተኮሩ ምርምሮችን መቃኘት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ተመሳሳይ ቃላትን ለማለማመድ የተዘጋጁ መልመጃዎች ቢኖሩ የተመሳሳይ ቃላቱ ፍካሬያዊና እማሬዊ ፍቺያቸው፣ ከሚገቡበት አውድ ወይም አብረው ሊሰለፉ ከሚችሉ ሌሎች ቃላት አንፃር ሊመዘኑ ይገባል። ምክንያቱም ተመሳሳይ ቃላት አጠቃላይ በሆነ እይታ ተመሳሳይ ቢመስሉም በተግባር ሲመረመሩ ግን ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል። ስለዚህ የተመሳሳይ ቃላት ትምህርት የሚቀርብባቸው መመሪያዎች ይህንኑ መመሳሰል አንባራዊ መሆኑን የሚጠቁም ማብራሪያ ቢታከልባቸው ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን መልመጃዎች በተፈለገው መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ። ስለዚህ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ግልፅና የተብራሩ፣ አስፈላጊውን ምሳሌ የያዙ ሊሆኑ ይገባል።

2.6 የመልመጃ አቀራረብ

በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ ለታላሚ ቋንቋ እውቀት መዳበር ቃላት ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት በሚለው ክፍል ለመግለፅ ተሞክሯል። ካላቸው ሚና ከፍተኛነትም አንፃር ከሚማረው ሰው አእምሮ ተዋህደው በሚያስፈልጉበት ጊዜ ያለችግር ስራ ላይ ለማዋል የሚመቹ መሆን አለባቸው። በመሆኑም የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ሲካሄድ ከቃላት አንፃር ለተጠቀሰው ብቃት የሚያደርሱ መሆን እንዳለባቸው ይታሰባል። ለዚህ ብቃት እንዲያደርሱም የተለያዩ ለቋንቋ መማር የሚረዱ

የመማሪያ መፅሀፍ አካላት በጥንቃቄ ሊዘጋጁ ይገባል። ከነዚህ አካላት ውስጥ አንዱ መልመጃ ነው።

መልመጃ ማለት ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የቀሰሙትን ትምህርት በሚመለከት እቤታቸው ወይም ክፍል ውስጥ በመስራት የተማሩትን የሚያንፀባርቁበት ክንዋኔ ነው በማለት አንበሴ (1993) ያብራሩታል። ከቃላት ለመለመድ በተደጋጋሚ ስራ ላይ መዋል መፈለግ አንባር ሲታይ መልመጃ በቋንቋ መለመድ ውስጥ የሚኖረው ደርሻ ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል። ይህንንም Scrivener (1998፣75) ተማሪዎች ለተወሰኑ አዳዲስ ቃላት በመጋለጣቸው ብቻ ስራችን አይጠናቀቅም። እንዲለምዷቸው፣ እንዲማሯቸው፣ በትውስታ ማህደራቸው እንዲያከማቿቸውና በሚያስፈልግበት ጊዜ ሊጠቀሙባቸው እንዲችሉ ልንረዳቸው ይገባል በማለት ይገልፃሉ።

እንዲሁም Cunningsworth (1995፣59) ተማሪዎች አንድን የቃል አይነት እንዲያስታውሱት፣ ያለችግር እንዲጠቀሙበትና የፍቺው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተቻለ አቅም በተደጋጋሚ በተለያየ አውድ ውስጥ ሊያገኙት ይገባል በማለት ያብራራሉ።

በአጠቃላይ መልመጃ ሲዘጋጅ በሚከተለው መልኩ ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን ምሁራን ይመክራሉ። መልመጃዎች ከአቀራረብ አንባር ከቀላል ወደ ከባድ እያደጉ የሚሄዱ ቢሆኑ ይመረጣል። ምክንያቱም ተማሪዎች ውስብስብ ያልሆነውን በመስራት የሚጠጥርባቸውን ለመስራት እንዲበረታቱ ያስፈልጋል። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ሳይጀምሩት ልሰራው አልችልም በሚል ስሜት ሳይሞክሩት ሊቀሩ ይችላሉ። የዚህ ሁኔታ መከሰት ተማሪዎች በተለያዩ መልመጃዎች በመሳተፍ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዳያዳብሩ ሊያደርጋቸው ይችላል። ስለዚህ ተማሪዎች ይበልጥ ውስብስብ ወዳለው ክንዋኔ ከመሄዳቸው በፊት በክብደቱ ቀለል ባለ ክንዋኔ ላይ በሚያገኙት ስኬት መበረታታት አለባቸው በማለት Anderson እና Lynch (1991) ላይ ያብራራሉ።

እንዲሁም Cunningsworth (1995) መልመጃዎች ሲቀረፁ የቃላትን ፍቺያዊ ተዛምዶ፣ የቃላት አብሮነትን ለመገንዘብ እንዲረዱ አውዳዊ መሆን እንዳለባቸው ይናገራሉ። በተጨማሪም በመልመጃነት የቀረበለትን ትምህርት ክፍል ለማዳበር የታለመ መሆን

እንዳለበት ይታመናል። ከቀረበው ትምህርት ጋር ተዛማጅነት ኖሮት እሱኑ ለማዳበር የቀረበ ከሆነ የተማሪዎቹን የመስራት ፍላጎት ሊያነቃቃ ይችላል።

በሌላ በኩል አንበሴ (1993፣48) መልመጃ ተማሪዎች ሰርተው እውቀት እንዲቀስሙበት አቀራረቡ ግልፅ መሆን አለበት በማለት ያብራራሉ። አቀራረቡ ግልፅ መሆን አለበት ሲባል የሚቀርብበት ቋንቋ፣ የመልመጃው ትዕዛዝ ተማሪው ተረድቶ ሊሰራው የሚችለው መሆን ያለበት መሆኑን አመላካች ነው። የሚሰጠው ትእዛዝ ለተማሪው ሊገባ በሚችል ግልፅ ቋንቋ መቀመጥ እንዳለበት ይታመናል። የሚሰጡ ምሳሌዎችም ካሉ ተማሪው እንዲሞክር መንገድ የሚከፍቱለት መሆን አለባቸው።

2.7 የቀደሙ ጥናቶች ቅኝት

አጥኝው ባደረገው አሰሳ በቃላት ላይ ያተኮሩና ከዚህ ጥናት ጋር በአንድም በሌላም መንገድ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ተገኝተዋል። እነዚህም ጥናቶች አማርኛን ማስተማር (Teaching Amharic) ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ እና ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ናቸው። እነርሱም ትንሳኤ (1988)፣ ሲሳይ (1990)፣ አንበሴ (1993)፣ አብይ ይመር (1991)፣ የሺጥላ (1997) እና ሞላ (2003) ናቸው።

የመጀመሪያው ጥናት የትንሳኤ ነው። የትንሳኤ ጥናት ርዕሱ ‹‹የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ፈተናዎች በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት›› የሚል ሲሆን ጥናቱም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ነው። የጥናቱ ዓላማም በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ውስጥ የቀረቡ የቃላት ጥያቄዎች ተገቢነት ያላቸው መሆንና አለመሆናቸውን መመርመር ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም ጥያቄዎቹ በአውድ ያልቀረቡ፣ ግልፅ አላማ የሌላቸው፣ አቀራረባቸው አውድን ያልተከተለ፣ አቀራረባቸው የትምህርቱን ዓላማና የማስተማር ዘዴ መሰረት ያላደረጉ መሆናቸው ተረጋግጧል።

ሁለተኛው የሲሳይ ሲሆን ጥናቱን ያካሄዱትም ‹‹በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ነው። የጥናቱ ዓላማም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረቡን

መገምገም ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ከቃላት ትምህርት አጠቃቀም ይልቅ በፍቻቸው ላይ የተመሰረተ መሆኑን፣ አውዳዊ አቀራረብ የሚከተልና የቃላት ትምህርቱ አቀራረብ በአብዛኛው ከአንብቦ መረዳት ጋር የተያያዘ መሆኑን ተመልክቷል።

ሶስተኛው የአብይ ጥናት ሲሆን እርሳቸውም ‹‹የአማራው ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት ያዙታ ግምገማ›› በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያ ጥናት አቅርበዋል። የጥናቱ አላማም የመማሪያ መፃህፍቱን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ይዙታ መመርመርና ትምህርቱን በተሻለ መልክ ለማቅረብ ይረዳሉ ተብለው የሚገመቱ የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆም ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቃላት አቀራረቡ ጉድለት ያለበትና ከይዘት አመራረጥና አደረጃጀት አንፃርም ድክመት የሚታይበት እንደሆነ ተደርሶበታል።

አራተኛው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው አንበሴ በቀለ (1993) ‹‹በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀ የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት ያቀረቡት ጥናት ነው። የጥናቱ ዓላማም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ1990ዓ.ም በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አመራረጥና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በተተኳሪው መፅሀፍ ቃላት በተገቢው መንገድ አለመመረጣቸው እና አለመደራጀታቸው እንዲሁም አዳዲስ ቃላት በተደጋጋሚ አለመቅረባቸው ተረጋግጧል።

አምስተኛው ደግሞ የሺጥላ ‹‹የ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቃላት ትምህርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ግምገማ›› በሚል ርዕስ ለ2ኛ ዲግሪ ማሚያ ያቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ነው።

የጥናቱ ዓላማም በ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥን፣ አደረጃጀትንና አቀራረብን መገምገም ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም የመማሪያ መፃህፍቱ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ የመስኩ ምሁራን ለዚህ ተግባር

እንዲውሉ ከሚሰነዘሯቸው ነጥቦች አንፃር ብዙ ድክመት እንዳለባቸው በጥናቱ ተደርሶበታል።

ለዚህ ጥናት የመጨረሻውና ስድስተኛው ሞላ ‹‹በትግራይ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና›› በሚል ርዕስ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ነው።

የጥናቱ ዓላማም በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው። በጥናቱ የተገኘው ውጤትም መማሪያ መፅሀፉ ለቃላት ትምህርት ተገቢ ትኩረት የሰጠ፣ በተቻለ መጠን ቃላትን በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሞ ለማስተማር የሞከረ፣ ይዘቶቹ ተከታታይና ተዋረዳዊ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ መሆናቸውን መረዳት የተቻለ ቢሆንም ይዘቶቹ የቴክኒክ ችግሮች ያሉባቸው መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

እነዚህ ከላይ ባጭር ባጭሩ የተገለፁት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያለያያቸውም የሚያማሳስላቸውም ነጥብ አለ። የሚያመሳስላቸው ሁሉም በቃላት ትምህርት ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ መሆናቸውና ከአንዱ በስተቀር (ክትንሳኤ) ሁሉም በመማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት ይዞታ ላይ ያተኮሩ መሆናቸው የሚያመሳስላቸው ነጥብ ነው።

ነገር ግን የሚያመሳስላቸው ነጥብ እንዳለ ሁሉ የሚያለያዩዋቸውም ነጥቦች አሉ። ይህም ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች በአብዛኛው ትኩረት አድርገው የተሰሩት አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ (ለትግራይና ለኦሮሚያ) ተማሪዎች በተዘጋጁ መፅሀፎች እና በማዕከላዊ ደረጃ ለ9ኛ እና ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁት ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ትኩረት የሚያደርገው አማርኛን በአፍፈትነት በሚማሩ ለአማራ ክልል ተማሪዎች በተዘጋጁት መፃህፍት ላይ ነው። እንዲሁም ጥናቶቹ በተለያዩ ጊዜያት መደረጋቸውም የጊዜ ልዩነት እንዳለ ያሳያል።

ሌላው ከአብይ ጥናት ጋርም ቢሆን በቃላት ላይ ማተኮሩ እና በተመሳሳይ የክፍል ደረጃና በተመሳሳይ ቦታ መሆኑ የሚያመሳስላቸው ቢሆንም አብይ የሰራባቸው መፅሀፎች

በ1987ዓ.ም የተዘጋጁት ሲሆኑ ይህ ጥናት ግን የሚያተኩረው በ1997ዓ.ም ተሻሽለው በተዘጋጁት መፅሀፎች ላይ መሆኑ የሚያለያያቸው ጉዳይ ነው። ሌላው የሚያለያያቸው ጉዳይም ጊዜና የትኩረት አቅጣጫ ነው። በአጠቃላይ ይህ ጥናት ከላይ ከተዘረዘሩት ጥናቶች ጋር በአላማ፣ በጊዜ እና በትኩረት አቅጣጫ እንደሚለይ መረዳት ይቻላል።

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ እና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት መሰረት ያደረገው ዓይነታዊ (Qualitative Research) የምርምር ዘዴን ነው። በመሆኑም በመማሪያ መፅሀፎቹ በቀረቡ የቃላት ትምህርቶች ላይ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ የይዘት ትንተና (Content Analysis) ተካሂዷል። ከይዘት ትንተናና ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችም በገላጭ (Discribtive) አግባብ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል።

3.2 የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፡-

- የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፎች፤
- የመማሪያ መፃህፎቹ አዘጋጆች ናቸው።

3.3 የናሙናዎች አመራረጥ

3.3.1 የመፅሀፎቹ አመራረጥ

አሁን ባለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የአንደኛ ደረጃ የመማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ነው። በክልሎች ከሚዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት መካከል በ1997ዓ.ም የተዘጋጁት የአማራ ክልል የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተጠቃሾች ናቸው። ምንም እንኳን የቃላት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ የተወሰኑ ጥናቶች የተካሄዱ ቢሆንም በአማራ ክልል የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን በተመለከተ የተሰሩ ስራዎች አጥኝው ባደረገው ዳሰሳ ባለማግኘቱ ተተኳሪ መፃህፍት ተደርገው ተመርጠዋል። በተጨማሪም በአነሳሽ ምክንያት ላይ እንደተገለፀው አጥኝው መፅሀፎቹን በቅርበት የማየት እድል ስለገጠመውና በዚያ ወቅትም የቃላት ትምህርት አቀራረባቸው ጥያቄ ስላስነሳበት ነው።

3.3.2 የመማሪያ መፃህፎቹ አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ

የመማሪያ መፃህፎቹ አዘጋጆች የተመረጡበት ምክንያት አዘጋጆቹ መፃህፎቹን ባዘጋጁበት ወቅት ለቃላት ትምህርቱ ይዘት አመራረጥና አቀራረብ የተከተሉት ሞዴል እንዳለ ወይም እንደሌለ ትክክለኛውን መረጃ ይሰጣሉ ብሎ በማሰብ ነው። በአጠቃላይ የትኛውን የቋንቋ ንድፈ ሀሳብ (Theory) በመከተል እንዳዘጋጁት ለማወቅ በማሰብ ነው። በዚህም አጥኝው አዘጋጆቹ ቁጥራቸው አናሳ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት በስራ ላይ ከሚገኙት በጠቅላይ ናሙና ከአዘጋጆቹ መረጃ ሰብስቧል።

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህንን ጥናት ለማካሄድና ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተመረጡት የይዘት ትንተና እና ቃለመጠይቅ ናቸው። በዚሁ መሰረት የመማሪያ መፃህፎቹ የቃላት ትምህርት ይዘት ተተንትኗል፤ እንዲሁም ለመማሪያ መፃህፍቱ አዘጋጆች ቃለመጠይቅ በማቅረብ የሚፈለገው መረጃ ተገኝቷል።

3.4.1 የይዘት ትንተና (Content analysis)

የይዘት ትንተናን እንደ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ተደርጎ በዚህ ጥናት ውስጥ ተወስዷል። ስለዚህ በቅድሚያ እስኪ ስለ ይዘት ትንተና ምንነት የተወሰነ እንበል። የይዘት ትንተናን በተመለከተ Rebert (1985) የይዘት ትንተና የተለያዩ ጭብጦችን የያዙ ሰነዳዊ መልእክቶች፣ ሀሳቦች፣ ስሜቶች እና አስተያየቶች የሚተነተኑባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች የሚያቅፍ አጠቃላይ ስያሜ ነው። እንዲህ ያለ ትንተና በአብዛኛው የተወሰኑ ቃላት፣ ሀረጋት፣ ግብ መቺ ሀሳብ መግለጫዎችና የመሳሰሉት በሰነዱ ውስጥ ስንት ጊዜ እየተደጋገሙ እንደሚመጡ ለማወቅ የሚያስችሉትን ላቅ ያሉ ስሌታዊ ዘዴዎችን ሁሉ ይይዛል፤ በማለት ያብራሩታል። በሌላ በኩል Koul (1993) እንደሚገልፁት ደግሞ የይዘት ትንተና የመልዕክቱን ወይም የሰነዱን ይዘት በአይነት በአይነት በመመደብ፣ በማስላትና በማነፃፀር ላይ ስለሚያተኩር አንዳንድ ጊዜ ሰነዳዊ፣ መረጃዊና ድርጊታዊ እየተባለ ይጠቀሳል። የመልዕክት ልውውጡ አፊሴላዊ መግለጫዎችን ማለትም የህዝብ ቆጠራ፣ የወንጀል ትምህርት ቤት፣ ልደት ወዘተ ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል፤ በማለት ያብራራሉ። Koul አያይዘውም ከአጠቃላይ ጉዳዮች አልፈን ወደ ትምህርታዊ ምርምር ስንመጣ፤

የመርሀ ትምህርት ትንተና፣ የማስተማሪያ መሳህፍት የይዘት ቅንብርና ገፅታ ትንተና፣ የትምህርት እቅድ፣ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች፣ ተቋማትና ኮሌጆች አቋምና የወደፊት እቅድ ሁሉ በዚህ ተመርምሮ ግንዛቤ ሊገኝበት ይችላል፤ በማለት ያብራሩታል። እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ይህ ጥናትም ዋና ትኩረቱ መማርያ መሳህፍትን መገምገም ስለሆነ፣ በይዘት ትንተና ስልት በመማሪያ መሳህፍቱ የተካተቱ የቃላት ትምህርቶች ተመርምረዋል። በዚህም በመማሪያ መሳህፎቹ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች እንዴት እንደተመረጡ፣ የቃላት ትምህርቶቹ በመፅሀፎቹ ውስጥ እንዴት እንደተደራጁ፣ እንዴት እንደቀረቡ እና ሌሎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ትንተናው ተካሂዷል።

3.4.2 ቃለመጠይቅ

በዚህ ጥናት ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ተደርጎ የተወሰደው ቃለ መጠይቅ ነው። ቃለመጠይቅ በቃል የሚቀርብ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። ይህም ጠያቂው ወይም ተመራማሪው ጥያቄዎቹን ለመላሹ ያቀርባል፤ ያብራራል፤ መላሹ ጋር ፊት ለፊት ሆኖ የተቻለውን ያህል መረጃ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል። መላሹ ደግሞ ለተጠየቀው ነገር መልሱን በቃል የሚሰጥበት ዘዴ ነው። ይህንንም ያለው (1998፣181) ቃለመጠይቅ በቃል የሚቀርብ መጠይቅ ነው። ከፅሁፍ መጠይቅ የሚለየው በመላሹና ቃለመጠይቁን በሚያካሂደው ሰው መካከል የፊት ለፊት የቃላት ምልልስ በመኖሩ ነው። ጠያቂው ጥያቄዎቹን ለመላሹ ያቀርባል፤ መላሹ ደግሞ ለተጠየቀው ነገር መልሱን በቃል ይሰጣል፤ በማለት ያብራሩታል። በሌላ በኩል Cohen (1994፣271) የምርምር ቃለመጠይቅ በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ተራክቦ ሲሆን በተጠያቂው ፈቃደኝነት ለአንድ ለተወሰነ አላማ ማለትም ለምርምሩ ርቱዕ የሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት፣ ማብራራት፣ መግለፅ እና በቀጥታ በሰዎች የቃል ግንኙነት መረጃ የመሰብሰብ ሂደት ነው፤ በማለት ይገልፁታል። እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ቃለመጠይቅ ርቱእ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጠቀሜታው የጎላ ነው። በዚህ ጥናትም በክልሉ ትምህርት ቢሮ መማሪያ መሳህፎቹን እንዲያዘጋጁ ለተደረጉት ሰዎች የቃለ መጠይቅ ቀርቦ መረጃ ተሰብስቧል። ቃለመጠይቁ ያስፈለገበት ምክንያትም አዘጋጆቹ መፅሀፎቹን ባዘጋጁበት ወቅት የቃላት

ትምህርት ይዘቶቹን ለመምረጥ፣ ለማደራጀትና ለማቅረብ የተጠቀሙባቸውን መስፈርቶች ለመለየት ነው።

3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴዎች

በዚህ ጥናት ከሰነድ ምርመራ እና ከመማሪያ መፅሀፎቹ አዘጋጆች በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል። ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች በአስረጅነት እየተወሰዱ የተተነተኑ ሲሆን፣ የቃላት ትምህርት ክንውኖች ቆጠራም ተካሂዷል። ቆጠራው የተካሄደው የቃላት ትምህርቶቹን አደረጃጀትና አቀራረብ ለማወቅ ነው። ይህም የቃላት ትምህርቶቹን አደረጃጀት ለማወቅ ከርዕስ አንባር፣ ከቅርፅ አንባር ወዘተ. ምን ያህል ክንውኖች እንደተደራጁ ለማወቅ ቆጠራ የተደረገ ሲሆን፣ አቀራረባቸውንም በአውድ የቀረቡና ያልቀረቡትን፣ ከክሊሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት ወዘተ. ለመለየት ቆጠራ ተካሂዶ በሰንጠረዥ መልክ በመቶኛ ተሰልተው ቀርበዋል። ከአዘጋጆቹ በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎችም ከሰነድ ምርመራ ከተገኙ መረጃዎች ጋር እየተጣቀሱ ተብራርተዋል።

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

4.1 የተተኳሪ መፃህፍቱ አጭር ቅኝት

የ7ኛ ክፍል መፅሀፍ በመጀመሪያ በ1989 ዓ.ም የታተመውና በ1997 ዓ.ም እንደገና ተሻሽሎ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ተዘጋጅቷል። ይህ መፅሀፍ 132 ገፆች ያሉት ሲሆን፣ በተለያዩ ቋንቋ ነክ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ 12 ምዕራፎችን አካትቷል። በመፅሀፉ ውስጥ በጠቅላላው 108 ክንውኖች ቀርበዋል። ከነዚህ የቋንቋ ክንውኖች ውስጥ 25 (23.14%) ያህሉ ቃላትን የሚመለከቱ ክንውኖች ናቸው። ይህም በመፅሀፉ በቀረቡ ክንውኖች ውስጥ ለቃላት ትምህርት የተሰጠውን ትኩረት ሊያሳየን ይችላል።

የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍም እንዲሁ መጀመሪያ የታተመው በ1990 ዓ.ም ሲሆን፣ በድጋሜ ተሻሽሎ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በጎንደር መምህራን ትምርት ኮሌጅ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ተዘጋጅቶ በ1997 ዓ.ም በአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ታትሟል። መፅሀፉ 108 ገፆች አሉት። በውስጡም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ምንባቦችን በውስጣቸው የያዙ 18 ምዕራፎችን ይዟል። በመፅሀፉ መጨረሻ ገፅ ላይም የተለያዩ ቃላትን ፍቺ በመዳዬ ቃል መልክ አቅርቧል። በመፅሀፉ ውስጥ በጠቅላላው 159 ክንውኖች ቀርበዋል። ከነዚህም መካከል 43 (27.04%) ያህሉ ቃላትን የተመለከቱ ክንውኖች ናቸው። ይህም በመጽሀፉ በቀረቡ ክንውኖች ውስጥ ለቃላት ትምህርት የተሰጠውን ትኩረት ሊያሳየን ይችላል።

ሁለቱም መፅሀፎች የሚጀምሩት በቃላት ትምህርት ነው። በዚህም በመፃህፍቱ ውስጥ በገፅ 1 ላይ የቃላት ትምህርትን ይዘት የቃላት አመሰራረት በሚል ርዕስ ውስጥ አካተው ይገኛሉ። የቃላት ትምህርታቸውም የሚጀምረው የቃላት አመሰራረት ከሚል ነው። ይህም በምዕራፍ ሁለት ቁጥር 2.2 እንደተገለፀው ቃላት እለት በእለት በሚደረገው አጠቃላይ መስተጋብር ማለትም ሀሳብ መለዋወጥን፣ መልዕክት ማስተላለፍን፣ ጥያቄ ማቅረብንና የመሳሰሉትን ነገሮች ለማሳካት የምንጠቀምባቸው ሁለገብ የቋንቋ መሰረታዊ ጉዳዮች

መሆናቸውና በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብና በመፃፍ ለመግባባት ቃላት ቁልፍ ሚና ያላቸው መሆኑ መፅሀፎቹ በቃላት ትምህርት መጀመራቸው በዚህ ረገድ ያላቸውን ጥንካሬ ያሳያል። ምክንያቱም ቃላትን በሚገባ ካወቁ ነው ሌሎቹን መስራት የሚችሉትና ነው። በተረፈ በመፃህፍቱ ያሉትን ክንውኖች አቀራረብ ያየን እንደሆነ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ 108ቱ ክንውኖች በ54 መልመጃዎች ስር ተካተው ቀርበዋል። በመፅሀፉ ውስጥ መልመጃዎች የቀረቡት መልመጃ አንድ፣ መልመጃ ሁለት፣ ወዘተ በማለት ሲሆን በነዚህ ውስጥም የቋንቋ ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን የሚመለከቱ ክንውኖች በዝርዝር ቀርበዋል። የቃላት ጥያቄዎችም ራሳቸውን ችለው እንዲሁም ከክሂሎችና ከስነልሳን ጥያቄዎች ጋር ተጣምረው ቀርበዋል።

የ8ኛ ክፍልን መፅሀፍ ክንውኖችም የተመለከትን እንደሆነ ክንውኖቹ በ48 መልመጃዎች ስር ተካተው ቀርበዋል። በመፅሀፉ ውስጥ የመልመጃዎች አቀራረብም እያንዳንዱ መልመጃ በተለያዩ ክፍሎች የተከፋፈለ ሆኖ ነው። ማለትም ክፍል አንድ አንብቦ መረዳት፣ ክፍል ሁለት መፃፍ፣ ክፍል ሶስት መናገርና ማዳመጥ እንዲሁም አንዳንድ መልመጃዎች ላይ የስነልሳንና የስነፅሁፍ ዘርፎችንም በክፍል በክፍል ተካተው እናገኛቸዋለን። የቃላት ክንውኖችም ራሳቸውን ችለው እንዲሁም ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረው ቀርበዋል።

4.2 የመማሪያ መፃህፎቹ አዘጋጆች ዳራ

በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተዘጋጁት በጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራን ነው። በቃለመጠይቁ በጥያቄ ተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት የግል ሁኔታን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ለአዘጋጆቹ ቀርበዋል። በዚህም እነርሱ መፅሀፎቹን እንዲያዘጋጁ እንዴትና በምን መስፈርት እንደተመረጡ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በወቅቱ የጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በክልሉ ብቸኛ ኮሌጅ እንደነበር እና በዚህም የተሻለ ልምድ አላቸው ተብለው እነርሱ እንደተመረጡ ሁለቱም የመጠይቁ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። መፅሀፎቹን ያዘጋጁት በወቅቱ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ሁሉም መምህራን ናቸው። በወቅቱ ቁጥራቸው አራት እንደነበሩና ሁሉም በስራው እንደተሳተፉ ከቃለመጠይቁ መረዳት ተችሏል። ከመፅሀፎቹ አዘጋጆች መምህራን ውስጥ አሁን በስራ

ላይ ያሉት ሶስቱ ሲሆኑ ቃለመጠይቅ አድራጊው እዚያ በነበረበት ወቅት ሁለቱን በአካል አግኝቶ ጥያቄውን ማቅረብ ችሏል። አንዱ አዘጋጅ ግን በሰአቱ ለግል ስራ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እንደሄዱ ተነግሮታል። ነገር ግን አጥኝው ሁለቱ በቂ ናቸው ብሎ በማመኑ ሁለቱን ጠይቆ ተመልሷል።

የመማሪያ መፅሀፎቹ አዘጋጆች ስለራሳቸው የትምህርት ዝግጅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽም በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ፣ አማርኛን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪያቸውን የሰሩ እና በመምህርነት ለረጅም ዘመናት ያገለገሉ መሆናቸውን ተናግረዋል። አዘጋጆቹ ከታች ክፍል ጀምረው በመምህርነት የሰሩ ናቸው። በኮሌጅ ደረጃ ሲያስተምሩ ግን የሚያስተምሯቸው የኮሌጅ ሰልጣኞች ዲፕሎማ መሆናቸውና ወጥተው የሚያስተምሩት በአብዛኛው ከ5-8ኛ ክፍል መሆኑ፤ እንዲሁም ከነዚሁ ተማሪዎቻቸው ጋር በቅርበት መስራታቸው ለስራቸው እገዛ እንዳደረገላቸው ገልፀዋል። አዘጋጆቹ በህይወት ያሉት አሁንም በኮሌጁ በመምህርነት ሙያ እያገለገሉ ይገኛሉ።

አዘጋጆቹ ተተኳሪ መፃህፍቱን ከማዘጋጀታቸው በፊት በተለያዩ የመማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ውስጥ በየግላቸው እንደተሳተፉ ገልፀዋል። ይህም በስርዓተ ትምህርት ገምጋሚነት፣ በመርሀ ትምህርት አዘጋጅነት፣ የአዲስ አበባን ከ1-4 መርሀ ትምህርት፣ የድሬዳዋን፣ የትግራይን እና ሌሎችንም በብዛት ማዘጋጀታቸውን ገልፀዋል።

በአጠቃላይ የተተኳሪ መፅሀፎቹ አዘጋጆች ዳራ እንደሚያመለክተው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ፣ አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው እንዲሁም በመምህርነት ሙያ ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ፣ በትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ብዙ ጊዜ ተሳትፎ ያላቸው በመሆኑ አዘጋጆቹ ለስራው ብቃት ያላቸው መሆኑን ያመላክታል።

4.3 የቃላት ትምህርቶችን ይዘት አመራረጥ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በጥናቱ ውስጥ በምዕራፍ ሁለት ቁጥር 2.3 እንደተገለፀው ቋንቋን ለጠቅላላ ዓላማ ለማስተማር ታስቦ ለሚነደፍ መርሀግብር እንዲያገለግሉ በሚሰናዱ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ የቃላት ትምህርቶች መረጣ መርሀ ትምህርቱን በመመርኮዝ፣ የትምህርትና የቋንቋ ሳይንስን መሰረት ባደረጉና በጥናትና ምርምር በተደገፉ መስፈርቶች አማካኝነት መከናወን እንደሚገባው ይታመናል። በዚህም የመስኩ ምሁራን

ለቃላት መረጣ ተግባር እንዲያገለግሉ ከሰነዘራቸው መስፈርቶች መካከል የቃላቱ የድግግሞሽ መጠን፣ የስርጭት ሽፋን፣ የፍቺ ሽፋን፣ ተስተማሪነት፣ በቅርብ መገኘትና የተማሪዎች ፍላጎት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መፃህፍቱ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች የተመረጡበትን መስፈርት ለመለየትና ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ለመፃህፍቱ አዘጋጆች ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።

አዘጋጆቹ ለመማሪያ መፃህፍቱ ዝግጅት መሰረት ያደረጓቸው ሰነዶች ምን ምን እንደነበሩ ተጠይቀው መልስ ሰጥተዋል። በነገራችን ላይ ሁለቱንም መፃህፍት ማለትም የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መፅሀፎችን ያዘጋጁት ተመሳሳይ ሰዎች የሳንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራን በመሆናቸው ስለሁለቱም መፃህፍት ዝግጅት የሰጡት መልስ በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። እናም ከላይ ለቀረበው ጥያቄ አዘጋጆቹ ምላሻቸውን ሲሰጡ፣ ቃላትን መርጦ ለትምህርትነት ለማቅረብ በዋነኛነት እንደመነሻ የተጠቀሙባቸው ሰነዶች፤ ለደረጃው የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት፣ ያስተማሩባቸው ሰነዶች በተለይም የትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት (Material preparation) የሚል ኮርስ ያስተማሩበትና ተማሪዎችንም ከትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት ጋር በተያያዘ የተለያዩ ክንውኖችን ያሰሩ ስለነበር ያንን እንደምንጭ እንደተጠቀሙ ገልፀዋል። ሌላው ክልሉ የመረጣቸው የትኩረት አቅጣጫዎችም እንደነበሩና እነርሱንም መሰርት አድርገው እንደመረጡ ገልፀዋል። በተጨማሪም ቀደም ሲል በደርግ ጊዜ ያገለግሉ ከነበሩ የመማሪያ መፃህፍት ውስጥም አስፈላጊ መረጃዎችን እንደወሰዱ አዘጋጆቹ ተናግረዋል።

በተጨማሪም የህብረተሰቡን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትና ፍላጎት የሚመለከቱ ታሪካዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ከልቦለድና ሌሎች መፃህፍት፣ መፅሄቶች፣ በሌላ ቋንቋ የተሰሩ ስራዎችን ወደ አማርኛ በመተርጎም፣ ከጋዜጦች ወዘተ እንደተጠቀሙ ባለመ.ያዎቹ ገልፀዋል። የተለያዩ ፅሁፎችን እንዳሉ በመውሰድ ወይም ለደራጃው በሚመጥን መልኩ በማሻሻል፣ ለምሳሌ፦ አላስፈላጊ (ሀራም) ቃላትን በማስወጣት፣ በራሳቸው የማመዛዘን ችሎታ ተጠቅመው ለተማሪዎች ይከብዳሉ የሚሏቸውን ቃላት በመጣኝ ቃላት በመተካት እና ሌሎች ማሻሻዎችን በማድረግ እንደተጠቀሙ አስረድተዋል። በመሆኑም አዘጋጆቹ ለቃላት ትምህርቶች መረጣ በዋናነት በአገር አቀፍ ደረጃ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት፣ አጠቃላይ የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ መሰረት

አድርገው በወጡ የተለያዩ መመሪያዎችና የክልሉ መንግስት ባስቀመጣቸው የትኩረት አቅጣጫዎች በመመርኮዝ በተለያዩ የታተሙና ያልታተሙ ፅሁፎች ላይ በመመስረት የቃላት ትምህርት ይዘት መረጣ እንዳካሄዱ መረዳት ይቻላል።

የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥን የተመለከተውና ለባለሙያዎቹ የቀረበው ሌላው ጥያቄ በመፃህፍቱ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች የተመረጡበት መስፈርት ምን ነበር? የሚል ነው።

ለዚህ ጥያቄ አዘጋጆቹ በሰጡት ምላሽ የቃላት ትምህርቱን ለመምረጥ የተጠቀሙበትን መስፈርት አንድ ሁለት ብለው ሊዘረዝሩ እንደማይችሉና ብዙ መስፈርቶችንም እንዳልተጠቀሙ ገልፀዋል። ነገር ግን የ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍን ሲያዘጋጁ አንድ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ምን ያህል የማያውቃቸው ቃላትን ሊያውቅ ይገባል? የሚለውን በራሳቸው ከግምት ውስጥ በማስገባት ቃላቱን ከተመረጡ ምንባቦች እንዳወጧቸው አስረድተዋል። ከምንባቦቹ ውጭ የተመረጡ የቃላት ትምህርቶችንም አስፈላጊነታቸውንና ደረጃውን መመጠናቸውን በራሳቸው የማመዛዘን አቅም ተጠቅመው በማረጋገጥ እንደመረጧቸው በዝርዝር ገልፀዋል።

የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍን ሲያዘጋጁም የቃላት ትምህርቱን ለማዘጋጀት የተጠቀሙት እንደ 7ኛው ክፍል ሁሉ የ8ኛ ክፍልንም አንድ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ምን ያህል የማያውቃቸው ቃላትን ሊያውቅ ይገባል? የሚለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ (በመልመጃዎች ስር) ተካተው የሚገኙት ቃላት አብዛኞቹ የተመረጡት ከምንባቦች እንደሆነ፣ አመራረጣቸውም በአዘጋጆቹ አስተሳሰብ 8ኛ ክፍል ለደረሱ ተማሪዎች ይጠቅራሉ ብለው ያመኑባቸውን እንደሆነ አስረድተዋል። ተማሪዎቹ ቃላቱን የበለጠ ሊለማመዱባቸውና ሊያውቋቸው ይገባል፤ ፍቺያቸውን እያዋዙ በውስጣቸው ሊያስቀሩዋቸው ይገባል የሚሉትንና የምንባቡን ፍቺ ለመረዳት እነሱን ማወቅ የግድ የሚሉ ቃላትን እንደመረጡ ገልፀዋል። በመፅሀፉ ውስጥ ካሉ ምንባቦች ውጭ የተመረጡ የቃላት ትምህርቶችም አዘጋጆቹ ራሳቸው ለተማሪዎች ያላቸውን ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት እንደመረጧቸው አስረድተዋል።

በመፃህፍቱ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች የተመረጡበትን መስፈርት አስመልክቶ ከዚህ በላይ በአዘጋጆቹ የተሰጡት ምላሾች ተጠቃለው ሲታዩ አብዛኞቹ የቃላት ትምህርቶች የተመረጡት ለደረጃው እንዲሆኑ ከመረጧቸው ምንባቦች ውስጥ መሆኑን፣ የቃላት ትምህርት መረጣው የተከናወነው በልምድና በትምህርት ያካበቱትን እውቀት በመመርኮዝ፣ በግል የማመዛዘን ችሎታቸውን በመጠቀም እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ይህ አሰራር በክለሳ ድርሳናት ውስጥ እንደተጠቆመው Wallace (1988፣16) የሚጠቅሱትን ቃላቱ ተዘወታሪ ባይሆኑም እንኳ በተወሰኑ የመማር ሁኔታዎች ውስጥ ጠቀሜታ ያላቸው ሆነው ሲገኙ በይዘትነት የሚካተቱበትንና የግል የማመዛዘን አቅምን በመጠቀምም ቢሆን የቃላቱን ተስተማሪነት ደረጃ የመገመት አዝማሚያ የሚታይበት ነው። የቀሩት የቃላቱን ተዘወታሪነት በድግግሞሽ ጥናት የመለየት፣ የቃላቱን የፍቺ ሽፋን የማወቅ፣ የስርጭት ባህሪያቸውን የመለየትና የተማሪዎችን ፍላጎት አሰሳ የማካሄድና በነዚህ ላይ ተመስርቶም ቃላቱን መምረጥ ጉዳይ ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠው ጠቋሚ ነው።

በሌላ በኩል ለትምህርት የሚመረጡ ቃላት በተማሪዎች የንባብ ማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ ብቻ መወሰን እንደሌለባቸው ከምንባብ ውጭም ተገቢው ስነልሳናዊና ሁኔታዊ አውድ ተመቻችቶላቸው ሊመረጡ እንደሚገባ Curtis እና Longo (2001፣10) ያሳስባሉ። ከዚህ ነጥብ አንፃር ለአዘጋጆቹ የቀረበው ጥያቄ በመፃህፍቱ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች የወጡት ከምንባቦች ውስጥ ብቻ ነው ወይስ ከምንባቦቹ ውጭም የገቡ ቃላት አሉ? የሚል ነበር። አዘጋጆቹ በሰጡት ምላሽም በሁለቱም መጻህፍት አብዛኞቹ የቃላት ትምህርቶች ከምንባቦቹ የወጡ ቢሆንም ከምንባቦቹ ውጭም ቢሆን በራሳቸው የግንዛቤ አቅም ተማሪዎች እንዲያውቋቸው አስፈላጊ ናቸው ያሏቸው ቃላት መካተታቸውን ገልፀዋል።

እንዲሁም የቃላት ትምህርቱ በመፅሀፎቹ ውስጥ ከተካተቱ ምንባቦች ብቻ የወጡ ወይም ከምንባቦቹ ውጭም የገቡ መኖራቸውን በተመለከተ በመፅሀፎቹ ይዘት በተደረገው ፍተሻ ሁለቱም መፅሀፎች በርከት ያሉ ከምንባቦች ውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን ቢይዙም ነገር ግን መፅሀፎች የሚጀምሩት የቃላት አመሰራረት በሚል ርዕስ ነው። በዚህም ከምንባብ ውጭም ቃላትን እንደትምህርትነት በተለይም አመሰራረታቸውን በተመለከተ በመፅሀፎቹ ውስጥ መካተታቸውን መገንዘብ ይቻላል። ይህ አሰራር የመፃህፍቱ ጠንካራ ጎን ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመፅሀፎቹን ይዘት ለመዳሰስ በተደረገው ሙከራ በመፅሀፎቹ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶችና ጥያቄዎች ለንባብ ከቀረቡ ፅሁፎች የወጡ እና ራሳቸውን ችለውም ከምንባብ ውጭ የቀረቡ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል። ይኸውም በ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ካሉት 25 ያህል የቃላት ትምህርት ጥያቄዎች 15 ወይም 60% ያህሉ ከምንባብ ውጭ የቀረቡ ናቸው። ሌሎች ቀሪዎቹ 10 ጥያቄዎች (40% ያህሉ) ደግሞ ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በይዘት ደረጃ ከመልመጃ ውጭ በመፅሀፉ ውስጥ በተለይም በመጀመሪያው ክፍል ከገፅ1-9 ድረስ ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ይዘቶች እንዲሁም ክንውኖች በቃላት አመሰራረት ርዕስ ስር ተካትተው እናገኛቸዋለን። ይህም በመፅሀፉ ውስጥ ለቃላት ትምህርት በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተሰጠውን ትኩረት ያሳየናል። ነገር ግን በመፅሀፉ ውስጥ የቃላት አመሰራረት ይልና ምህፃረ ቃላትን እና ገላጮችን መጠቀም የሚሉትን ነጥቦችም ከቃላት መመስረቻ ዘዴዎች ስር ተካተው ቀርበዋል። ይህንንም በእስረጅ ስናየው።

አስረጅ1፡- <u>የቃላት አመሰራረት</u>

በዚህ ምዕራፍ የምንማራቸው ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. በዋና ቃል ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር ወይም በማርባት አዳዲስ ቃላትን መመስረት፤
2. ሁለት ቃላትን በማጣመር ቃላትን መመስረት፤
3. ምህፃረ ቃላትን መጠቀም፤
4. ገላጮችን መጠቀም፤

(7ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 1)

ከላይ ከቀረበው አስረጅ መረዳት እንደሚቻለው በመፅሀፉ ውስጥ ምህፃረ ቃላትን መጠቀም እና ገላጭ ቃላትን መጠቀም የሚሉት በርዕስነት ከቃላት መመስረቻ ዘዴዎች ጋር አብረው ቀርበዋል። ይህ ደግሞ ተማሪዎችን ለስህተት ይዳርጋል። ምክንያቱም ምህፃረ ቃላትን መጠቀም እና ገላጮችን መጠቀም እንደ ይዘት መቅረብ የለባቸውምና ነው። መጠቀም ሌላ ጉዳይ ነው፤ በይዘት መልክ ማቅረብ ደግሞ ሌላ። ከላይ እንደምናየው ምህፃረ ቃላትን

መጠቀም ይላል ከዚህ መረዳት የሚቻለውም ምህፃረ ቃላትን በመጠቀም ሀሳብን ማስተላለፍን፣ መግባባት መቻልን ወዘተ እንጂ ስለምህፃረ ቃላት ምንነት፣ ቃላትን እንዴት ይመሰርታሉ ወዘተ. ስለሚለው የሚለው ነገር የለምና ነው። እንዲሁም እርባታን እንደቃል መመስረቻ ይወስደዋል። ይህም በመፅሀፉ ላይ የሚስተዋል ሌላ ችግር ነው።

የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍንም ያየን እንደሆነ እንደ 7ኛ ክፍል መፅሀፍ ሁሉ የቃላት ትምህርቶቹ ከምንባቦች ውስጥም ከምንባቦች ውጭም ተመርጠዋል። በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ከቀረቡት 43 የቃላት ክንውኖች ውስጥ 26 (60.47%) ያህሉ በመፅሀፉ ውስጥ ከቀረቡት ምንባቦች ውጭ የወጡ ሲሆኑ፣ 17 (39.53%) ያህሉ ደግሞ በመፅሀፉ ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ የወጡ ናቸው። የ8ኛ ክፍል መፅሀፍም እንደ 7ኛ ክፍል መፅሀፍ ሁሉ በመፅሀፉ የመጀመሪያ ገፅ ላይ የቃላትን አመሰራረት በተመለከተ በሰፊው ይዳስሳል። ነገር ግን በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቀረቡት የቃላት መመስረቻ ዘዴዎች የተሳሳቱና ተማሪዎችንም የሚያሳስቱ ሆነው አልተገኙም። ይህም ለመፅሀፉ እንደጠንካራ ጎን ሊታይ ይችላል። እንዲሁም ባህልን የሚነኩ፣ ከየታ ጋር የሚጣረሱ ቃላት በሁለቱም መፃህፍት ውስጥ አይስተዋሉም። ይህም ለመፅሀፎቹ እንደ ጥንካሬ ሊታይላቸው ይችላል።

በሌላ በኩል የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥን የሚመለከቱ ሌሎች መስፈርቶች ለምሳሌ፣ ተስተማሪነት፣ የፍቺ ሽፋን፣ በቅርብ መገኘትና የተማሪዎች ፍላጎት በሚሉት መስፈርቶች ሲፈተሹ፣ መማሪያ መፅሀፎቹ በዚህ ረገድ ድክመት እንዳለባቸውና ከላይ ከተጠቀሱት መስፈርቶች አንዱንም እንዳልተጠቀሙ ከአዘጋጆቹና ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በዚህም በመፅሀፎቹ የቃላት ዘይቤዎችና ፈሊጦች፣ የቃላት የከታችና የተከታች ፍቺ፣ የቃላት እማሬ እና ፍካሬ ፍቺ ምንም ተኩረት አልተሰጣቸውም። ይህም መፅሀፎቹ በዚህ ረገድ የሚስተዋልባቸውን ድክመት ያሳያል።

4.4 የቃላት ትምህርቶችን አደረጃጀት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ስለቃላት ትምህርት አደረጃጀት ሲነሳ የአዳዲስ ቃላት አቀራረብ ክትትሎሽና መጠነርዕይ ውሳኔዎች የሚመሰረቱት በስነልሳናዊና በስነትምህርታዊ እሳቤዎች እንዲሁም ባለው የመማር ማስተማር ሁኔታ ግንዛቤ ላይ እንደሆነ ይታወቃል (Dubin እና Olshtain 1992፣47)። ከዚህ አኳያ ቃላት በጥንቃቄ በሚታቀዱ ተከታታይ ደረጃዎች፣ ተስማሚ በሚሆኑበት ስልትና ያለውን ተጨባጭ የመማር ማስተማር ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ

መደራጀት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ተገቢ የቃላት መምረጫ መስፈርቶችን በመጠቀም ለአንድ ደረጃ እንዲመጥኑ ሆነው የተመረጡ ቃላት ባንድ ላይ ለማደራጀትና በመልመጃ መልክ ለመንደፍ የሚያስችሉ የተለያዩ የማደራጃ ስልቶች እንዳሉ በዚሁ ጥናት በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.4 ተገልጿል። ከነዚህ መካከል McCarthy (1990፣ 99-102) Gairns እና Redman (1986፣69-71) የዘረዘሩዋቸው ርዕሰ ጉዳይን፣ ፍቺን፣ የአወቃቀር ቅርፅን፣ አውዳዊ ዝምድናን መሰረት በማድረግ ማደራጀት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ከዚህ በተጨማሪም ቃላትን እንዳስፈላጊነቱ በቃል ክፍላቸው፣ በዲስኩር አያያዝነታቸው፣ በድርብ ቃልነታቸው፣ በፈሊጥነታቸው ወዘተ ማደራጀት ለቃላት ትምህርቱ ስኬት የራሱ ድርሻ እንዳለው ይታመናል።

እንዲሁም የቃላት ትምህርት አደረጃጀት የመማር ሂደቱን የጠበቀና ትርጉም ያለው ሊሆን ይገባል። ይኸውም አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ በከፍተኛ ሁኔታ ከሚደጋገሙ በዝቅተኛ ሁኔታ ወደ ሚደጋገሙ ቀስ በቀስ የሚሄድ መሆን ይኖርበታል።

ከዚህ አንፃር የተተኳሪ መፃህፍቱን የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ለመፈተሽ ሲባል ለመፅሀፎቹ አዘጋጆች ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። በዚህም ቃላቱን ለማደራጀትና በመልመጃ መልክ ለመቅረፅ የተጠቀማችሁበት መስፈርት ምን ነበር? ተብለው የተጠየቁት አዘጋጅ 01 ለጥያቄው ማብራሪያ ጠይቀው ካገኙ በኋላ፡-

> *ይህ አሁን እያሳየሽኝ ያለ ነጥብ ነው። ይህ በደንብ ቢታሰብበት ከአንድ ምንባብ ወደ ሌላው ምንባብ ሲሄድ እንደገናም ደግሞ በራሱም በምንባቡ ውስጥ ተከታታይ ቃላት የሚያነሱት በወጥነት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተካተው እንዲሄዱ ማድረግ ይቻላል። በአንዳንድ ቦታ ላይ በመፅሀፎቹ ውስጥ የሆነ አለ። ግን የአጋጣሚ ይመስለኛል። ነገር ግን መፅሀፎቹን ስናዘጋጅ የቃላትን ትምህርት ለብቻው ትኩረት ሰጥተን በዚህ አይነት ሄደዋል አልሄዱም ብለን አላረጋገጥንም። እንዳውም የቃላት አደረጃጀት ብለን ለብቻው ነጥለን አላየነውም። የተከተልነውም የነበረውን መንገድ ነው። ስለዚህ አደረጃጀት ላይ ከምትለው ነጥብ አንፃር ከታየ ምናልባት ችግር ሊኖር ይችላል።* በማለት መልሰዋል።

አዘጋጅ 02 ተጠይቀው የሰጡት ምላሽም ተመሳሳይ ነው። በተለይም የቃላት አደረጃጀትን በተመለከተ ያዩት ወይም የተከተሉት መስፈርት በተናጥል እንደሌለ እና የነበረውን

መንገድ (Trend) እንደተከተሉ ገልፀዋል። አንድ ምንባብ ውስጥ ካሉ ቃላት ከበድ ይላሉ የምንላቸውን ቃላት በአንድ ላይ በመሰብሰብ በመልመጃ መልክ ተማሪዎች ፍቺያቸውን ወዘተ እንዲያውቁ እናደርጋለን እንጂ አንተ በምትለኝ መስፈርት አላየነውም በማለት አብራርተዋል። በተጨማሪም ቃላቱን ከተለያዩ ክሂሎች ስር ከሚገኙ መልመጃዎች ጋር ለማዛመድና አብረው ለማቅረብ እንደሞከሩ ገልፀዋል። በተለይም በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስር የቃላት ጥያቄዎች እንዳሉ ጠቁመዋል። ለምሳሌ አንድ አረፍተነገር በመውሰድ አረፍተነገሩ ውስጥ የሚገኝ አንድ አዲስ ቃል መስመር ይደረግበትና የዚያ ቃል ፍቺ ምን እንደሆነ ተማሪዎች እንዲመልሱ ይደረጋል፤ በማለት አብራርተዋል።

ከአዘጋጆቹ ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው መፅሀፎቹን ሲያዘጋጁ የቃላት ትምህርቶቹን በአንድ ላይ ለማደራጀትና በመልመጃ መልክ ለመቅረፅ በልምድና በአጋጣሚ ከማደራጀት ያለፈ በሳይንሳዊ የቃላት ትምህርት ማደራጃ መርህን እንዳልተከተሉ የሚያሳይ ነው። ይህም መማሪያ መፅሀፎቹ በቃላት ትምህርት አደረጃጀት ላይ ያለባቸውን ደክመት የሚጠቁም ይሆናል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የተተኳሪ መፅሀፎቹ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መፅሀፎቹን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል። በዚህም በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የቀረቡት ቃላት እንዴት እንደተደራጁ ለመመርመር በየክንዋኔው እንዲቀናጁ የተደረገበትን መንገድ ለማየት ተመክሯል።

ሰንጠረዥ 1፡- የ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

ተ.ቁ	የተደራጁበት ሁኔታ	ክንዋኔ	
		ብዛት	በመቶኛ
1	ባላቸው ፍቻዊ ተዛምዶ የተደራጁ	1	4%
2	ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር የተደራጁ	8	32%
3	ባንድ ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸው የተደራጁ	9	36%
4	ስለቃላት የተወሰነ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ከመቻል አንፃር የተደራጁ	7	28%
ድምር		25	100%

ከሰንጠረዥ 1 መረዳት እንደሚቻለው የቃላት ትምህርቱን በተለያየ መንገድ ተደራጅተው ቀርበዋል። የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ ሆነም አልሆነም ቃላቱ በተለያዩ ክንዋኔዎች ስር እንዲገቡ ተደርገው ቀርበዋል። አንድ ላይ እንዲቀርቡ ከተደረገባቸው መንገዶች አንዱ ቃላቱ ያላቸው ፍቻዊ ተዛምዶ ነው። በ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ቃላት ባላቸው ፍቻዊ ተዛምዶ በተመሳሳይና በተቃራኒነት ፍቺ ሊሆኗቸው ከሚችሉ ጋር ተቀናጅተው የቀረቡባቸው ክንዋኔዎች ብዛት 1 (4%) ነው። ይህም በዚህ ዙሪያ ብዙ ትኩረት እንዳልተሰጠ ያሳያል።

ሌላው ቃላት የተደራጁበት መንገድ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ መመሳሰል ነው። በዚህ መንገድ ከተደራጁት ክንዋኔዎች ውስጥ ስለድርብ ቃላት የሚያወሱት ክንዋኔዎችም ይገኙበታል። በዚህ መልክ የተደራጁት 8 (32%) ያህል ናቸው። ከተጠቀሱት ውጭ 9 (36%) ያህሉ ክንዋኔዎች ደግሞ የተደራጁት በተወሰነ ምንባብ ውስጥ በጋራ በመገኘታቸው ነው። ከዚህ ያለፈ አንድ ላይ ለመቅረባቸው በምክንያትነት መጥቀስ የሚቻለው ምናልባት አዘጋጆቹ ለተማሪዎች በምንባቦቹ ውስጥ እንግዳ ይሆኑባቸዋል ብለው ማሰባቸው ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል በመፅሀፉ ውስጥ ስለቃላት እርባታ (ቅጥያዎች) ለማስተማር የቀረቡትን ጥያቄዎች ብንወስድ ለቃላቱ አንድ ላይ መቅረብ እንደመስፈርት የተወሰደ የሚመስለው ቃሎቹ በቅጥያዎች አማካኝነት ወደ ተለያዩ ቃላት መርባት መቻላቸው እና የተለያዩ ቅጥያዎችን ማስቀጠል መቻላቸው ነው። በዚህም በመፅሀፉ ውስጥ ስለቃላት የተወሰነ ግንዛቤ ከማስጨበጥ አንፃር የተደራጁ 7 (28%) ያህል ጥያቄዎችን እናገኛለን።

ባጠቃላይ በጥሩ የቃላት ማደራጃ መስፈርትነት ምሁራን ከሚጠቀሷቸው ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ ከሚኖራቸው የፍቺ ተዛምዶና ከሚኖራቸው የቅርፅ ተመሳስሎ አንፃር ሲታይ የ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የቃላት አደረጃጀት ችግር እንዳለበት ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል። በዚህም ከአጠቃላይ 25 ጥያቄዎች 9 (36%) ያህሉ ብቻ ናቸው ከላይ ባልናቸው መስፈርቶች የተደራጁት። ሌሎቹ 16 (64%) ያህሉ ግን የተደራጁት ባንድ ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸው እና ስለቃላት የተወሰነ ግንዛቤ ከማስጨበጥ አንፃር ነው። ይህም በመፅሀፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ላይ ችግር እንዳለ አመላካች ነው።

ለንጠረዥ 2፡- የ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

ተ.ቁ	የተደራጁበት ሁኔታ	ክንዋኔ	
		ብዛት	በመቶኛ
1	ባላቸው ፍቻዊ ተዛምዶ የተደራጁ	1	2.32%
2	ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር የተደራጁ	14	32.56%
3	ባንድ ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸው የተደራጁ	12	27.90%
4	ስለቃላት የተወሰነ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ከመቻል አንፃር የተደራጁ	16	37.20%
ድምር		43	100%

ከሰንጠረዥ 2 መረዳት እንደሚቻለው እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም የቃላት ትምህርቱ የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኙ ሆነም አልሆነ ቃላቱ በተለያየ ክንዋኔ ስር እንዲገቡ ተደርገው ቀርበዋል። አንድ ላይ ተደራጅተው እንዲቀርቡ ከተደረገባቸው መንገዶች አንዱ ቃላቱ ያላቸው ፍቻዊ ተዛምዶ ነው። በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ቃላት ባላቸው ፍቻዊ ተዛምዶ ምክንያት በተመሳሳይነትና በተቃራኒነት ፍቺ ሊሆኗቸው ከሚችሉ ቃላት ጋር ተቀናጅተው የቀረቡባቸው ክንዋኔዎች ብዛት 1 (2.32%) ነው። ይህም መፅሀፉ በዚህ ረገድ የሚስተዋልበትን ድክመት ያሳያል።

ሌላው በመፅሀፉ ውስጥ ቃላት የተደራጁበት መንገድ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ መመሳሰል ነው። በዚህ መንገድ ከተደራጁት ክንዋኔዎች በመፅሀፉ ውስጥ በገፅ 2 የሚገኙት ጥምር ቃላት እና ቅጥያዎችን የሚመለከቱትን ክንዋኔዎች መጥቀስ ይቻላል። በዚህ መልክ የተደራጁት ክንዋኔዎችም 14 (32.56%) ያህል ናቸው። ሌላው በመማሪያ መፅሀፉ ወስጥ 12 (27፣90%) ያህሉ ክንዋኔዎች ደግሞ የተደራጁት በአንድ ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸው ነው። ከዚህ ባለፈ አንድ ላይ ለመቅረባቸው በምክንያትነት መጥቀስ የሚቻለው ምናልባት በአዘጋጆቹ ለተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ እንግዳ ይሆኑባቸዋል ተብለው መታሰባቸው ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል ስለቃላት የተወሰነ እውቀት ከማስጨበጥ አንፃር የተደራጁ ክንውኖችም አሉ። በዚህ መንገድ ማደራጀት የራሱ ድክመት አለው። በተለይም አደረጃጀቱ በጠበቀ የቃላቱ ትስስር ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ቃላቱ በቀላሉ እንዳይታወሱ ያደርጋል። በመፅሀፉ ውስጥ በዚህ መንገድ የተደራጁ በርከት ያሉ ክንውኖች ይገኛሉ። በዚህም ከአጠቃላይ ክንውኖች 16 (37.20%) ያህሉ በዚህ መንገድ ተደራጅተው ቀርበዋል። ለዚህም በመፅሀፉ ገፅ 3 ላይ የቀረቡትን የቃላት አመሰራራትን የሚመለከቱትን ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል።

አስረጅ2፡- በ ‹‹ሀ›› ስር የተሰጡትን ቅጥያዎችን በ ‹‹ለ›› ስር ከተሠጡት ቃላት ላይ በመቀጠል የምትችሉትን ያህል ቃል መስርቱ።

ሀ	ለ	የሚመሰረት ቃል
1. -ነት	ሀ. ልጅ	----------
2. -ሽ	ለ. ሆድ	----------
3. -ኡ	ሐ. መስበር	----------
4. -ኣም ወዘተ.	መ. ነገር	----------

(8ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 3)

በዚህ ክንውን ላይ እንደምናየው የተለያዩ ቃላት ተዘርዝረዋል፤ ቅጥያዎችም እንዲሁ ተዘርዝረዋል። ነገር ግን ለቃላቱ አብረው መቅረብ እንደመስፈርት የሚሆነው ቅጥያዎችን መውሰዳቸው ካልሆነ በቀር ሌላ መስፈርት ልናገኝ አንችልም። በዚህም ምክንያት አደረጃጀታቸው በጠበቀ ትስስር ላይ የተመሰረተ አይሆንም። ይህም ከላይ እንደተገለፀው ቃላቱ በቀላሉ እንዳይታወሱ ሊያደርግ ይችላል።

በአጠቃላይ በጥሩ የቃላት ማደራጃ መስፈርትነት ከሚጠቀሱት ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ ከሚኖራቸው የፍቺ ተዛምዶና ከሚኖራቸው የቅርፅ ተመሳስሎ አንፃር ሲታይ የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍም የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ድክመት እንዳለበት መረዳት ይቻላል። በዚህም ከአጠቃላይ 43 ጥያቄዎች 15 (34.88%) ያህሉ ብቻ ናቸው ከላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች አንፃር የተደራጁት። ቀሪዎቹ 28 (65.11%) ያህሉ ግን የተደራጁት ባንድ

ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸው እና ስለቃላት የተወሰነ ግንዛቤ ከማስጨበጥ አንፃር ነው። ይህም በመፅሀፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ላይ ችግር እንዳለ የሚያሳይ ነው።

በአጠቃላይ የሁለቱ መፃህፍት አዘጋጆች የሰጡት ምላሽ እና ከመፅሀፎቹ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው መማሪያ መፅሀፎቹ በቃላት ትምህርት አደረጃጀት ላይ ያላቸውን ድክመት ነው። ምክንያቱም ከላይ እንደተገለፀው አዘጋጆቹ መፅሀፎቹን ሲያዘጋጁ የቃላት ትምህርት አደረጃጀትን በተመለከተ ለብቻው ትኩረት ሰጥተው እንዳልተመለከቱት እና መስፈርት ተከትለው ሳይሆን በልምድ እንዳደራጁት ገልፀው ነበር። ከመፅሀፎቹ የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም የሁለቱም መማሪያ መፅሀፎች የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ድክመት እንደሚስተዋልበት መጠቆም ይቻላል። ምክንያቱም ከመረጃው የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የቃላት ትምህርቶቹ ሳይንሳዊ መርሆችን ተከትለው የተደራጁ አይደሉምና ነው።

4.5 የቃላት ትምህርቱን አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

4.5.1 የቃላት ትምህርቶቹን አውዳዊ አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.1 እንደተገለፀው አንድ ቃል ምንም አይነት የቅርፅ ለውጥ ሳይደረግበት በተለያዩ አውዶች ውስጥ የተለያየ ፍቺ ሊሰጥ ይችላል። የዚያ ቃል ትክክለኛ ፍቺ ሊታወቅ የሚችለው ቃሉ ቢያንስ በዓረፍተነገራዊ አውድ ሲገባ ነው። Lowson እና Hogben (1996፣106) እንደሚያስገነዝቡት ከስነልሳናዊም ሆነ ከስነልቦናዊ እይታ አንፃር ቃላት የተሸከሙት ፍቺ ግልፅ የሚሆነው ትርጉም ባለው አውድ ውስጥ ሲገቡ እንደሆነ እስከታመነበት ድረስ የቃላት የመማር ማስተማርም አውዳዊ አቀራረብን መሰረት ማድረግ ይኖርበታል።

ቃላትን በአውድ ስለማቅረብ ሲነሳ፣ የቃላቱን ፍቺ ከአውዳቸው መተንበይ በሚቻልበት አኳኋን ማቅረብ ቸል የማይባል ጉዳይ ነው። ለተማሪዎች ፍንጭ በመስጠት የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ እንዲተነብዩ ማድረግ አመርቂ ወደሆነ የማስታወስ ችሎታ ሊያመራ እንደሚችል ይታወቃል። ሆኖም Verspoor እና Lowie (2003፣549) እንደሚያስረዱት ቃላቱ የሚቀርቡበት አውድ የተተንባይነት ደረጃውን የጠበቀ ሊሆን ይገባል። ይህም ሲባል

በቃሉና በቀረበበት አውድ ውስጥ በሚገኙ ቃላት መካከል ጠንካራ ንክኪ ካለ ወይም Nation እና Coady (1988፣105) እንደሚገልፁት ዓረፍተነገራዊ አውድ ረጅም (ከ10 ቃላት በላይ) ወይም አጭር (ከ5 ቃላት በታች) ከሆነ በቃሉ ተተንባይነት ብቃት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

የተተኳሪ መፃህፍቱን የቃላት ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ለመፅሀፎቹ አዘጋጆች የቃላት ትምህርቶቹ አቀራረብ የቃላቶቹን አውዳዊነት የተከተለ ነወይ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። በዚህም አዘጋጆቹ በሰጡት ምላሽ የቃላት ትምህርትን አቀራረብ በተናጥል ለብቻው የተለየ ትኩረት እንዳልሰጡት ነገር ግን የቃላቱን ትምህርት ከተለያዩ ክሂሎች ጋር በማጣመር ለማቅረብ እንደሞከሩ ገልፀዋል። ቢሆንም ግን የቃላቱን አውዳዊ አቀራረብ የተለየ ትኩረት ሰጥተው ባይሰሩትም በመፅሀፎቹ ውስጥ ግን ቃላት በአውድ ጭምርም እንደቀረቡ ገልፀዋል። ይህንን ሲሉ ግን በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የቃላት ትምህርቱን አቀራረብ ለብቻው የተለየ ትኩረት ባይሰጡትም አጠቃላይ ለመፅሀፎቹ ዝግጅት በሰጡት ትኩረት የቃላት ትምህርቱም አብሮ ትኩረት ተሰጥቶት በአቀራረቡ ላይ ቃላት በአውድ ተደግፈው የቀረቡበት ክፍል እንዳለም ለመግለፅ ነው። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ በአውድ ተደግፈው እንዳልቀረቡና ከአውድ ውጭም የቀረቡ ቃላት እንዳሉ ገልፀዋል።

ከአዘጋጆቹ ምላሽ መረዳት የሚቻለው ለቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ የተለየ ትኩረት እንዳልተሰጠው ነው። ነግር ግን በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ በመጠኑም ቢሆን አውዳዊ አቀራረቦች መኖራቸውን ነው። ይህም የሚያሳየው ለመፅሀፎቹ ዝግጅት በአጠቃላይ በሰጡት ትኩረት እንጅ ለቃላት ትምህርቱ አቀራረብ በተናጥል በሰጡት ትኩረት የሰሩት እንዳልሆነ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የተተኳሪ መፃህፍቱን የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የመፃህፍቱን ይዘት ለመፈተሽ ተሞክሯል። በመሆኑም መማሪያ መፃህፍቱ ለቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ የሰጡት ትኩረት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 3፡- የ7ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት ትምህርቱን አውዳዊ አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች

ተ.ቁ	የቀረቡበት ሁኔታ	በአውድ የቀረቡ		በአውድ ያልቀረቡ	
		በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ
1	በዓረፍተነገር ተደግፈው የቀረቡ ቃላት ክንውኖች	3	12%	--	--
2	ለቀረቡት ቃላት ፍቺያቸውን አረፍተነገር ሰርቶ ማሳየትን የሚጠይቁ ክንውኖች	5	20%	--	--
3	ከፍቺ መመሳሰልና ከተቃራኒ ፍቺ አንፃር የቀረቡ ክንውኖች	7	28%	1	4%
4	ስለቃላት የተወሰነ እውቀት ለማስጨበጥ የቀረቡ ክንውኖች	--	--	9	36%
ድምር		15	60%	10	40%

ከሰንጠረዥ 3 መረዳት እንደሚቻለው የ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ 25 የቃላት ጥያቄዎች 15 (60%) ያህሉ በአውድ የቀረቡ ሲሆኑ 10 (40%) ያህሉ ደግሞ ከአውድ ውጭ የቀረቡ ናቸው። እነዚህም 3 (12%) ያህሉ ቃላቱ በዓረፍተነገራዊ አውድ ተደግፈው የቀረቡባቸው ሲሆን፣ 5 (20%) ያህሉ ደግሞ ተማሪዎች ለቀረቡላቸው ቃላት ፍቺያቸውን ዓረፍተነገር ሰርተው እንዲያሳዩ የሚያለማምዱ ናቸው። እንዲሁም ከፍቺ መመሳሰልና ከተቃራኒ ፍቺ አንፃር ከቀረቡት ክንውኖች 7 (28%) ያህሉ በአውድ የቀረቡ በተለይም ከምንባቦች ውስጥ አውዳዊ ፍቺ እንዲፈልጉ የሚጋብዙ ሲሆኑ፣ አንዱ ክንውን ግን ከአውድ ውጭ የቀረበ ሆኖ ተገኝቷል። በተመሳሳይ ስለቃላት የተወሰነ እውቀት ለማስጨበጥ ከቀረቡት ክንውኖች ውስጥ 9 (36%) ያህሉም ከአውድ ውጭ የቀረቡ ናቸው። ነገር ግን እነዚህ ቃላት በዋናነት ለማስተማር የገቡት በቅጥያዎች ቃላትን ስለመመስረት፣ ስለጥምር ቃላት ወዘተ ስለሆነና

ፍቺን ለማስተማር ስላልገቡ በአውድ አለመቅረባቸው በመፅሀፉ የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የጎላ ላይሆን ይችላል።

የቃላት ትምህርት ውጤታማ ከሚሆንባቸው አቀራረቦች አንዱ የቃላት ትምህርትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ ነው። በዚህ ረገድ በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው አብዛኞቹ ክንውኖች በአውድ የቀረቡ ናቸው። ምንም እንኳ አዘጋጆቹ በሰጡት ምላሽ ይህንን ጉዳይ የተለየ ትኩረት እንዳልሰጡት ቢገልፁም። በመሆኑም Harmer (1993፣24) ቃላትን በተናጥል ከማቅረብ ይልቅ በአውድ ማቅረብ ቃላቱ ለረዥም ጊዜ ሳይረሱ እንዲቆዩ ለማድረግ ያግዛል የሚለውን ሀሳብ በተገቢው ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ውጤት ያመለክታል።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍን የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ ከመፅሀፉ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን በዝርዝር እንመልከታቸው።

ሰንጠረዥ 4፡- የ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ

ተ.ቁ	የቀረቡበት ሁኔታ	በአውድ የቀረቡ		በአውድ ያልቀረቡ	
		ብዛት	በመቶኛ	ብዛት	በመቶኛ
1	በዓ.ነገር ተደግፈው የቀረቡ የቃላት ትምህርት ክንውኖች	5	11.62%	--	--
2	ለቀረቡት ቃላት ፍቺያቸውን ዓ.ነገር ሰርቶ ማሳየትን የሚጠይቁ ክንውኖች	10	23.25%	--	--
3	ለፍቺ መመሳሰልና ከተቃራኒ ፍቺ አንፃር የቀረቡ ክንውኖች	8	18.60%	1	2.32%
4	ስለቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የቀረቡ ክንውኖች	--	--	19	44.18%
	ድምር	23	53.47%	20	46.51%

ከሰንጠረዥ 4 መረዳት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ 43 የቃላት ክንውኖች ውስጥ 23 (53.47%) ያህሉ በአውድ የቀረቡ ሲሆን 20 (46.51%) ያህሉ ደግሞ ያለ አውድ የቀረቡ ናቸው። ይህም 5 (11.62%) ያህሉ ቃላት በዓረፍተነገራዊ አውድ ተደግፈው የቀረቡ ሲሆን፣ 10 (23.25%) ያህሉ ደግሞ ተማሪዎች ለቀረቡላቸው ቃላት ፍቺያቸውን ዓረፍተነገር ሰርተው እንዲያሳዩ የሚያለማምዱ ናቸው። እንዲሁም ከፍቺ መመሳሰልና ከተቃራኒ ፍቺ አንፃር ከቀረቡት ክንውኖች 8 (18.60%) ያህሉ በአውድ የቀረቡ በተለይም ከምንባቦች ውስጥ የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ እንዲፈልጉ የሚጋብዙ ሲሆኑ፣ አንዱ ክንውን ግን ከአውድ ውጭ የቀረበ ሆኖ ተገኝቷል። በተመሳሳይ ስለቃላት የተወሰነ እውቀት ለማስጨበጥ የቀረቡ ክንውኖች 19 (44.18%) ያህሉም ከአውድ ውጭ የቀረቡ ሆነው ተገኝተዋል። ነገር ግን እነዚህ ቃላት ለማስተማር የገቡት የቃላት አመሰራረትን፣ ቅጥያዎችን፣ ጥምር ቃላትን ወዘተ ስለሆነና ፍቺን ለማስተማር ስላልገቡ በአውድ አለመቅረባቸው በመፅሀፉ የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ላይኖር ይችላል።

ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ውጤት የሚያሳየው በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ክንውኖች ስለቃላት እውቀት ለማስጨበጥ ከቀረቡት ክንውኖች ውጭ ሌሎቹ በአውድ የቀረቡ መሆናቸውን ነው። የቃላት ትምህርት ውጤታማ ከሚሆንባቸው አቀራረቦች አንዱ የቃላት ትምህርትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ ነው። በዚህ ረገድ በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ አብዛኞቹ ክንውኖች በአውድ የቀረቡ መሆናቸው ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት ያሳያል። ምንም እንኳ አዘጋጆቹ ይህን በተመለከተ በሰጡት መረጃ ይህን ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው እንዳልተመለከቱት ቢገልፁም። በመሆኑም Harmer (1993፣24) ቃላትን በተናጥል ከማቅረብ ይልቅ በአውድ ማቅረብ ቃላቱ ለረዥም ጊዜ ላይረሱ እንዲቆዩ ለማድረግ ያግዛል የሚለውን ሀሳብ በተገቢው ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ውጤት ያመለክታል።

ሌላው የቃላትን አውዳዊ አቀራረብ ስናነሳ ቃላት የቀረቡባቸው አረፍተነገራዊ አውዶች መጠን ማየቱ አይቀሬ ጉዳይ ነው። በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.1 እንደተገለፀው ቃላት የሚቀርቡባቸው ዓረፍተነገራዊ አውዶች ከአምስት እስከ አስር ቃላትን የያዙ ሲሆኑ

የቃላትን ፍቺ ለመገመት ያመቻሉ። በአንፃሩ ከአምስት መጠኑ እያነሰ እና ከአስር እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለትንበያው የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እየቀነሰ ይሄዳል። በመሆኑም ቃላት የሚቀርቡባቸው ዓረፍተነገራዊ አውዶች በጣም አጭር ወይም ረጅም መሆን የለባቸውም።

ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መፃህፍቱ ውስጥ የቃላት ትምህርቶቹ የቀረቡባቸውን የአረፍተነገሮች መጠን ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመሆኑም በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ በአውድ ከቀረቡ ክንውኖች ውስጥ በዓረፍተነገር ተደግፈው የቀረቡት የቃላት ክንውኖች እና ለቀረቡት ቃላት ፍቺያቸውን በዓረፍተነገር ሰርቶ ለማሳየት የሚጠይቁ ክንውኖች በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል። በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ያሉት ቃላት ብዛታቸውም በአብዛኛው ከአምስት እስከ አስር ሆኖ ተገኝቷል። በሌላ በኩል ግን በመፅሀፎቹ ውስጥ ከፍቺ መመሳሰልና ከተቃራኒ ፍቺ አንፃር በአውድ የቀረቡ ክንውኖች ግን በአብዛኛው በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ ከላይ ከተጠቀሰው መለኪያ ውጭ ሆነው ተገኝተዋል። ምክንያቱም በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ ከፍቺ ጋር የተያያዙት ጥያቄዎች የወጡት ከምንባቦች ውስጥ መሆኑና ፍቺያቸውን ለመረዳት ምንባቦችን አንብቦ መጨረስን መጠየቃቸው ፍቺ መተንበይ ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ነው። ነገር ግን ይህ አንደ ትልቅ ድክመት ሊታይ አይችልም። ምክንያቱም የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ ተማሪዎች ሲለዩ ቃሉ የገባበትን ዓረፍተነገር ብቻ በማየት ሊተነብዩ ይችላሉና ነው። ደግሞም ተማሪዎች ሙሉ ምንባቡን አንብበው ጨርሰው የቃላቱን ፍቺ መፈለጋቸው ምንም ድክመት የለውም፤ ጥንካሬ እንጅ። ምክንያቱም በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.1 እንደተገለፀው ቃላት በአውድ ከሚቀርቡባቸው መንገዶች አንዱ ከምንባብ ውስጥ ማውጣት ነውና።

እስኪ ከመማሪያ መጽሀፎች ውስጥ የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ የሚጠይቁ ቃላትን ለምሳሌ ያህል እየወሰድን በአስረጅ እንመልከት።

አስረጅ3፡- ከዚህ ቀጥሎ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡- በቀለ የአባቱ ሀብት <u>ተካፋይ</u> ነው። /ድርሻውን የሚወስድ/

በቀለ የአባቱን ችግር <u>ተካፋይ</u> ነው። /ለችግር ደራሽ/

ሀ. ሽንኩርት ረከሰ / /

ለ. በሰራው መጥፎ ድርጊት ስሙ ረከሰ / /

ሐ. ፀሀይ ስትወጣ እመጣለሁ / /

መ. ተራራ ስትወጣ እመጣለሁ / /

ሠ. የበጉ ቆዳ በአራጁ ተገፈፈ / /

ረ. በሬዎቹን ሁሉ በሌባ ተገፈፈ / /

(7ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 13)

ይህን ከ7ኛ ክፍል መፅሀፍ የተጠቀሰውን አስረጅ ስናየው ተማሪዎች አውዱን በመጠቀም የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ ለማወቅ ብዙም እንደማይቸገሩ ነው። ነገር ግን ከተሰጠው ምሳሌ ማየት እንደሚቻለው ቃሉ በተለያየ አውድ ገብቶ የተለየ ትርጉም አያሳይም። ተመሳሳይ ትርጉም ነው የያዘው። ለዚህም በአስረጁ የቀረበውን ‹‹ተካፋይ›› የሚለውን ቃል ማየት በቂ ነው። በመፅሀፉ ሌላው ክፍልም ይህን መሰል እና ሌሎች ከምንባብ የወጡ በአውድ የቀረቡ ጥያቄዎች በርከት ብለው ይገኛሉ። አቀራረባቸውም በጠንካራ ጎናቸው የሚጠቀስና ለመተንበይ የማያስቸግሩ ናቸው። ከላይ የተጠቀሰው አይነት አንዳንድ ችግር ቢኖርባቸውም።

አስረጅ4፡ ምንባቡን እንደገና በማስተዋል አንብቡና የሚከተሉት ቃላትና ሀረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍቺ/ አገባባዊ ትርጉም ግለፁ።

ሀ. ትግል ሐ. አመለጥኩ ሠ. ቅኝ ተገዥነት ..

ለ. ወጣት መ. ተወኝ ረ. ዜማ እንዳጠና ወዘተ...

(8ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 43)

በዚህ በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥም ከላይ በተገለፀው አስረጅ እንደምናየው ምንባቡን በደንብ አንብበው የቃላቱንና የሀረጋቱን አውዳዊ ፍቺ እንዲፈልጉ ነው የሚያዝዘው። ነገር ግን ጥያቄው በራሱ ብዙ ችግር የሚስተዋልበት ነው። ማለትም ቃላትና ሀረጋትን ቀላቅሎ

የትኞቹ ሀረጎች የትኞቹ ደግሞ ቃላት እንደሆኑ ሳይለይ ማቅረቡ ተማሪዎችን የሚያላስት ነው። ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ‹‹ትግል›› እና ‹‹ወጣት›› የሚሉት ብቻ ናቸው ቃላት ሌሎቹ ግን ዓረፍተ ነገሮች ናቸው። ‹‹አመለጥኩ››፣ ‹‹ተወኝ››፣ ‹‹ቅኝ ተገዥነት›› እና ‹‹ዜማ እንዳጠና›› የሚሉት ዓረፍተነገሮች ናቸው። ስለነዚህ ጉዳዮች ደግሞ መፅሀፉ በዝርዝር የሚያብራራው ነገር የለም። በዚህም ተማሪዎችን ለስህተት ሊዳርጋቸው ይችላል።

በአጠቃላይ ከሁለቱም መማሪያ መፅሀፎች የሰነድ ፍተሻ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የሁለቱም መፅሀፎች የቃላት አቀራረብ በአብዛኛው አውድን የተከተለ ሆኖ ተገኝቷል። በተለይም ስለቃላት የተወሰነ እውቀት ለማስጨበጥ ከቀረቡት ክንውኖች ውጭ በሁለቱም መፅሀፎች የቀረቡት አብዛኞቹ ክንውኖች በአውድ የቀረቡና ከአውድ ለመተንበይ ብዙ የማያስቸግሩ ሆነው ተገኝተዋል። ነገር ግን ከላይ የቀረቡት አይነት ስህተቶች ደግሞ ተማሪዎችን ለስህተት የሚዳርጉ በመሆናቸው ከአዘጋጆቹ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

4.5.2 የቃላትን የፍቺ ዝምድና አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

Bauer (1998፣ 31-34) እንደሚያስረዱት ፍቺን መሰረት ያደረገ የቃላት ዝምድና በቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ፣ በከታች ተከታችና በአብሮ ተሰላፊ ቃላት ዝምድና ላይ ያተኩራል። በዚህም ቃላት እርስ በርሳቸው እንዴት ይዛመዳሉ? በአንድ ስነልሳናዊ አውድ ተከታትሎ በመሰለፍ ፍቺን እንዴት ግልፅ ያደርጋሉ? የሚሉ ነጥቦች በትምህርቱ ዝግጅት ትኩረት የሚቸራቸው ናቸው።

ስለተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት ትምህርት ሲነሳ፣ ቃላት ፍፁም ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ስለማይሆኑ አንድ ቃል በተለያየ አውድ ሲገባ የተለያየ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ ሊኖረው ይችላል። ይህንኑ ለተማሪዎች ማሳየት ይቻል ዘንድ የቃላት ማስተማሪያ ስልት አውዳዊ መሆን እንደሚገባው ምሁራን ያሰምሩበታል (Wallace 1988፣76)።

ቃላት የተመሳሳይና የተቃራኒ ፍቺ ዝምድና ብቻ ሳይሆን፣ የከታች (አጠቃላይ) ተከታች (ዝርዝር) እና በአንድ አውድ አብሮ በመሰለፍ የፍቺና የአውድ ዝምድናን የማሳየት ባህሪ አላቸው። ከዚህ አኳያ በመማሪያ መፃህፍት የሚካተት የቃላት ትምህርትም የከታችና

የተካታች ቃላትን የፍቺ ዝምድና የሚፈትሽ፣ አንድ ቃል ከየትኛው ቃል ቀድሞ ወይም ተከትሎ ይገባል? የሚለውን የሚያስለይ፣ እንዲሁም በተገቢው አውድ ተገቢውን ቃል መርጦ ለመጠቀም የሚያስችል ትምህርት ማቀፍ እንዳለበት ይታመናል።

ከዚህ አንፃር ለመፅሀፎቹ አዛጋጆች የቃላት ትምህርቱን አቀራረብ በተመለከተ የቃላት ትምህርቱን ስታቀርቡ የቃላትን የፍቺ ዝምድና ከግምት አስገብታችኋል ወይ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ የተለየ ትኩረት እንዳልሠጡት እና የራሳቸውን ልምድ ተጠቅመው እንዳቀረቡት ገልፀዋል። በተለይም በቃላት አቀራረብ ውስጥ የቃላትን የፍቺ ዝምድና ትኩረት ሰጥተው እንዳልተመለከቱት እና ከዚህ አንፃርም የቃላት ትምህርቱን ለማቅረብ እንዳልሞከሩ ገልፀዋል።

ሌላው የቃላትን የፍቺ ዝምድና አቀራረብ ምን እንደሚመስል በተተኳሪ መፃህፍቱ ላይ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል። በዚህም በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ በተካሄደው ፍተሻ በጠቅላላው በመፅሀፉ ውስጥ ከቀረቡት 25 ክንውኖች ውስጥ 14 ያህሉ ከቃላት ፍቺ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። እነዚህንም በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.2 በተገለፁት ቃላትን በተመሳሰሏቸው እና በተቃርኗቸው፣ በቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት እንዲሁም በአብሮ ተሰላፊነታቸው ያላቸውን አቀራረብ በዝርዝር ለማየት ተሞክሯል።

ሰንጠረዥ 5፡- ስለቃላት ፍቻዊ ዝምድና አቀራረብ ከ7ኛ ክፍል መፅሀፍ የተገኙ መረጃዎች ተንተና

ተ.ቁ	የክንውኑ አይነት	የክንውኑ ብዛት	
		በቁጥር	በመቶኛ
1	የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን የሚመለከቱ ክንውኖች	8	57.14%
2	አብሮ ተሰላፊ ቃላት አውድ ተኮር ሆነው የቀረቡባቸው ክንውኖች	3	21.43%
3	የቃላት የከታች እና ተከታች ፍቺ የሚያመለክቱ ክንውኖች	--	--
4	የቃላትን ፍቺ በዓ.ነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቁ ክንውኖች	3	21.43%
	ድምር	14	100%

በሰንጠረዥ 5 እንደተዘረዘረው በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ የቃላቱን ፍቻዊ ዝምድና ለማስተማር ከቀረቡት የተለያዩ ክንውኖች ውስጥ የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የሚመለከቱ ክንውኖች 8 (57.14%) ሲሆኑ፣ አብሮ ተሰላፊ ቃላት አውድ ተኮር ሆነው ቀረቡበት ደግሞ 3 (21.43%) ያህል ናቸው። እንዲሁም የቃላትን ፍቺ በዓረፍተነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቁ 3 (21.43%) ክንውኖችም በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ቀርበዋል። ነገር ግን የቃላት የከታች (አጠቃላይ) እና ተከታች (ዝርዝር) ፍቺን የሚመለከቱ ምንም ክንውኖች አለመኖራቸው መማሪያ መጽሀፉ በዚህ ረገድ ያለበትን ድክመት ያሳየናል። ምክንያቱም የቃላት ፍቻዊ ዝምድና ከሚቀርብባቸው መንገዶች የከታች ተከታች ግንኙነት አንዱ ስለሆነ ነው።

ከሰንጠረዥ 5 የተገኘው ውጤት እንደሚሳየው የቃላትን የፍቺ ዝምድና የሚመለከቱ ክንውኖች በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ በብዛትም ባይሆን በቂ ነው በሚባል ሁኔታ መካተታቸውን ነው። ነገር ግን የቃላትን የከታች ተከታች ግንኙነት የሚመለከቱ ክንውኖች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አለመካተታቸው ተማሪዎች በቃላት መካከል ያለውን የከታች እና ተከታች ግንኙነት እንዳይረዱና የቃላቱን ስነፍቻዊ ስፋትና ጥበት እንዳያውቁ ያደርጋቸዋል። ይህም መፅሀፉን የፍቺ ዝምድና አቀራረብ ድክመት እንዳለበት ያሳየናል።

በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ በተደረገው ፍተሻም በጠቅላላው ከቀረቡት አጠቃላይ 43 ክንውኖች ውስጥ 15 ያህሉ ክንውኖች ከፍቺ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። እነዚህን ክንውኖችም እስኪ እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ በሠንጠረዥ በዝርዝር እንያቸው።

ሰንጠረዥ 6፡- ስለቃላት ፍቻዊ ዝምድና አቀራረብ ከ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ተ.ቁ	የክንውኑ አይነት	የክንውኑ ብዛት	
		በቁጥር	በመቶኛ
1	የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የሚመለከቱ ክንውኖች	6	40%
2	አብሮ ተሰላፊ ቃላት አውድ ተኮር ሆነው የቀረቡባቸው ክንውኖች	4	26.67%
3	የቃላት የከታች ተከታች ፍቺን የሚያመለክቱ ክንውኖች	--	--
4	የቃላትን ፍቺ በዓ.ነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቁ ክንውኖች	5	33.33%
	ድምር	15	100%

በሰንጠረዥ 6 እንደተዘረዘረው በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ የቃላትን ፍቻዊ ዝምድና ለማስተማር ከቀረቡት የተለያዩ ክንውኖች ውስጥ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን የሚመለከቱ ክንውኖች 6 (40%) ያህል ሲሆኑ፣ አብሮ ተሰላፊ ቃላት አውድ ተኮር ሆነው የቀረቡበት ደግሞ 4 (26.67%) ያህሉ ናቸው። እንዲሁም የቃላትን ፍቺ በዓረፍተነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቁ 5 (33.33%) ክንውኖች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ቀርበዋል። ነገር ግን የቃላትን የከታች ተከታች ፍቺን የሚመለከቱ እንደ 7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ሁሉ በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም ምንም አይነት ይዘት አልተካተተም። ይህም በዚህ ረገድ በሁለቱም መፅሀፎች ላይ ያለውን ድክመት ሊያሳየን ይችላል።

ከሰኝጠረዥ 6 የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የፍቺ ዝምድናን የሚመለከቱ ክንውኖች በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም እንደ 7ኛ ክፍል መፅሀፍ ሁሉ በበቂ ሁኔታ መቅረባቸውን ነው። ነገር ግን በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም የቃላት የከታች ተከታች ፍቺን የሚመለከቱ ክንውኖች ምንም አለመቅረባቸው መፅሀፉ በዚህ ረገድ ድክመት እንደሚስተዋልበት አመላካች ነው። በዚህም ተማሪዎች በቃላት መካከል ያለውን የከታች ተከታች ግንኙነት ለመረዳትና የቃላቱን ስነፍቻዊ ስፋትና ጥበት ለማወቅ ይቸገራሉ።

በተተኳሪ መፅሀፎቹ ውስጥ ከቃላት ፍቻዊ ዝምድና ጋር በተያያዘ ንበት ሊያመጣ የሚችለውን የፍቺ ለውጥ የሚያስገነዝቡ ይዘቶች መካተታቸውን ለማረጋገጥ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል። በዚህም በ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ንበት ሊያመጣ የሚችለውን የፍቺ ለውጥ የተመለከቱ ይዘቶች አለመካተታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። በሌላ በኩል ግን ንበት ሊያመጣ የሚችለውን የፍቺ ለውጥ የተመለከቱ ይዘቶች በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ መካተታቸው በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል። ይህንንም በአስረጅ እንመልከተው።

አስረጅ5፡- በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚጠቁትን ሆሄ አውጥታችሁ ፃፉ። ሁለት ሁለት እየሆናችሁ አንዳችሁ ሆሄው ሲጠቁት ቃሉ የሚኖረውን ትርጉም ሌሎቻችሁ ደግሞ ሆሄው ሳይጠቁት ቃሉ የሚኖረውን ትርጉም ዓረፍተነገር እየሰራችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡- ቃል የሚጠብቅ ሆሄ ሲጠብቅ የሚኖረው ትርጉም ሲላላ የሚኖረው ትርጉም

አለ ‹‹ለ›› ካሳ በህይወት አለ። መፅሀፍ ማንበብ ጥሩ ነው አለ።

1.1 ስለ 3.3 በላ

1.2 ገና 3.4 ገላ

(የአማርኛ 8ኛ ክፍል፣ ገፅ 27)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አስረጆች የሚያሳዩት በ8ኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ጥብቀትን የሚመለከትና ጥብቀት የሚፈጠረውን የፍቺ ልዩነት የሚያሳዩ ጥያቄዎች መቅረባቸውን ነው። ነገር ግን ጥያቄዎቹ በራሳቸው ችግር ያለባቸው ናቸው። በተለይም ‹‹ስለ›› እና ‹‹ገላ›› የሚሉት ቃላት የሚጠብቁ ቃላት አለመሆናቸው ቃላቱ በሚመረጡበት ጊዜ ትኩረት አለመሰጠቱን የሚያሳዩ ናቸው። ተማሪዎችንም ሊያደናግሩ ይችላሉ።

በአጠቃላይ የተተኳሪ መፅሀፎቹ የቃላት የፍቺ ዝምድና አቀራረብ በአይነትም ሆነ በመጠን በርከት ያሉ ተግባራትን ይዟል። በተለይም ከ7ኛ ክፍልም በተሻለ የ8ኛ ክፍል እንደ ጥብቀት ያሉ ክንውኖችን ጨምሮ አካቶ ይዟል። ምንም እንኳ አንዳንድ ጥያቄዎች የተወሰነ ችግር ቢስተዋልባቸውም። ነገር ግን በሁለቱም መማሪያ መፅሀፎች ውስጥ የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነትን የሚያሳዩ ክንውኖች አልተካተቱም። ይህም ሁለቱም መፅሀፎች በዚህ ረገድ ያለባቸውን ድክመት ያሳያል። እንዲሁም የ7ኛ ክፍል መፅሀፍ በንበት ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የፍቺ ለውጥ የሚመለከቱ ክንውኖችንም አላካተተም። ጠቅለል አድርገን ስናው ግን መፅሀፎቹ በፍቺ ዝምድና አቀራረብ ረገድ የተወሰነ ድክመት ቢኖርባቸውም ግን አቀራረባቸው የተሻለና በበጎ ጎኑ ሊነሳ የሚችል ሆኖ ተገኝቷል።

4.5.3 የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ንዑስ ክፍል ስር የተተኳሪ መፅሀፎቹ ለቃላት እርባታና ምስረታ የሰጡትን ትኩረትና የአቀራረቡን ተገቢነት ለማየት ተሞክሯል። በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.3 እንደተገለፀው ቃላትን የሚረቡበትንና የሚመሰረቱበትን ሂደት በሚያሳይ

መንገድ ማቅረብ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት በሚገጥሟቸው ጊዜ የቃላቱን ውስጣዊ መዋቅር በመፈተሽ ፍቻቸውን ለመረዳት የሚያስችሉ ፍንጮችን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

ከዚህ አኳያ የቃላት እርባታና ምስረታን አቀረረቦች በተመለከተ በተተኳሪ መጽሀፎቹ ላይ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል።

4.5.3.1 የ7ኛ ክፍል መጽሀፍ የቃላት እርባታና ምስረታ ስርዓት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

የ7ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላትን እርባታና ምስረታ በተመለከተ የሚጀምረው ገና ከመግቢያ መጽሀፉ መጀመሪያ ገፅ ላይ ነው። መግቢያ መፅሀፉ የሚጀምረው የቃላት አመሰራረት በሚል ርዕስ ነው። ይህም ተማሪዎች በአመቱ መጀመሪያ በቅድሚያ ስለቃላት አውቀው ከዚያ በኋላ ወደ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች እንዲያመሩ የታሰበ ይመስላል። ምክንያቱም ቃላት ለሌሎች የቋንቋ ክፍሎች የማወቂያ መንገድ/ መሰረቶች ናቸውና ነው።

የቃላትን አመሰራረት በተመለከተ በመግቢያ መፅሀፉ ላይ በገፅ 1 እንደተገለፀው የሚዳሰሱት ይዘቶች በዋና ቃል ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር ወይም በማርባት አዳዲስ ቃላትን መመስረት፣ ሁለት ቃላትን በማጣመር ቃላትን መመስረት፣ ምህፃረ ቃላትን መጠቀም እና ገላጮችን መጠቀም ናቸው። እዚህ ላይ ምህፃረ ቃላትን እና ገላጮችን መጠቀም ከቃላት አመሰራረት ጋር ምን እንዳገናኛቸው ባይታወቅም፣ በመግቢያ መፅሀፉ ውስጥ ግን ምህፃረ ቃላትን መጠቀም እና ገላጮችን መጠቀም የቃላት አመሰራረት በሚለው ይዘት ስር ተካተው እናገኛቸዋልን። ይህም የመፅሀፉን ችግር ሊያሳየን ይችላል። ምክንያቱም ቃላትን በማርባት አዳዲስ ቃላትን መመስረት እና ገላጮችን መጠቀም በአንድ ክፍል ውስጥ ሊካተቱ አይችሉም። ምክንያቱም ገላጮችን በውህድ አሀድ ውስጥ ስለተጠቀምን የሚመሰረት አዲስ ቃል የለምና ነው። ነገር ግን ሌሎችን ማለትም በዋና ቃል ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር ወይም በማርባት አዳዲስ ቃላትን መመስረት እና ሁለት ቃላትን በማጣመር ቃላትን መመስረት የሚሉትን በዝርዝር እናያቸዋለን።

ቅጥያዎችን በመጨመር ወይም በማርባት አዳዲስ ቃላት መመስረትን ለማስተማር በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች የቅድመና የድህረ አምድ ቅጥያዎችን በመጠቀምና

ቃላቱን በማርባት ላይ ያተኮሩ እና አራት ክንዋኔዎችን ያካተቱ ናቸው። በእነዚህ ይዘቶች በመለማመድ ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት እርባታና ምስረታ አውቀው በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል በሚያግዝ መልኩ ለማቅረብ ተሞክሯል። ምንም እንኳ የራሳቸው የሆነ ድክመት ቢስተዋልባቸውም። ይህንንም በአስረጅ እንየው።

አስረጅ6፡- ምሳሌ1 ጠበቀ፣ አጠበቀ፣ አስጠበቀ፣ ተጠበቀ፣ መተበቅ፣ (ዋናቃል)ጥብቅ፣ ይጠብቃል፣ ጠብቅ፣ ጠባቂ፣ ጠበቆች፣ ጠበቀው፣....

2. ከዚህ በታች ስድስት ዋና ቃላት ቀርበዋል። በምሳሌ አንድ መሰረት በእያንዳንዱ ዋና ቃል ላይ የቻላችሁትን ያህል ቅጥያዎች በመጨመርና በማርባት ሌላ ቃል መስርቱ።

ሀ. ለበሰ ሐ. መነዘረ ሠ. ደመደመ

ለ. ወለደ መ.ለመለመ ረ. በሰበሰ (7ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 1-2)

ከአስረጁ እንደምናየው ቃላትን በማርባትና ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ ለማዘዝ የቀረበ ይመስላል። በመሰረቱ የጥያቄው ትዕዛዝም ሆነ ጥያቄው ችግር ይስተዋልበታል። ማለትም የጥያቄው ትዕዛዝ የሚለው ተማሪዎች የቻሉትን ያህል ቅጥያዎችን በመጨመርና በማርባት ቃል እንዲመሰርቱ ነው። ነገር ግን ምን አይነት ቅጥያዎችን ቀጥለው ምን አይነት ቃል እንደሚመሰርቱ የሚገልፅ ነገር የለም። ይህም የግልፅነት ችግር ነው። ሌላው በጥያቄዎቹ ቃላት እና በምሳሌዎቹ መካከልም ልዩነት ይታያል። ማለትም በምሳሌው ውስጥ እንደ ዋና ቃል የተወሰደው ‹‹ጥብቅ›› የሚለው ቃል ሲሆን በጥያቄዎች ውስጥ ግን እንደ ዋና ቃል የተወሰዱት ከላይ ማየት እንደሚቻለው የቃላቱ ግሶች ናቸው። ይህም ሌላ ችግር ነው በመፅሀፉ ውስጥ የሚስተዋል። ምክንያቱም ተማሪዎችን ግራ የሚያጋቡና ለስህተት የሚዳርጉ ናቸውና ነው። ሌላው በጥያቄው ላይ የሚስተዋለው ችግር በግሶቹ መካከል ያለው ልዩነት ነው። ለምሳሌ በምሳሌው ከተሰጠው ‹‹ጥብቅ›› ከሚለው ቃል ‹‹ጠበቀው›› የሚል ቃል ተመስርቶ ይገኛል። በተመሳሳይ ተማሪዎች በጥያቄው ከተሰጣቸው ‹‹በሰበሰ›› ከሚለው ቃል በተመሳሳይ ለመመስረት ቢሞክሩ መመስረት አይችሉም። ስለዚህ ነገርም በመፅሀፉ ላይ የተገለፀ ነገር የለም። ይህም ተማሪዎችን የሚያወዛግብና ግራ የሚያጋባ ነው። ይህም የመፅሀፉን ችግር የበለጠ ያጎለዋል።

ሌላው በመፅሀፉ ውስጥ የቀረበው ቃላት መመስረቻ ዘዴ ጥመራ ነው። በመፅሀፉ ውስጥ ሁለት ቃላትን በማጣመር ድርብ ቃል መመስረት እንደሚቻል የሚያሳዩ ይዘቶች ቀርበዋል። ለዚህም ሁለት ክንውኖች በመፅሀፉ ውስጥ ቀረቡ ሲሆን ለተማሪዎች መነሻ የሚሆን ነገርም ቀርቧል። እስኪ ይህንንም በአስረጅ እንየው።

አስረጅ7፡- መመሪያ1፡ በ ሀ ምድብ የተዘረዘሩትን ከ ለ ምድብ ከተዘረዘሩት ጋር በማጣመር ድርብ ቃል መስርቱና አንዳንድ አረፍተነገር ስሩባቸው።

ሀ	ለ
---------1. ሰብል	ሀ. ጫማ
---------2. በትር	ለ. መቅ
---------3. እግር	ሐ. ቆርቁር
---------4. ቀትር	መ. ወንጌል
---------5. አፍ	ሠ. መንግስት
---------6. ግንድ	ረ. ቀላል

(7ኛ ክፍል መጽሀፍ፣ ገፅ 5)

ከአስረጁ እንደምናየው ተማሪዎች ድርብ ቃላትን ከሁለት ቃላት በማጣመር እንዲመሰርቱ እና በመሰረቱት ቃል ላይም ዓረፍተነገር እንዲሰሩ ያዝዛሉ። ይህም የተማሪዎችን ቃላት ብቃት አቅም ከማጎልበት አንፃር ድርሻው የጎላ ነው። ነገር ግን በዚህ ጥያቄ ላይም የተወሰነ ችግር ይስተዋላል። ይህም በ ‹‹ሀ›› ስር ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል ‹‹አፍ›› የሚለው ቃል በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት ቃላት የሚጣመረው ቃል የለም። እንዲሁም በ ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩትም ‹‹ጫማ›› የሚለው ቃል በ ‹‹ሀ›› ስር ከተዘረዘሩት የሚጣመረው ቃል የለም። ይህም ጥያቄዎቹ ሲወጡ ለቃላት ምርጫው የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያመላክታል።

ሌላው ከዚህ ከቃላት ምስረታ ጋር የተያያዘው ጉዳይ የቃላት የቅርፅ ጉዳይ ነው። በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥም የቃላት ቅርፅን በመለወጥ ቃላትን እንዲመሰርቱ የሚያዝዝ ጥያቄ ቀርቧል። በአስረጅ ስናየውም፤

አስረጅ8፡- በምሳሌው መሰረት የቃላቱን ቅርፅ ከለወጣችሁ በኋላ በተለወጡት ቃላት አንዳንድ ዓረፍተነገር ስሩባቸው።

ምሳሌ፡ ቀይ ቀያይ

አበበ ቀያይ ደሮዎች ገዛ።

ሀ. ነጭ ሐ. ደግ ሠ. ሠፊ

ለ. ቂል መ. ረጅም ረ. ጥቁር

(7ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 3)

ከአስረጁ እንደምናየው ቃላትን ቅርፃቸውን በመለወጥ ሌላ ቃል ማርባት እንደሚቻል ለተማሪዎች ለማስገንዘብ ተብሎ የገባ ይመስላል። ነገር ግን እንደላይኛዎቹ ጥያቄዎች ሁሉ በዚህ ጥያቄ ላይም የተወሰነ ችግር ይስተዋላል። ይህም በጥያቄዎቹ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ አንዱ ማለትም ‹‹ቂል›› የሚለው ቃል በምሳሌው መሰረት ቅርፁን በመቀየር ቃል መመስረት አይቻልም። ምናልባት ቃሉን በመደጋገም እንጅ። ይህም የተለየ ባህሪ ነው። ስለዚህ ነገር ግን በመፅሀፉ ላይ የተገለፀ ነገር የለም። ይህም ተማሪዎችን ለስህተት የሚዳርግ ነው።

ሌላው በመፅሀፉ ውስጥ ከቃላት ምስረታ ጋር ተያይዞ የተነሳው ጉዳይ ምህፃረ ቃላትን የሚመለከተው ነው። በመፅሀፉ ውስጥ ምህፃረ ቃላት እንደ ቃል መመስረቻ ቢጠቀሱም ብዙም ምህፃረ ቃላትን የተመለከቱ ይዘቶች በመፅሀፉ ውስጥ አልተካተቱም። ነገር ግን ምህጻረ ቃላትን ፈልገው እንዲያመጡና የምህፃረ ቃላትን ጠቀሜታ እንዲረዝሩ የሚያትቱ የተወሰኑ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እዚህ ላይ በመፅሀፉ የሚስተዋለው ስህተት ምህፃረ ቃላትን እንደ ቃል መመስረቻ መውሰዱ ነው። ይህንንም በአስረጅ እንየው።

አስረጅ9፡- በእንግሊዝኛ ቋንቋ ምህፃረ ቃላት ዋነኛ የአዳዲስ ቃላት መመስረቻ መንገዶች ናቸው። በአማርኛ ቋንቋ ግን ምህፃረ ቃላት እንደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ዋነኛ የቃላት መመስረቻ መንገድ አይደሉም። አባባሉን በመቃወም ወይም በመደገፍ ከልዩ ልዩ ምንጮች ሀሳብ አሰባስባችሁ ዝርዝር ማብራሪያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ከላይ ከቀረበው አስረጅ መረዳት እንደሚቻለው ምህፃረ ቃላት በአማርኛ ቋንቋ የቃል መመስረቻ ስለመሆን አለመሆናቸው እንጂ የሚያትተው ስለምህፃረ ቃላት ምንነት፣ አጠቃቀም፣ አመሰራረት ወዘተ አይደለም። ይህ ደግም ተማሪሪዎች በዚህ ዙሪ በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ይችላል። ምክንያቱም ሌላ ተመሳሳይ ይዘት በመፅሀፉ ውስጥ አልተካተተምና ነው።

4.5.3.2 የ8ኛን ክፍል መፅሀፍ የቃላት እርባታና ምስረታ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍም እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ የሚጀምረው የቃላት አመሰራረት በሚል ርዕስ ነው። በመማሪያ መፅሀፉ ገጽ 2 እንደተገለፀው ቃላት በተለያየ መንገድ ይመሰረታሉ። ከነዚህም መካከል በመፅሀፉ ውስጥ ሆሄያቱን (ድምፆችን) አቀናጅቶ ቃላትን መመስረት፣ ቃላት ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላት መመስረት እና አንድን ቃል ከሌላ ቃል ጋር በማጣመር አዲስ ቃል መመስረት እንደሚቻል ተዘርዝረዋል። በመፅሀፉ ውስጥም በእነዚህ መንገዶች ቃላት እንዲመሰረቱ የሚያደርጉ ክንውኖች ቀርበዋል። በመፅሀፉ ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ 43 ጥያቄዎች ውስጥ 15 ያህሉ ከቃላት አመሰራረት ጋር የተያያዙ ናቸው። እነዚህንም በዝርዝር በሰንጠረዥ እንመልከታቸው።

ሰንጠረዥ 7፡- የ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላት አመሰራረትን የተመለከቱ መረጃዎች

ተ.ቁ	የክንውኑ አይነት	የክንውኑ ብዛት	
		በቁጥር	በመቶኛ
1	ድምፆችን አቀናጅቶ ቃላት መመስረት	2	13.33%
2	ቃላት ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር አዲስ ቃል መመስረት	10	66.67%
3	አንድን ቃል ከሌላ ቃል ጋር በማጣመር አዲስ ቃል መመስረት	3	20%
	ድምር	15	100%

ከላይ ከሰንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው ሆሄያትን (ድምፆችን) አቀናጅቶ ቃላት መመስረትን የሚመለከቱ 2 (13.33%) ያህል ክንውኖች ቀርበዋል። ነገር ግን ከአጠቃላይ ክንውኖች ብዛት አንፃር ሲታዩ ቁጥራቸው ትንሽ ነው። ሌላው ቃላት ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር አዲስ ቃል መመስረትን የሚመለከቱ 10 (66.67%) ያህል ክንውኖች ቀርበዋል። እንዲሁም በማጣመር ማለትም አንድን ቃል ከሌላ ቃል ጋር በማጣመር አዲስ ቃል መመስረት የሚያስችሉ 3 (20%) ክንውኖችም በመፅሀፉ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ። ሌላው ከላይ በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ላይ እንዳየነው ሁሉ እዚህም የምናነሳው ጉዳይ አህፅሮተ ቃል ነው። አህፅሮተ ቃላት በምህፃረ ቃልነት ሲቀርቡ የሚይዙትን ቅርፅ ማወቁ የንግግርና የፅሁፉት ቅርፃቸውን ጠብቆ በትክክለኛው መንገድ በቃላቱ ለመገልገል ያስችላል። በዚህም በመፅሀፉ ውስጥ አህፅሮተ ቃላትን የሚመለከቱ 3 ይዘቶች (ክንውኖች) ተካተዋል። በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ግን እንደ 7ኛ ክፍል ምህፃረ ቃላት እንደ ቃል መመስረቻ አይወሰዱም። በይዘትነት ግን በመፅሀፉ ውስጥ ተካተዋል። ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን እንመልከት።

አስረጅ9፡- የሚከተሉት ምህፃረ ቃለት የሚወክሏቸውን ቃላት ፃፉ።

ምሳሌ፡ አህፅሮተ ቃል ሙሉ ቃል

አ.ብ.ክ.መ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

1. ባ.መ.ኮ 3. ጎ.ህ.ሳ.ኮ

2. ኢ.ሳ.ቴ.ኮ 4. ሥ.ት.ዝ.ጥ.ም.ተ

(8ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገጽ 21)

ከላይ ማየት እንደሚቻለው አህፅሮተ ቃላትን የሚመለከት ጥያቄ ቀርቧል። ሌሎች ጥያቄዎችም በመፅሀፎ ውስጥ ቀርበው ይገኛሉ።።። ይህም መፅሀፉ በዚህ ረገድ ያለውን ጥንካሬ ሊያሳየን ይችላል። ነገር ግን በዚህ ጥያቄ ላይ የሚስተዋል ችግር አለ። እርሱም አህፅሮተ ቃሉ ሲፃፍ ከመጨረሻው ፊደል በኋላ ያለችት ነጥብ ተትታለች። ከላይ ማየት እንደሚቻለው አ.ብ.ክ.መ በሚለው ምህፃረ ቃል ውስጥ ከ‹‹መ›› ቀጥሎ ነጥብ መኖር ነበረበት ነገር ግን የለችም። ይህም ተማሪዎች አስፈላጊ አይደለችም ወደሚል ድምዳሜ

ሊያደርሳቸው ይችላል። ይህም ተማሪዎችን ማላላት ነው። በነገራችን ላይ ‹‹አ.ብ.ክ.መ›› የሚለው ምህፃረ ቃል ሙሉ ቃሉ ሲፃፍ የሚሆነው ‹‹የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መ›› የሚል ነው። ስለዚህ ከ‹‹መ›› ቀጥሎ ነጥቧ መኖሯ የግድ ነው ማለት ነው ሙሉ ቃሉን በትክክል ለመፃፍ።

በአጠቃላይ የተተኳሪ መፃህፍቱን የቃላትን እርባታና ምስረታ የተመለከቱት መረጃዎች የሚያሳዩት ተተኳሪ መፃህፍቱ በዚህ ረገድ ድክመት እንደሚስተዋልባቸው ነው። በተለይም ሁለቱም መፅሀፎች በቃላት አመሰራረት ፣ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን እንዴት እንደሚመሰርቱ በሚሳዩ እና የቃላት መመስረቻ ዘዴዎችን በሚያስገነዝቡ ክንውኖች መጀመራቸው እንደጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ቢሆንም በመፅሀፎቹ በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የሚታየው ስህተት ግን ተማሪዎችን የሚያሳስት ነው። በተለይም በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላትን አመሰራረት እና የመመስረቻ ዘዴዎችን የተመለከቱት መረጃዎች የግልፅነት ችግር የሚስተዋልባቸውና ተማሪዎችን ሊያሳስቱ የሚችሉ ናቸው። በአንፃራዊነት የ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ግን ብዙ የጎላ ስህተት የማይስተዋልበትና ተማሪዎችንም የማያሳስት ነው። ምንም እንኳ ከቃላት መመስረቻ ዘዴዎች ውጭ በሆነው በምህፃረ ቃላት ጥያቄዎች ላይ የተወሰነ ችግር ቢስተዋልበትም።

4.5.4 የፊሊጠች፣ የጥምር ቃላትና የአያያዥ ቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና

በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.5 እንደተብራራው ብዙ የቋንቋ ብቃት ትምራምች የሚጠቁሙት ቃላት በትውስታ ማህደር የሚቀመጡት ነጠላ ሆነው ብቻ ሳይሆን የሀረግ አካል ሆነው ጭምር ነው (Nattinger 1988፣75)። እነዚህ ቃላዊ ሀረጎች በቀላሉ ሊታወሱ ከመቻላቸውም በላይ ተናጋሪው በነጠላ ቃል ላይ እንዳያተኩርና ከዚህ ይልቅ ሀሳቡን በዲስኩር መዋቅር ላይ እንዲያሳርፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። ይህንን የቃላዊ ሀረጎች ቁልፍ ሚና ተማሪዎች እንዲረዱትና በተገቢው ተግባቦታዊ አውድ እያፈለቁ እንዲጠቀሙ የሚያስችል በጥንቃቄ የተዋቀረ የቃላት ትምህርት መስጠት እንደሚያስፈልግ ይታወቃል።

ከዚህ ነጥብ አንፃር በተተኳሪ መፅሀፎቹ የቃላዊ ሀረጎች (የፊሊጦች፣ የጥምር ቃላትና የተለመዱ አገላለፆች) ትምህርት ስለቀረቡበት ሁኔታ ለአዘጋጆቹ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ እንደሌሎቹ ሁሉ ለዚህም የተለየ ትኩረት እንዳልሰጡትና በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥም በበቂ ሁኔታ ቀርበዋል ብለው እንደማያምኑ ነው። ምናልባትም በዚህ ረገድም መማሪያ መፅሀፎቹ ድክመት ሊስተዋልባቸው እንደሚችል ጠቁመዋል። ነገር ግን መማሪያ መፅሀፎቹን በተለይም የቃላት ትምህርት አቀራረቡን የተለየ ትኩረት እንዳልሰጡት ግን በአጠቃላይ የመፅሀፎቹ ዝግጅት ምንም እንኳ አጭር ጊዜ ቢሰጣቸውም ተገቢውን ትኩረት እንደሰጡ ገልፀዋል። ነገር ግን የቃላትን ትምህርት ነጥለው የተለየ ትኩረት እንዳልሰጡት ጠቁመዋል።

ከመማሪያ መፅሀፎቹ አዘጋጆቹ ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው የቃላዊ ሀረጎች በመጽሀፎቹ ውስጥ ምን ያህል ተካተዋል? እንዴትስ ቀርበዋል? የሚሉትን ነገሮች በተለየ ትኩረት ሰጥተው እንዳላዩት ነው። ይህም የመማሪያ መፅሀፎቹ ዝግጅት በዚህ ረገድ ድክመት እንዳለበት የሚያሳይ ነው።

ከቃላዊ ሀረጎች አቀራረብ ማለትም ፊሊጣዊ አነጋገሮች የቀረቡበት ስልት ፊሊጦችን ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችል መሆን አለመሆን፣ የጥምር ግሶችና የጥምር ስሞች አቀራረብ የቃላቱን ቅርፅና ፍቺ ለመረዳት አመቺ መሆን አለመሆንና የተለመዱ አገላለፆች አቀራረብ ቃላቱ በዲስኩር ውስጥ ያላቸውን አገልግሎት ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸውን በተመለከተ በተተኳሪ መፅሀፎች ውስጥ የቀረቡበትን ሁኔታ ለመመርመር ተሞክሯል። ይህንንም በዝርዝር ለማየት እንሞክር።

የ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ የፊሊጣዊ አነጋገሮች የቀረቡበት ስልት ፊሊጦቹን ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው የመማሪያ መፅሀፉ ፍተሻ እንዳውም ከነጭራሹ ፊሊጣዊ አነጋገሮችን የተመለከተ ምንም ይዘት በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አለመካተቱን ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህም በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.5 እንደተገለፀው ፊሊጣዊ አነጋገሮች በቋንቋው ውስጥ ካላቸው የተለየ ባህሪ እና ከሚሸከሙት የተለየ ፍቺ በተለይም የሚጣመሩት ለየብቻቸው ካላቸው ፍቺ የተለየና የማይገናኝ ፍቺ መያዛቸው እናም ይህን የሚያሳይ ይዘት በመፅሀፉ ውስጥ ምንም አለመካተቱ መፅሀፉ በዚህ ረገድ የሚስተዋልበትን

ድክመት ያሚያሳይ ይሆናል። በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በገፅ 5 ጥመራ በሚል ርዕስ በማጣመር ድርብ ቃል እንዲመሰርቱ የሚያዝዝ ጥያቄ ቀርቧል። ጥያቄውም አዛምድ ሲሆን አብዛኞቹ የሚመሰረቱት ድርብ ቃላት ናቸው። ነገር ግን በዚሁ መልመጃ ስር በ‹‹ሀ›› ረድፍ ‹‹ቀትር›› በ‹‹ለ›› ረድፍ ደግሞ ‹‹ቀላል›› የሚል ቃል ይገኛል። ይህም ‹‹ቀትረ-ቀላል›› የሚል ድርብ ቃል ለመመስረት የታሰበ ይመስላል። ነገር ግን ‹‹ቀትረ ቀላል›› የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አነጋገር ሆኖ እናገኘዋልን። መማሪያ መፅሀፉ ግን ድርብ ቃልንና ፈሊጣዊ አነጋገርን ቀላቅሎ ከማቅረብ ውጭ በመካከላቸው ምን አይነት ልዩነትና ተመሳሳይነት እንዳለ የሚያትተው ጉዳይ የለም። እንዳውም ፈሊጣዊ አነጋገር የሚል በርዕስ ደራጃ እንኳ አይገኝም።

በአጠቃላይ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በተመለከተ የ7ኛ ክፍል መፅሀፍ አቀራረብ ምንም የቀረበ ይዘት ስለሌለ ይህ ነው የማይባል ነው። በዚህ ረገድ መማሪያ መፅሀፉም ከፍተኛ ድክመት ያታይበታል።

የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍን የፈሊጣዊ አነጋገሮች ሁኔታ ያየን እንደሆነም ከ7ኛ ክፍሉ መፅሀፍ የተለየ አይደለም። በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን የተመለከቱ ይዘቶች በመፅሀፉ ውስጥ አልተካተቱም። እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም ስለድርብ ቃላት ለማስተማር የተካተቱት ይዘቶች ውስጥ አንዳንድ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ልናገኝ እንችል ይሆናል። ነገር ግን የቀረቡት ድርብ ቃልን ለማስተማር ስለሆነ ተማሪዎችም የሚወስዷቸው እንደ ድርብ ቃል ነው።

ሌላው እዚህ የሚነሳው ጉዳይ በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የጥምር ቃላት አቀራረብን የተመለከተው ጉዳይ ነው። በዚህም የ7ኛ ክፍል መፅሀፍን የጥምር ግሶችና የጥምር ስሞች አቀራረብ የቃላቱን ቅርፅና ፍቺ ለመረዳት አመቺ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል። በተካሄደው ፍተሻም በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ጥመራ የሚል ርዕስ ራሱን ችሎ በገፅ 5 ውስጥ ይገኛል። በስሩም የተለያዩ ክንውኖችን አካቷል። ክንውኖችም የሚያገዘቡት በአዛምድ መልክ የቀረቡ ስለሆኑ በማዛመድ ድርብ ቃል እንዲመሰርቱና በመሰረቱት ቃል ዓረፍተነገር እንዲሰሩ ነው። ሁሉም ክንውኖች ተመሳሳይ ናቸው። የሚጣመሩት ቃላት ስሞች ወይም ሌላ የቃል ክፍል ይሁኑ በመመሪያው ላይ

የተገለፀ ነገር የለም። እንዲሁ በጥመራ ቃል እንዲመሰርቱ ያዝዛል እንጅ። እስኪ በአስረጅ እንየው።

አስረጅ10፦ በ ‹‹ሀ›› ምድብ የተዘረዘሩትን በ ‹‹ለ›› ምድብ ከተዘረዘሩት ጋር በማጣመር ድርብ ቃል መስርቱና አንዳንድ ዓረፍተነገር ስሩባቸው።

ሀ	ለ
----------1. ምግብ	ሀ. ደራሽ
----------2. አየር	ለ. ጣቢያ
----------3. ወዶ	ሐ. ድስት
----------4. ፈጥኖ	መ. ቤት
----------5. ብረት	ሠ. ወለድ
----------6. ፖሊስ	ረ. ገብ

(7ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 6)

ከላይ ከአስረጁ ማየት እንደሚቻለው ጥያቄዉ ተማሪዎች ድርብ ቃል እንዲመሰርቱና በድርብ ቃሉም አረፍተነገር እንዲሰሩበት ያዝዛል። ይህም ድርብ ቃላቱን ከመጠቀም አንፃር ተማሪዎችን ሊያለማምዳቸው ይችላል። ነገር ግን በመፅሀፉ ውስጥ ስለ ጥምር ስሞችና ጥምር ግሶች በዝርዝርና በተናጥል የሚለው ነገር የለም። በእርግጥ በገፅ 6 ‹‹በመልመጃ አንድ መመሪያ አንድና ሁለትን ስትሰሩ በጥመራ ያስተዋላችኋቸውን አብይት ነጥቦች ዘርዝራችሁ አስረዱ።›› የሚል ጥያቄ ቀርቧል። ምናልባት በዚህም ተማሪዎች ምንን ከምን አጣምረው ምን እንደመሰረቱ፣ በጥመራ ጊዜ ቅጥያ መኖር አለመኖሩን ወዘተ ሊዘረዝሩ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን መታሰብ ያለበት ይህ ክንውን ተማሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው ዘርዘር አድርጎ በግልፅ የማያስቀምጥ መሆኑ ነው። ይህም ተማሪዎችን ግራ ሊያጋባቸው ይችላል።

በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም ቢሆን የጥምር ግሶችና የጥምር ስሞች አቀራረብ የቃላቱን ቅርፅና ፍቺ ለመረዳት አመቺ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ በተካሄደው የሰነድ ፍተሻ እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ ጥምር ስም ጥምር ግስ የሚል ነገር በተናጥል አለመቅረቡ ተረጋግጧል። ነገር ግን ተማሪዎች በጥመራ ቃላትን እንዲመሰርቱ በአዛምድ መልክ ክንውን ተሰጥቷቸዋል። በይዘቱም 7ኛ ክፍል ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ ነው። የተለየና እያደገ፣ እየሰፋ የሄደ ነገር የለም። እንዳውም 7ኛ ክፍል 3 ክንውኖች ስለቀረቡ የተሻለ ሽፋን ተሰጥቶታል ማለት ይቻላል። በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ግን ጥመራ የሚል ርዕስ ቢኖርም የተሰጠው ክንውን ከገፅ 5-6 ያለው አንድ ብቻ ነው። እርሱም 7ኛ ክፍል ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ ነው። በዚህም መፅሀፉ በዚህ ረገድ ብዙም ትኩረት እንዳልሰጠው መገንዘብ ይቻላል።

ሌላው የቃላዊ ሀረጎች ትምህርትን የሚመለከተው ጉዳይ በተተኳሪ መፅሀፎቹ ውስጥ የተለመዱ አገላለፆች (አያያዥ ቃላት) አገልግሎታቸውን ለመረዳትና ቃላቱን በንግግርም ሆነ በፅሁፍ እያስታወሱ ለመጠቀም የሚያስችሉ መሆን አለመሆናቸው ነው። በዚህም በተተኳሪ መፅሀፎቹ ውስጥ አያያዥ ቃላትን የተመለከቱ ይዘቶች አለመካተታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ አያያዥ ቃላትን የተመለከቱ ይዘቶች የሉም። ይህም መፅሀፎቹ በዚህ ረግድ ምንም እንዳልሰሩ የሚያሳይ ነው።

በአጠቃላይ በተተኳሪ መፅሀፎቹ የቃላዊ ሀረጎች ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻና ከአዘጋጆቹ የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው ተተኳሪ መፅሀፎቹ በዚህ ረገድ ክፍተት እንዳለባቸው ነው። በተለይም ተተኳሪ መፅሀፎቹ ስለፈሊጣዊ አነጋገሮችና ስለ አያያዥ ቃላት ምንም አለማለታቸው እንደ ትልቅ ድክመት ሊታይ ይችላል። እንዲሁም በመጠኑም ቢሆን ስለጥምር ቃላት ቢቀርብም እሱም ቢሆን የአቀራረብ ችግር ይስተዋልበታል።

4.5.5 ቃላት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.6 እንደተገለጸው ተማሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች የተረዷቸውን ቃላት አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ ውስጥ የሚጠቀሙበት የቅበላ

እውቀታቸውን ተጠቅመው ነው። ስለዚህ ቃላትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ተማሪዎች የተግባቡት አቅም መጠን ሚዛኑን በጠበቀ የቃላት ትምህርት ክንውን መታገዝ ይኖርበታል። የተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎች መዳበርም ከቃላት ውጭ የሚታሰብ አይደለም። ስለዚህ የቃላት ትምህርት ህይወት የሚኖረው ቃላት በተናጥል ሳይሆን ለመረዳትና ለመጠቀም በሚያስችሉ አውዶች ውስጥ መቅረብ ሲችሉ ነው። በሌላ አገላለፅ መረዳት በማዳመጥና በማንበብ፣ መጠቀም ደግሞ በመናገርና በመፃፍ የሚገለፁ ክሂሎች ናቸው። ተማሪዎች ቃላትን የመረዳት ችሎታቸውን የሚያዳብሩት አቀባይ ክሂሎችን ተጠቅመው ነው። ለዚህ ደግሞ አዳዲስ ቃላት ከሌሎች ጋር አብረው የሚገኙበት ውህድ አሀድ እንዲያዳምጡና እንዲያነቡ ማድረግና አስቀድሞ በተቀመጠላቸው ተግባር መሰረት ተፈላጊውንና የማይፈለገውን መረጃ እንዲለዩ መደረግ አለበት። ከዚህ አንፃር በተተኪ መፅሀፎች የቃላት ትምህርቶቹ ከክሂሎች ጋር ተጣምረው የቀረቡበትን ሁኔታ ለማወቅ የመማሪያ መፅሀፎቹ አዘጋጆች ተጠይቀው ምላሽ ሰጥተዋል።

በዚህም የመማሪያ መፅሀፎቹ አዘጋጆች የቃላት ትምህርቶች በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ ከየትኞቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር በብዛት ተጣምረው እንደቀረቡ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ እንደሌሎቹ ጥያቄዎች ሁሉ ለዚህ ጥያቄም መፅሀፎቹን ሲያዘጋጁ የተለየ ትኩረት እንዳልሰጡት ገልፀው፤ ነገር ግን በመፅሀፎቹ ውስጥ በአብዛኛው ከአንብቦ መረዳትና ከመፃፍ ኪሂሎች ጋር ተጣምረው እንደቀረቡ ገልጸዋል። በተለይም ብዙዎቹ የቃላት ትምህርቶች ከምንባብ የወጡ በመሆናቸው የቃላት ትምህርቱ ከአንብቦ መረዳት (ከንባብ ክሂል) ጋር አብረው እንደቀረቡ አስረድተዋል።

ከአዘጋጆቹ ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው በመፅሀፎቹ ውስጥ የቃላት ትምህርቱን ከሁሉም ክሂሎች ጋር አጣምሮ ለማቅረብ የተለየ ትኩረት እንዳልተሰጠው እና በመፅሀፎቹ ውስጥም የቃላት ትምህርቶች ከክሂሎች ውስጥ ከንባብ ክሂልና ከመፃፍ ክሂል ጋር ብቻ ተጣምረው መቅረባቸውን ነው። ነገር ግን ከመናገርና ከማዳመጥ ክሂል ጋር እንዳልቀረቡ ያሳያል።

ሌላው ቃላት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት በተመለከተ በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የቀረቡበትን ሁኔታ ለማወቅ በተካሄደው የሰነድ ፍተሻ በአጠቃላይ በ7ኛ ክፍል

መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት 25 ክንውኖች 18 ያህሉ ከክሂሎች ጋር ተጣምረው ቀርበዋል። ይህንንም በዝርዝር እንመልከተው።

ሰንጠረዥ 8፡- በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህረቶች ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት የተመለከቱ መረጃዎች ተንተና

ተ.ቁ	የክሂሎችና የቃላት ትምህርቱ ጥምረት	የክንዋኔዎች ብዛት	
		በቁጥር	በመቶኛ
1	የቃላት ትምህርቶቹ ከማዳመጥ ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	1	5.56%
2	የቃላት ትምህርቶቹ ከንግግር ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	1	5.56%
3	የቃላት ትምህረቶቹ ከአንብቦ መረዳት ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	10	55.55%
4	የቃላት ትምህርቶቹ ከፅህፈት ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	6	33.33%
ድምር		18	100%

ከላይ ከሰንጠረዥ 8 መረዳት እንደሚቻለው በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ከቀረቡት ክንውኖች ውስጥ ከክሂሎች ጋር የቀረቡት ከሁሉም ክሂሎች ጋር በእኩል መጠን ተቀናጅተው አለመቅረባቸውን ነው። በዚህም ከማዳመጥ ክሂል ጋር አንድ ክንውን ብቻ የቀረበ ሲሆን ከንግግር ክሂል ጋርም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲነጋገሩበት የሚያዝዝ ክንውን አንድ ብቻ ነው። አብዛኞቹ የቃላት ትምህርት ክንውኖች ከምንባብ የወጡ በመሆናቸው በመፅሀፉ ውስጥ 10 (55.55%) ክንውኖች ከአንብቦ መረዳት ጋር አብረው የቀረቡ ናቸው። እንዲሁም 6 (33.33%) ክንውኖች ደግሞ ከፅህፈት ክሂል ጋር አብረው የቀረቡ ወይም ተማሪዎች በፅሁፍ እንዲያቀርቡ የሚጋብዙ አይነት ናቸው። በዚህም በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አብዛኞቹ የቃላት ትምህርት ክንውኖች ከአንብቦ መረዳትና ከፅህፈት ክሂል ጋር

ተጣምረው የቀረቡ ናቸው። በአንዳሩ ግን ከንግግርና ከማዳመጥ ክሂል ጋር ደግሞ ብዙም አብረው አልቀረቡም። ይህም ከአዘጋጆቹ ምላሽ ጋር የሚጣጣም ነው።

ሌላው አንዳንድ ክንውኖች ደግሞ ከሁለት ክሂሎች ጋር በቅንጅት ቀርበው በመፅሀፉ ውስጥ እናገኛለን። ማለትም በአንድ ጊዜ ተማሪዎችን እንዲያነቡና እንዲፅፉ የሚጋብዙ አይነት ሆነው የቀረቡ አሉ ለማለት ነው። ይህንንም በአስረጅ እንየው።

አስረጅ11፡- ከዚህ በታች አስር ዓ.ነገሮች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ዓ.ነገር ተስማሚ የሆነውን ቃል ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በመምረጥ አሟልታችሁ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ።

1. ፋጡማ አውሮፕላን---------ናት።

   ሀ. በራሪ ለ. አብራሪ ሐ. መብረር መ. በረሮ

2. ልጆች መዝሙር----------ይወዳሉ።

   ሀ. ዘመሩ ለ አዝምሮ ሐ. መዘመር መ. ዝማሬ

3. የኢትየጵያ ህዝቦች የኑሮ ደረጃቸውን የሚያሻሽሉት ----------ብቻ ነው።

   ሀ. ሰርቶ ለ. መስራት ሐ. ስራ መ. ሲሰሩ ወዘተ...

(7ኛ ክፍል መጽሀፍ፣ ገፅ 3-4)

ከላይ ከምሳሌው ማየት እንደሚቻለው መፅሀፉ ተማሪዎችን እንዲፅፉና እንዲያነቡ የሚያደርግ ትዕዛዝ አለው።

በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥም የቃላት ትምህርቶች ከክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ በመፅሀፉ ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ 43 የቃላት ክንውኖች ውስጥ 25 ያህሉ ከክሂሎች ጋር ተጣምረው ቀርበዋል። እነዚህ ክንውኖችም ተጣምረው የቀረቡት ከንባብና ከፅሀፈት ክሂሎች ጋር ብቻ ነው። ይህንንም እስኪ በዝርዝር እንየው፤

ሰንጠረዥ 9፡- በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት ትምህርቶች መካከል ከክሂሎች ጋር ያላቸውን ጥምረት የተመለከቱ መረጃዎች

ተ.ቁ	የክሂሎችና የቃላት ትምህርቱ ጥምረት	የክንዋኔዎች ብዛት	
		በቁጥር	በመቶኛ
1	የቃላት ትምህርቶቹ ከማዳመጥ ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	--	--
2	የቃላት ትምህርቶቹ ከንግግረ ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	--	--
3	የቃላት ትምህርቶቹ ከአንብቦ መረዳት ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	12	48%
4	የቃላት ትምህርቶቹ ከፅህፈት ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ	13	52%
ድምር		25	100%

ከላይ ከሰንጠረዥ 9 ማየት እንደሚቻለው በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ የቃላት ትምህርት ክንውኖች መካከል 25 (58.13%) ያህሉ ከክሂሎች ጋር በጥምረት ቀርበዋል። ከነዚህም ውስጥ 12 (48%) ያህሉ ከአንብቦ መረዳት ጋር የቀረቡ ሲሆን ሌሎቹ 13 (52%) ያህሉ ደግሞ ከፅህፈት ክሂል ጋር አብረው ቀርበዋል። ነገር ግን በመፅሀፉ ውስጥ ከንግግርና ከማዳመጥ ክሂል ጋር አብሮ የቀረበ የቃላት ትምህርት የለም። ይህም መፅሀፉ በዚህ ረገድ ያለበትን ድክመት ሊያሳይ ይችላል።

ሌላው በተተኳሪ መፅሀፎቹ ውስጥ የቃላት ክንውኖች ተጣምረው የቀረቡት ከስነልሳን ጋር ነው። በሁለቱም መማሪያ መፅሀፎች ውስጥ የቃላት አመሰራረት፣ እርባታን፣ ቅጥያዎችን፣ ወዘተ የሚመለከቱ ክንውኖች ይገኛሉ። ይህም የቃላት ትምህርቶቹ ከስነልሳን ጋር ተጣምረው መቅረባቸውን ያሳየናል።

በአጠቃላይ በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ ከክሂሎች ጋር ተጣምረው ከቀረቡት ክንውኖች ውስጥ አብዛኞቹ ከፅህፈትና ከአንብቦ መረዳት ጋር ብቻ ተጣምረው የቀረቡ መሆናቸውን ከአዘጋጆች ምላሽና ከሰነድ ፍተሻው በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከንግግርና ከማዳመጥ ክሂል ጋር ግን ብዙም ቀርበው አይታዩም። ይህም እነEyraud (2000፣2) ‹‹አብዛኛው የቃላት እውቀት የሚጨበጠው በንባብ፣ በማዳመጥ፣ በውይይት፣ ወዘተ ነው›› በማለት ከገለፁት ሀሳብ ጋር የሚስማማ አይደለም።

4.5.6 የቃላት ትምህርቱን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በመማር ሁኔታ ውስጥ የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ትምህርት የማንኛውም መርሀ ትምህርት ዋንኛ አካል መሆን እንዳለበት Gairns እና Redman (1986፣81) ይገልፃሉ። በመማሪያ መፃህፍት የሚካተት መዝገበ ቃላትን የተመለከተ ትምህርት ዋና ትኩረት የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብን በማለማመድ ላይ ማረፍ ይኖርበታል። ይህ በተራው አዳዲስ ቃላትን ከአገባባቸው መተንበይ በማይቻልበት ሁኔታ፣ መዝገበ ቃላትን ለመጠቀምና አዲሶቹ ቃላት በተለያዩ አገባቦች የሚይዙትን የተለያየ ፍቺ ለመረዳት ያስችላል።

ከዚህ አንፃር ተተኳሪ መፅሀፎቹ የሚገኙበትን ሁኔታ ለማወቅ በተካሄደው የሰነድ ፍተሻ በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ መዝገበ ቃላትን የሚመለከት ጥያቄ የቀረበው አንድ ብቻ ነው። እርሱም፡-

አስረጅ12፡- ከመዝገበ ቃላት ወይም ሰው ጠይቃችሁ ወይም የፈለጋችሁትን አስር የአማርኛ ቃላት መርጣችሁ በሁለት ዓ.ነገር ውስጥ ሲገቡ የተለያዩ ፍቺዎችን እንዲሰጡ አድርጋችሁ ዓ.ነገር ስሩባቸው። የሚለው ነው።

(7ኛ ክፍል መጽሀፍ፣ ገፅ 13)

ይዘቱ የገባው የቃላቱን ፍቺ ለማስተማር ታስቦ ነው። ከጥያቄው መረዳት እንደሚቻለውም ለተማሪዎች አማራጮችን ስለሚሰጥ ማለትም ሰው መጠየቅ፣ መዝገበ ቃላት ላይ መፈለግ፣ አልያም የፈለጉትን እንዲያመጡ ስለሚያዝዝ መዝገበ ቃላት እንዲጠቀሙ የመገፋፋት ሀይሉ ዝቅተኛ ነው። እንዲሁም በመፅሀፉ ውስጥም ሌሎች መዝገበ ቃላትን የሚመለከቱ ክንውኖች የሉም።

በ8ኛ ክፍል መፅሀፍም እንዲሁ እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ መዝገበ ቃላትን በሚመለከት የቀረበው ክንውን አንድ ብቻ ነው። ይዘቱም እንደ 7ኛ ክፍል ሁሉ ፍቺን ለማስተማር የቀረበ ክንውን ነው። ክንውኑም፡-

አስረጅ13፡- የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ ወይም ሰው ጠይቃችሁ ፅፋችሁ አምጡ፡፡

ቆቅ፣ ሐር፣ በለስ፣ ሚዳቋ፣ ምስጥ፣ ዝንጅብል፣ መረቅ፣ ሜንጦ የሚሉት ናቸው፡፡

(8ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 29)

ከክንውኑ ማየት እንደሚቻለው ክንውኑ የተካተተው ትርጉምን ለማስተማር ታስቦ ነው፡፡ ነገር ግን በክንውኑ እንደ 7ኛ ክፍሉ ሁሉ ተማሪዎች የቃላቱን ትርጉም ለማወቅ መዝገበ ቃላቱን እንዲያዩ የማዘዙ ነገር ልል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በመፅሀፉ ውስጥ ሌሎች መዝገበ ቃላትን የመመለከቱ ይዘቶች አልተካተቱም፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ምርመራ የተገኘው መረጃ እንደሚያረጋግጠው በተተኳሪ መፅሀፎቹ ውስጥ ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን እንዲጠቀሙ የሚገፋፉና አጠቃቀሙን የሚያለማምዱ መልመጃዎች በሚፈለገው መጠንና አይነት አለመካተታቸውን ነው፡፡

4.5.7 የመልመጃ መመሪያዎችና ምሳሌዎችን ግልፅነት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

የቃላት ትምህርቱ ውጤታማ የሚሆነው በወጉ በተሰናዱ የቃላት መልመጃዎች አማካኝነት ሲሆን መልመጃዎቹ በተለያየ መንገድ የተቀረፁ፣ በተገቢ ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች የተደገፉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ Eyraud (2000፣3) በሚገልፀው መሰረት የቃላት መልመጃ ሲዘጋጅና መመሪያ ሲቀረፅለት መልመጃው ያተኮረበት የቃላት ትምህርት ይዘት፣ ያንን ይዘት ለተማሪዎች ለማቅረብ በምርምር የተደገፈውን ስልት መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መፅሀፎቹ ውስጥ የቃላት ትምህርቱ ክንውኖች መመሪያዎች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ በተካሄደው የሰነድ ፍተሻ በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ብዙም የምሳሌና የመመሪያ ግልፅነት ችግር የሚስተዋልባቸው ጥያቄዎች (ክንውኖች) የሉም፡፡ ነግር ግን የተወሰኑ ክንውኖች ይህ ችግር ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለአብነት ያህልም በገፅ 10 ላይ የቀረበውን እንመልከተው፡፡

አስረጅ14፡- ከዚህ በታች በምንባቡ መሰረት የሚመለሱ የቃል/የሀረግ ፍቺ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የቃላቱ /ሀረጋቱ በመጀመሪያ/ በምንባቡ መሰረት/ ተመሳሳይ/ ፍቺ ፈለጉላቸው። ቀጥሎ ተቃራኒ ፍቺ ፈለጉላቸው።

ምሳሌ፡- <u>አንድ የሚያደርጋቸው</u>፤ 1. የማያመሳስላቸው/ተመሳሳይ ፍቺ/

2. የሚያለያያቸው/ተቃራኒ ፍቺ/

ሀ. ያለልዩነት መ. ሊጣመመ

ለ. መርህ ሠ. ለፀዳ

ሐ. አካሄድ ረ. ትምክህት ወዘተ.

(7ኛ ክፍል መፅሀፍ፣ ገፅ 10)

ከላይ ከአስረጁ ማየት እንደሚቻለው የጥያቄው ትዕዛዙ ግልፅ አይደለም። በቅንፍ የተከፋፈለ ስለሆነና ቅንፉ የትኛውን ከየትኛው ለመለየት እንደገባ ለማወቅ ያስቸግራል። የግልፅነት ችግርም ይስተዋልበታል። እንዲሁም ወደ ምሳሌው ስንመጣ እርሱም ግልፅ አይደለም። በምሳሌው ላይ እንደምናየው ‹‹አንድ የሚያደርጋቸው›› የሚል ቃል ይሰጥና አንደኛ ብሎ ‹‹የማያመሳስላቸው /ተመሳሳይ ፍቺ/›› ይላል። ምን ለማለት እንደፈለገ ግን ግልፅ አይደለም። ሌላው በጥያቄዎቹ ውስጥም ‹‹ሊጣመመ›› እና ‹‹ለፀዳ›› የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። የነዚህን ቃላት ምንነትም ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ በዚህ ጥያቄ ትዕዛዙ፣ ምሳሌው እና ጥያቄው የግልፅነት ችግር ይስተዋልባቸዋል። የእንደዚህ አይነት ችግሮች በመፅሀፉ ውስጥ መኖር ደግሞ ተማሪዎችን ሊያደናግሩና ሊያሳስቱ ይችላሉ።

በ8ኛ ክፍል መጽሀፍም የቃላት ትምህርት ክንውኖች የመልመጃ መመሪያዎችና ምሳሌዎች ግልፅነትን በተመለከተ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል። በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ይህ ነው የሚባል የጎላ ችግር አይስተዋልም። ክንውኖቹ ግልፅ መመሪያና ምሳሌዎችን ያካተቱ ሆነው ተገኝተዋል። ይህም በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.5.8 እንደተገለፀው የቃላት ትምህርት ውጤታማ የሚሆነው በወጉ በተሰናዱ የቃላት መልመጃዎች አማካኝነት ሲሆን መልመጃዎቹ በተለያየ መንገድ ተቀርፀው፣ በተገቢ ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች የተደገፉ ሊሆኑ ይገባል፤ ከሚለው ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነው።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃልያና አስተያየት

5.1 ማጠቃልያ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማራ ክልል በመጀመሪያ ደረጃ ለሁለተኛ እርከን ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፅሀፎች የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀት እና አቀራረብ ቃላትን ከማስተማር አኳያ ያላቸውን ብቃት መፈተሽ ነው። በዚህ አብይ አላማ ስር የሚካተቱ አራት መሰረታዊ ጥያቄዎች ይገኛሉ።

1. የመፅሀፎቹን የቃላት ትምህርት ይዘት ለመምረጥ በስራ ላይ የዋሉት መስፈርቶች ተገቢ ናቸው ወይ?
2. የመማሪያ መፅሀፎቹ የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ለቃላት ትምህርት አደረጃጀት ምሁራን የሚጠቅሷቸውን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ተደራጅተዋል ወይ?
3. በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የቃላት ትምህርቶቹ ተገቢ የሆኑትን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶችን በመጠቀም ቀርበዋል ወይ?
4. በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች የቃላቱን የተለያዩ የፍቺ ገፅታዎች ለመቃኘትና ቃላቱን አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችል አቀራረብ አላቸው ወይ? የሚሉት ናቸው።

ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ያስገኙት ውጤት እንደሚያስረዳው በሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪ መፅሀፎች ውስጥ በጠንካራ ጎንነት የሚጠቀሱ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ስልቶች የተስተዋሉ ሲሆን የዚያኑ ያህል ደግሞ ድክመቶችም አልታጡም። በዚህ መሰረት ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶች ተጠቃለው ይቀርባሉ።

በአማራ ክልል በ7ኛ እና 8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሀፎች ውስጥ የቃላት ትምህርቶቹ ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች አንፃር ሲታዩ በቂ ቦታ እንደተሰጣቸው

በጥናቱ የተገኘው ውጤት ያመለክታል። በመፅሀፎቹ የተካተቱ የቃላት ትምህርቶችን ለመምረጥ ሁለት ዋና ዋና መስፈርቶች በጥቅም ላይ ውለዋል። አንደኛው አንድ ቃል ሰፊ አገልግሎት ሽፋንና ስርጭት ባይኖረውም እንኳ ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርብ ውህድ አሀድ ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሲገኝ የሚመረጥበት በቅርብ የመገኘት መስፈርት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የቃሉን ተስተማሪነት የተመለከተ ነው። ይኸውም አዘጋጆች በግል የማመዛዘን ችሎታቸው ላይ ተመርኩዘውም ቢሆን የቃሉን የክብደት ደረጃ በመገመት ይመጥናል ያሉትን የመረጡበት መስፈርት ነው። በአንባሩ የመስኩ ምሁራን ቋንቋን ለጠቅላላ ዓላማ ለማስተማር ታስቦ ለሚነደፍ መርሀ ግብር እንዲውሉ ከሰነዘሯቸው መስፈርቶች መካከል የቃላቱን ተዘወታሪነት በድግግሞሽ ጥናት የመለየት፣ የቃላቱን የፍቺ ሽፋን የማወቅ፣ የቃላቱን የስርጭት ባህሪ የመለየት፣ የተማሪዎችን ፍላጎት አሰሳ የማካሄድና በነዚህ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ ቃላትን የመምረጥ ጉዳይ ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጣቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በሌላ በኩል በሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪ መፅሀፎች የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች ለደረጃው ይመጠናሉ ተብለው ከተመረጡ ምንባቦች የወጡ ቢኖሩም የተስተማሪነት ደረጃቸው ከግምት ውስጥ እየገባ ከምንባቦቹ ውጭም ቃላት በይዘትነት እንደተመረጡ ታውቋል። ይህም ደግሞ ተገቢ አሰራር እንደሆነ ይታመናል።

የመፅሀፎቹን የቃላት ትምህርት አደረጃጀት በተመለከተም በአብዛኛው ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር፣ በአንድ ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸውና ስለቃላት የተወሰነ ግንዛቤ ማስጨበጥ ከመቻል አንፃር እንደተደራጁ፣ ነገር ግን ይህ በአጋጣሚ የሆነ እንጅ ቃላትን በመልመጃ መልክ ለማደራጀት አዘጋጆቹ ከመነሻው ይህ ነው የሚባል መስፈርት እንዳልተጠቀሙ በጥናቱ ተደርሶበታል። ነገር ግን ምሁራን ለቃላት መደራጃ እንደመስፈርት ከሚጠቅሷቸው ከሚኖራቸው የፍቺ ተዛምዶና ከቅርፅ አንፃር ማደራጀት ከሚሉት ነጥቦች አንፃር ሲታዩ ድክመት ይታይባቸዋል።

በቃላት ፍቺ ላይ ያተኮሩ የቃላት ትምህርቶችን አቀራረብ ስንመለከት፣ በመፅሀፎቹ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አብዛኞቹ በአውድ ተደግፈው ቀርበዋል። ቃላቱ ከቀረበላቸው አረፍተነገራዊ አውዶች በአብዛኛው የቃላትን ፍቺ በገቡበት ቦታ ለመገመት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች ይዘው ቀርበዋል። በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ ስለቃላት የተወሰነ

እውቀት ለማስጨበጥ ከቀረቡት የቃላት ክንውኖች ውጭ ሌሎች ግን በአውድ ተደግፈው መቅረባቸው ተረጋግጧል። ነገር ግን በመፅሀፎቹ ውስጥ አንዳንድ ስህተቶች ይስተዋላሉ። በተለይም በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ። ይህም አዘጋጆቹ እንደሚሉት የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያሳየናል።

ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ከማቅረብ አኳያ በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ በአዛምድ መልክ፣ አብሮ ተሰላፊ ቃላት አውድ ተኮር ሆነው ቀርበዋል። እንዲሁም የቃላትን ፍቺ በዐረፍተነገር እንዲያሳዩ የሚጠይቁ ክንውኖች መቅረባቸውም ተረጋግጧል። የቃላት ተመሳስሎና ተቃርኖ ዋነኛ ማቅረቢያ ስልት ቃላቱን በአውድ ማቅረብ ሆኖ ሳለ በየመልመጃው የሚዘመዱት ቃላትና ሀረጋት በ‹‹ሀ›› እና በ‹‹ለ›› ክፍል ሌጣቸውን ቀርበዋል። የቃላቱ ሌጣቸውን መቅረብ ደግሞ ተማሪዎቹ ቃላቱ በምን ዓይነት አገባብ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ እንደያዙ ለመረዳት ያስቸግራቸዋል። ከዚህም ሌላ የቃላት የከታች ተከታች የፍቺ ዝምድናን የተመለከተ ትምህርት በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ ከነአካቴው አልተካተተም።

በቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደት ላይ የተመረኮዘው ትምህርት በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ በመጀመሪያ ክፍላቸው አካባቢ መቅረቡ ተረጋግጧል። በዚህም በ8ኛ ክፍል መፅሀፍ የቃላትን አመሰራረት በተመለከተ ቃላት በቅጥያዎች፣ በጥመራ፣ በድምፆች ቅንጅት እንደሚመሰረቱ የሚያሳዩ መረጃዎች ቀርበዋል። አቀራረባቸውም በጠንካራ ጎኑ የሚጠቀስ ነው።

በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ግን የቃላት አመሰራረትን የሚመለከተው መረጃ የግልፅነት ችግርና ተማሪዎችን ለስህተት የሚዳርግ ሆኖ ተገኝቷል። በመረጃው እንደተገለፀውም ምህፃረ ቃላትንና ገላጭ ቃላትን መጠቀም እንደ ቃል መመስረቻ ይወስዳቸዋል። ይህም ተማሪዎችን ሊያሳስት የሚችል ነው። እንዲሁም በጥመራ ቃል እንዲመሰርቱ የቀረቡት ጥያቄዎች ላይም ችግር ይስተዋልባቸዋል።

የቃላዊ ሀረጎችን (ፈሊጦች፣ ጥምር ስሞች፣ ጥምር ግሶችና አያያዥ ቃላትን) በሚመለከትም በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ ፈሊጣዊ አነጋገሮችንና አያያዥ ቃላትን የተመለከተ ይዘት አልተካተተም። ይህም የመፅሀፎቹ እንደ ትልቅ ድክመት ሊቆጠር

ይችላል። እንዲሁም የጥምር ቃላት አቀራረብም ደክመት ያለበትና ግልፅነት የጎደለው እንዲሁም ለመረዳትና አፍልቆ ለመጠቀም በማያስችል ስልት መቅረባቸው ተረጋግጧል።

በሌላ በኩል የቃላት ትምህርቱ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በመጣመር የቀረቡበት ሁኔታ በሁለቱም መፅሀፎች ውስጥ ሚዘናዊ እንዳልሆነ ጥናቱ አሳይቷል። በዚህም ትምህርቱ በአብዛኛው ከአንብቦ መረዳትና ከፅህፈት ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡ ሲሆን በተለይ ከማዳመጥና ከንግግር ክሂሎች ጋር ተጣምረው የቀረቡበት ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ ነው። ከዚህም ሌላ ከቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች መካከል ተማሪዎች የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብን እንዲካኑ የሚያግዝ ትምህርት ማቅረብ አንዱ ሆኖ ሳለ በሁለቱም መፅሀፎች በመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ትምህርት ‹‹የለም›› ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ በጥናቱ ተደርሶበታል።

በመጨረሻም የቃላት ትምህርቱ የቀረቡባቸው መመሪያዎች ተገቢነትን በተመለከተው የጥናቱ ክፍል በሁለቱም መፅሀፎች አብዛኞቹ መመሪያዎች በተገቢ ማብራሪያዎችና ምሳሌዎች በመደገፍ ግልፅ ሆነው የተነደፉ ናቸው። ሆኖም በምሳሌ ያልተደገፉና ተገቢ ማብራሪያ የሚጎድላቸው ጥቂት መመሪያዎች በ7ኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ መኖራቸው በጥናቱ ተጠቁሟል። ከዚህ ጥናት አጠቃላይ ውጤት በመነሳትም አጥኝው ከዚህ በታች ያሉትን አስተያየቶች ሰንዝሯል።

5.2 አስተያየት

ከዚህ በላይ በማጠቃልያው የተገለፁትን የጥናቱን ውጤቶች መሰረት በማድረግ መቀጠል የሚገባቸው የመፅሀፎቹ ጠንካራ ጎኖች መኖራቸው ሳይዘነጋ ችግር በታየባቸው የመፅሀፎቹ የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ አጥኝው የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰንዝሯል።

- የቃላት መረጣው ሲካሄድ በተቻለ መጠን ቋንቋን ለጠቅላላ ዓላማ ለማስተማር ለሚነደፍ መርሀ ግብር እንዲውሉ በመስኩ ምሁራን ለተሰነዘሩት የቃላት መምረጫ መስፈርቶች ሁሉ ተገቢው ትኩረት ቢሰጥ፤
- የቃላት ትምህርት አደረጃጀቱን በተመለከተም ምንም እንኳ በመፅሀፎቹ ውስጥ ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር፣ በአንድ ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸውና

ስለቃላት የተወሰነ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ በመባላቸው የተደራጁ ቢሆንም ግን ምሁራን እንደሚሉት የፍቺ ገፅታቸውን፣ የቅርፃቸውን መመሳሰል ወዘተ ከግምት ያስገባ አደረጃጀትም ተግባራዊ ቢደረግ፤

- በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ በተለይም ፊሊጣዊ አነጋገሮችን፣ አያያዥ ቃላትን የተመለከቱ ይዘቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው በመማሪያ መፅሀፎቹ ውስጥ እንዲካተቱ ቢደረግ፤
- በመፅሀፎቹ ውስጥ ፍቺን እንዲያለማምዱ ቀርበው በአውድ ያልቀረቡ መልመጃዎች በአውድ ቢደገፉ፣ የፍቺ ተመሳስሎና ተቃርኖ የሚያለማምዱ በአዛምድ መልክ የቀረቡ ቃላትም ከምንባብ የተመረጡት በምንባቡ የሚገኙበት መሰመር ቢጠቆም (ላልተጠቆሙት)፣ ከምንባብ ውጭ የተመረጡት ደግሞ በ‹‹ሀ›› ክፍል የተዘረዘሩት ቃላት በአውድ እንዲቀርቡ ቢደረግ የመፅሀፎቹን የቃላት ፍቺ ትምህርት ያሻሽለዋል፡፡
- በመፅሀፎቹ ውስጥ የቃላት የክታች ተክታች የፍቺ ዝምድናን የሚያለማምዱ መልመጃዎች ተቀርፀው ቢካተቱ፤ የጥምር ቃላት ትምህርት ቃላቱን ለመረዳትና ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ ቢቀርቡ፤ የቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደት የተመረኮዙ መልመጃዎች ተማሪዎች የቅጥያዎቹን ተግባርና በቅጥያዎች መግባት ቃላቱ ያሳዩትን የቅርፅና የፍቺ ለውጥ ለመዳሰስ በሚችሉበት አኳኋን ቢቀርቡ፤
- በሁለቱም መፅሀፎች የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተጣምረው ቢቀርቡና በመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብ ላይ ያተኮሩ መልመጃዎች በጥራት ተቀርፀው ቢካተቱ፤

ዋቢ ፅሁፎች

ሞላ አፅብሃ። 2003። ‹‹በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና።›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፤ ተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።(ያልታተመ)

ሲሳይ ተበጀ። 1990። ‹‹በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት።›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።(ያልታተመ)

ተስፋ አበራ እና ማረው አለመ። 1993። ‹‹አማርኛ ቋንቋን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማስተማር ዘዴ።›› ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ለልዩ ዲግሪ ፕሮግራም የርቀት ትምህርት የተዘጋጀ።(ያልታተመ)

ትንሳኤ ብርሀኔ። 1988። ‹‹የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት።›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጲያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ስነዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።(ያልታተመ)

ባየ ይማም። 2000። *የአማርኛ ሰዋስው* (የተሻሻለ ሁለተኛ እትም)። አዲስ አበባ፤ እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማህበር።

አብይ ይመር። 1991። ‹‹የአማራው ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት ይዞታ ግምገማ።›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።(ያልታተመ)

አንበሴ በቀለ። 1993። ‹‹በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መፅሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና።›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም

ለኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነዕሁፍ ክፍል አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።(ያልታተመ)

የሸጥላ መንግስቱ። 1997። በ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቃላት ትምህርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ግምገማ።›› በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት።(ያልታተመ)

የኢትዮጲያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። 1993። *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ያለው እንዳወቀ። 1998ዓ.ም። *የምርምር መሰረታዊ መርሆች አተገባበር*። ባህርዳር፣ ባህርዳር ዩኑቨርሲቲ።

ዳኛቸው ወርቁ እና አምሳሉ አክሊሉ። 1993። *የአማርኛ ፊሊጦች (ሶስተኛ እትም)*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። 1990። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

Alderson, J.C, Clopham. C, and Wall. 1995. *Language test construction and evaluation*. Camberidge: Cambridge University Press.

Allen, V.F. 1983. *Techniques in teaching vocabulary*. Oxford; oxford university press

Anderson, A. and Tony Lynch. 1991. *Listening*. Oxford: OUP.

Atkins, J. Hailom, B. and Nuru, M. 1996. *Skill development methodology*(part2). Addis Abeba: Addis Abeba University Press.

Bauer, L. 1998. *Vocabulary*. London and New York; Routledge.

Biber, D. Conard, S. and Reppen, R. 1998. *Corpus linguistics; Investigating language structure and use*. Cambridge: Cambridge University Press.

Candlin, C. N. 1988. "preface" In Ronald Carter and Michael McCarthy(eds) *Vocabulary and language teaching.* New York: longman.

Carter, R. and McCarthy, M. 1988. *Vocabulary and language teaching.* New York: longman.

Cohen,L. and Lawrence,M. 1994. *Research methods in Education.* London/ New York; Routhledge.

Cumino, M. 1990. "The role of vocabulary in foreign language teaching." In Hill, D. and Holden, S. (eds). *Effective Teaching and Learning.* London: modern English publications. Vol 26, No. 4, pp83-89.

Cunningsworth, A. 1995. *Evaluating and selecting EFL teaching Materials.* Oxford: Heinemann International.

Curtis, M.E. and Longo, A.M. 2001. Teaching Vocabulary to Adolescents to Improve Comprehension. Reading Online, 5(4). Available; http;//www. Reading online. Org/articles/ art-index Asp? HREF- Curtis/ index htm.

Dubin, F. and Olshtain, E. 1986. *Course Design; Developing Programs and materials for language learning.* Cambridge: Cambridge University Press.

_____ 1992. *Course Design; Developing Programs and materials for language learning (6th ed.).* Cambridge: Cambridge University Press.

Elley, W. 1989. Tailoring the evolution to fit the context. In Johnson, R.(ed). *The second language curriculum.* Camdridge; Cambridge university press. Vol.21, No.2, pp.53-60.

Ellis, R. 1995. *Understanding Second language Acquisition.* Oxford: Oxford University Press.

Eyraud, K. 2000. "The word wall Approach: promoting L2 Vocabulary learning." *English Teaching Forum.* Vol. 38, No. 3, pp.1-11.

Gairns, R. and S. Redman. 1986. *Working with words; Aguide to Teaching and learning Vocabulary.* Cambridge:CUP.

Harmer, J. 1991. *The practice of English language teaching.* London: New York: Longman Group(UK) Ltd.

_____. 1993. *The practice of English Language Teaching.* London; Longman groups (UK) Limited.

_____. 1994. *The practice of English language teaching.* London: longman.

Hatch, E. and Brown, C. 1995. *Vocabulary, Semantics and language Education.* Cambridge: Cambridge University Press.

Hunt, A and Belgar D. 2002. Current Research and practice in Teaching Vocabulary. In Richards, J and Willy Renandya(eds). *Methodology in Language Teaching; An Anthology of current Practice.* Cambridge: Cambridge University Press. Vol.4, No.4, pp313-319.

Hutchinson, T. and Torres, E. 1994. "the Text book as agent of change" ELT Journal. Vol. 48, No. 4, pp. 315-328.

Joe, A. 1995. "The Value of retelling Activities to vocabulary." *Guidelines: A periodical for Classroom Language Teaching.* Vol. 17, No. 1, pp1-8.

Koul, L. 1993. *Methodology of Educational Research.* 2nd Rev. ed. New Delhi Vicas publishing house put. Ltd.

Lewis, M. 1993. *The lexical Approach.* London: Commercial Colour Press.

Lewis, M. and Hill, J. 1992. *Practical Technique for language teaching.* London: Commercial Colours Press.

Lowson, M. and Hogben, D. 1996. "The vocabulary Learning sterategies for Foreign Language students." *Language Learning Journal.* Vol. 16, No. 1, PP.1o1-135.

McCarthy, M. 1990. *Vocabulary.* Oxford: Oxford University Press.

McCarten, J. 2007. Teaching Vocabulary; Lesson from the Corpus lesson for the Classroom. www.cambridge.org.

Ming, T. 1993. "Innovative ways t Teach Vocabulary some practical Idea for the classroom Teacher." *Guidelines; A Periodical for Classroom teacher.* Vol. 19, No. 1, pp. 11-21.

Morgan, J. and Rinvlucri, M. 1986. *Vocabulary.* Oxford: OUP.

Morley, J. 1990. "Lexicography and language Learning." In Hill, D. and Susan Holden(eds). *Effective Teaching and learning.* London: Modern English Publications. Vol. 13, No. 4, pp34-37.

Nation, P. and Cody, J. 1988. "Vocabulary and reading." In Carter, R. and McCarthy, M. (eds). *Vocabulary and Language Teaching.* New York: Longman Group (UK) Limited.

Nation, P. 2000. Designing and Improving a language Course. English Teaching Forum. Vol. 38, No. 4, pp2-11. http://www.victoria.ac.nz/lals/staff/paulnation.aspx.

Nattinger, J. 1988. "Some Current Trends in Vocabulary Teaching." In Carter, R. and McCarthy, M. (eds). *Vocabulary and language Teaching.* New York: Longman Group (UK) Limited. Vol.32, No. 3, pp. 23-26.

Nattinger, J.R. and Decarrico, J.S. 1992. *Lexical phrases and language teaching.* Oxford: Oxford University Press.

Nunan, D. 1998. *Language teaching Methodoldgy: A text book for language teachers.* Edinberugh: Pearson Education Ltd.

_____ 1991. *Language Teaching Methodolgy: A text book for language teachers.* Edinberugh: Pearson Education Ltd.

Pikulski, J. and Templeton, S. 2004. Teaching an Developing vocabulary; Key to long-term Reading Sccess. http://www.eduplace.Com/state/author/pik_temp.pdf.

Rebert, A. 1985. *Dictionary of psychology.* London; penguin Books.

Richards, J.C. 2009. *Curriculum Development in Language Teaching(12th ed.)*. Cambridge: Cambridge University Press.

_____. 1985. *The context of language teaching.* Cambridge: CUP.

River, W. 1994. *Communicating Naturally in second language* (8th ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Scrivener, J. 1998. *Learning Teaching.* Oxford: Macmilan publishers Limited.Seal, B.D.1991. "Vocabulary learning teaching" In Celce- Murcia, M.(ed). *Teaching English as a second or foreign language*(2nd ed). Boston: Heinle and Heinle publisher.

Sinclair, J. McH and Renouf, A. 1988. "A Lexical Syllabus for language." In Carter, R. and McCarthy, M.(eds.) *Vocabulary and language teaching.* New York: Longman Group(UK) Limited. Vol.22, No.3, pp.67-69.

Simcock, M. 1993. "Developing Productive vocabulary using the ask and Answer Technique." *Guidelines: A periodical for classroom language teachers.* Vol. 15, No. 2, pp. 1-7.

Ur, P. 1996. *A Course in language teaching; practice and theory.* Cambridge: CUP.

Verspoor, M. and Wander Lowie. September 2003. "making sense of polysemous words." Language Learning Journal. Vol.53, No. 3, PP. 547-586.

Wallace, M. 1988. *Teaching vocabulary.* Oxford: Hieinmann Educational books Ltd.

Wilkins, A. 1982. *Linguistics in Language Teaching.* London: The English Language Book society and Edward Arnold (publishers) Ltd.

Ying, Y.S. 2001. "Acquiring Vocabulary Through a context Based Approach." English Teaching Forum. Vol. 39, No. 2, pp.18-21.

Yule, G. 1996. *The Study of Languages(2nd ed*). Cambridge: Cambridge University Press.

መዳዬ ቃላት

ቃሉ/ ሀረጉ በመገኛ ቋንቋው	የአማርኛ ፍቺው
Availability	በቅርብ መገኘት
Bilingual Dictionary	ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት
Binary Antonyms	ተፃራሪ/ የጥንድ ተቃርኖ
Collocations	አብሮ ተሰላፊ
Compounding	ጥመራ
Connotation	ፍካሬ
Conversances	የተገላቢጦሽ ተቃርኖ
Corpus	የውህድ አሀድ ስብስብ
Denotation	እማሬ
Derivation	ምስረታ
Directionality	ባለአቅጣጫ ተቃርኖ
Gradable Antonyms	ተደራጅ ተቃርኖ
Guessing Clues	ለመገመት የሚረዱን ፍንጮች
Hyponym	ተከታች
Inflection	እርባታ
Institutional Expressions	የተለመዱ አገላለፆች
Learnability	ተስተማሪነት
Linguistic Context	ስነልሳናዊ አውድ
Monolingual Dictionary	ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት
Personalized Groups	ግላዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ፍረጃ
Productive Vocabulary	ፍሉቅ ቃላት
Receptive Vocabulary	ኢ-ፍሉቅ ቃላት
Situational Context	ሁኔታዊ አውድ
Standard Monolingual Dictionary	ደረጃውን የጠበቀ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት
Super Ordinate	ከታች

አባሪዎች

አባሪ ‹‹ሀ››

አስረጅ 1

<u>የቃላት አመሰራረት</u>

በዚህ ምዕራፍ የምንማራቸው ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው።

5. በዋና ቃል ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር ወይም በማርባት አዳዲስ ቃላትን መመስረት፤
6. ሁለት ቃላትን በማጣመር ቃላትን መመስረት፤
7. ምህፃረ ቃላትን መጠቀም፤
8. ገላጮችን መጠቀም፤

ትምህርቱ በአጫጭር ገለፃዎች፣ በምሳሌዎችና በመልመጃዎች ይቀርባል።

አስረጅ 2

በ ‹‹ሀ›› ስር የተሰጡትን ቅጥያዎችን በ ‹‹ለ›› ስር ከተሠጡት ቃላት ላይ በመቀጠል የምትችሉትን ያህል ቃል መስርቱ።

<u>ሀ</u>	<u>ለ</u>	የሚመሰረት ቃል
5. -ነት	ሀ. ልጅ	----------
6. -ሽ	ለ. ሆድ	----------
7. -ኡ	ሐ. መስበር	----------
8. -ኣም	መ. ነገር	----------
9. -ኢያ	ሠ. ጠረቤዛ	----------
10.-ህ		----------

11.-ኧኛ ----------

12.-ዎች ----------

13.-ኣችን ----------

14. -ኣችሁ ----------

አስረጅ 3

ከዚህ ቀጥሎ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡- በቀለ የአባቱ ሀብት ተካፋይ ነው። /ድርሻውን የሚወስድ/

በቀለ የአባቱን ችግር ተካፋይ ነው። /ለችግር ደራሽ/

ሀ. ሸንኩርት ረከሰ / /

ለ. በሰራው መጥፎ ድርጊት ስሙ ረከሰ / /

ሐ. ፀሀይ ስትወጣ እመጣለሁ / /

መ. ተራራ ስትወጣ እመጣለሁ / /

ሠ. የበጉ ቆዳ በአራጁ ተገፈፈ / /

ረ. በሬዎቹን ሁሉ በሌባ ተገፈፈ / /

አስረጅ 4

ምንባቡን እንደገና በማስተዋል አንብቡና የሚከተሉት ቃላትና ሀረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍቺ/ አገባባዊ ትርጉም ግለፁ።

ሀ. ትግል ሠ. ቅኝ ተገዥነት ቀ. ባዶ እግር ነ. የውበት እሳቤ

ለ. ወጣት ረ. ዜማ እንዳጠና በ. ያልሰለጠነ ኘ. አቀንቃኝ

ሐ. አመለጥኩ ሰ. ትምህርት ቤት ቢከተኝ ተ. ቀላል ታሪክ የለውም ከ. አዘጋጅ

መ. ተወኝ ሸ. ሸማኔ ቸ. እኔን ያየህ ተቀጣ ኸ. ፕሮዲዩሰር

አስረጅ 5

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚጠብቁትን ሆሄ አውጥታችሁ ዓፉ። ሁለት ሁለት እየሆናችሁ አንዳችሁ ሆሄው ሲጠብቅ ቃሉ የሚኖረውን ትርጉም ሌሎቻችሁ ደግሞ ሆሄው ሳይጠብቅ ቃሉ የሚኖረውን ትርጉም ዓረፍተነገር እየሰራችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡ ቃል የሚጠብቅ ሆሄ ሲጠብቅ የሚኖረው ትርጉም ሲላላ የሚኖረው ትርጉም

አለ ‹‹ለ›› ካሳ በህይወት አለ። መፅሀፍ ማንበብ ጥሩ ነው አለ።

1.3 ስለ 3.3 በላ

1.4 ገና 3.4 ገላ

አስረጅ 6

መመሪያ፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹን በቡድን ሰርታችሁ በክፍል ውስጥ ተነጋገሩባቸው።

ምሳሌ1 ጠበቀ፣ አጠበቀ፣ አስጠበቀ፣ ተጠበቀ፣ መተበቅ፣ (ዋናቃል)ጥብቅ፣ ይጠብቃል፣ ጠብቅ፣ ጠባቂ፣ ጠበቆች፣ ጠበቀው፣....

2. ከዚህ በታች ስድስት ዋና ቃላት ቀርበዋል። በምሳሌ አንድ መሰረት በእያንዳንዱ ዋና ቃል ላይ የቻላችሁትን ያህል ቅጥያዎች በመጨመርና በማርባት ሌላ ቃል መስርቱ።

ሀ. ለበሰ ሐ. መነዘረ ሠ. ደመደመ

ለ. ወለደ መ.ለመለመ ረ. በሰበሰ

አስረጅ 7

መመሪያ1፡ በ ሀ ምድብ የተዘረዘሩትን ከ ለ ምድብ ከተዘረዘሩት ጋር በማጣመር ድርብ ቃል መስርቱና አንዳንድ አረፍተነገር ስሩባቸው።

ሀ	ለ
---------1. ሰብል	ሀ. ጫማ
---------2. በትር	ለ. መቅ
---------3. እግር	ሐ. ቆርቁር
---------4. ቀትር	መ. ወንጌል
---------5. አፍ	ሠ. መንግስት
---------6. ግንድ	ረ. ቀላል

አስረጅ 8

በምሳሌው መሰረት የቃላቱን ቅርፅ ከለወጣችሁ በኋላ በተለወጡት ቃላት አንዳንድ ዓረፍተነገር ስሩባቸው።

ምሳሌ፡ ቀይ ቀያይ

አበበ ቀያይ ደሮዎች ገዛ።

ሀ. ነጭ ሐ. ደግ ሠ. ሠፊ

ለ. ቂል መ. ረጅም ረ. ጥቁር

አስረጅ 9

የሚከተሉት ምህፃረ ቃለት የሚወክሏቸውን ቃላት ፃፉ።

ምሳሌ፡ አህፅሮተ ቃል ሙሉ ቃል

አ.ብ.ክ.መ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

3.ባ.መ.ኮ 3. ጎ.ህ.ሳ.ኮ

4.ኢ.ሳ.ቴ.ኮ 4. ሥ.ት.ዝ.ጥ.ም.ተ

5/ ከአምስት ያላነሱ የታወቁ ስሞችን አህፅሮተ ቃል ዓራና ሙሉ /ዝርዝር አጠራራቸውን ከነናቸው በማስፈር አሳዩ።

ምሳሌ፡- አህፅሮተ ቃል ሙሉ ቃል

ከ.ነ.ማ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር

አስረጅ 10

በ ‹‹ሀ›› ምድብ የተዘረዘሩትን በ ‹‹ለ›› ምድብ ከተዘረዘሩት ጋር በማጣመር ድርብ ቃል መስርቱና አንዳንድ ዓረፍተነገር ስሩባቸው።

ሀ ለ

----------1. ምግብ ሀ. ደራሽ

----------2. አየር ለ. ጣቢያ

----------3. ወደ ሐ. ድስት

----------4. ፈጥኖ መ. ቤት

----------5. ብረት ሠ. ወለድ

----------6. ፖሊስ ረ. ገብ

አስረጅ 11

ከዚህ በታች አስር ዓ.ነገሮች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ዓ.ነገር ተስማሚ የሆነውን ቃል ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በመምረጥ አሚልታችሁ ዓራና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ።

4. ፋጡማ አውሮፕላን---------ናት።

ሀ. በራሪ ለ. አብራሪ ሐ. መብረር መ. በረሮ

5. ልጆች መዝሙር----------ይወዳሉ።

ሀ. ዘመሩ ለ አዝምሮ ሐ. መዘመር መ. ዝማሬ

6. የኢትየጵያ ህዝቦች የኑሮ ደረጃቸውን የሚያሻሽሉት ----------ብቻ ነው።

ሀ. ሰርቶ ለ. መስራት ሐ. ስራ መ. ሲሰሩ

7. የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሊያጠናክሩ ከሚችሉት የገቢ ምንጮች አንዱ የ---------- ውጤት ነው።

ሀ. እርሻ ለ. ማረስ ሐ. አራሽ መ. አስተራረስ

8. የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ዛሬም ሆነ ነገ ----------ይኖራል።

ሀ. ማስከበር ለ. ተከብሮ ሐ. አስከብሮ መ. አስከባሪ

9. አስማማው አንደኛነቱን እንደ ---------- ሰባተኛ ክፍል ደረሰ።

ሀ. መጠበቅ ለ. አስጠበቀ ሐ. አጠበቀ መ. ጠበቀ

10.በሀገራችን የኤድስ በሽታ---------- ራሳችንን ከበሽተው መጠበቅ ይኖርብናል።

ሀ. እየተስፋፋ ለ. እየሰፋ ሐ. ስለሰፋ መ. ስለተስፋፋ

11.በክፍላችን ውስጥ ---------- ልጆች ፀባያቸውን እንዲያሻሽሉ ምክር ተሰጣቸው።

ሀ. ውሸተኛ ለ. ውሸታም ሐ. እየዋሸ መ. ዋሸ

12.የጉልበት ስራ መስራት ለአካል---------- ይሰጣል።

ሀ. መጠንከር ለ. ጠንካራ ሐ. ጥንካሬ መ. አጠነካከር

13. ነጭ ሽንኩርት ለብዙ አይነት---------- የሚሰጠው ፈውስ ተረጋግጧል።

ሀ. መታመም ለ. ታማሚ ሐ. አስታማሚ መ. ህመም

አስረጅ 12

ከመዝገበ ቃላት ወይም ሰው ጠይቃችሁ ወይም የፈለጋችሁትን አስር የአማርኛ ቃላት መርጣችሁ በሁለት ዓ.ነገር ውስጥ ሲገቡ የተለያዩ ፍቺዎችን እንዲሰጡ አድርጋችሁ ዓ.ነገር ስሩባቸው።

አስረጅ 13

የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ ወይም ሰው ጠይቃችሁ ፅፋችሁ አምጡ።

ቆቅ፣ ሐር፣ በለስ፣ ሚዳቋ፣ ምስጥ፣ ዝንጅብል፣ መረቅ፣ ሜንጦ

አስረጅ 14

ከዚህ በታች በምንባቡ መሰረት የሚመለሱ የቃል/የሀረግ ፍቺ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የቃላቱ /ሀረጋቱ በመጀመሪያ/ በምንባቡ መሰረት/ ተመሳሳይ/ ፍቺ ፈልጉላቸው። ቀጥሎ ተቃራኒ ፍቺ ፈልጉላቸው።

ምሳሌ፡- <u>አንድ የሚያደርጋቸው</u>፤ 1. የማያመሳስላቸው/ተመሳሳይ ፍቺ/

2. የሚያለያያቸው/ተቃራኒ ፍቺ/

ሀ. ያለልዩነት ረ. ትምክህት

ለ. መርህ ሰ. ቦታ

ሐ. አካሄድ ሸ. ወንድማማችነት

መ. ሊጣመመ ቀ. የሚገኝ

ሠ. ለፀዳ በ. ሚስጥራዊ

አባሪ ‹‹ለ››

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ለአማራ ክልል ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አዘጋጆች የቀረበ ቃለመጠይቅ

መግቢያ፡- የዚህ ቃለመጠይቅ ዋና ዓላማ በ1997ዓ.ም የታተመውን የአማራ ክልል የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አዘገጃጀትንና አቀራረብን መገምገም የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው። ለዚህ ጥናት መሳካት ደግሞ በመፅሀፉ ዝግጅት ከተካፈሉ ባለሙያዎች የሚገኙ መረጃዎች ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርጉ ይታመናል። ስለዚህ ቀጥዬ ለማቀርብለዎ ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡኝ በትህትና አጠይቃለሁ። እኔም በበኩሌ እርስዎ ከሚሰጡኝ ምላሽ የማገኘውን መረጃ ለታቀደው ጥናት ብቻ እንደማውል አረጋግጥሎታለሁ።

የማቀርብልዎትን ጥያቄዎች ለመመለስ ፍቃደኛ ሆነው ይህንን ጊዜ ስለሰጡኝ በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ።

መሪ ጥያቄዎች

1. በቅድሚያ ስምዎን፣ የትምህርት ደረጃዎትን፣ የሰለጠኑበትን የትምህርት መስክ፣ የአገልግሎት ዘመንዎን፣ የትና በምን አይነት የስራ ሃላፊነት ላይ እንዳገለገሉ ቢገልፁልኝ?
2. በ1997ዓ.ም የታተመውን የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ለማዘጋጀት እርስዎ እንዴት እንደተመረጡ ቢገልፁልኝ?
3. የመማሪያ መፅሀፉ ዝግጅት ዋና ዓላማ ምን ነበር?

4. ከአሁን በፊት በመማሪያ መፅሀፍ ዝግጅትም ሆነ በሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ተካፍለው ከሆነ መቼ፣ በየትኛው ደረጃና በዝግጅቱ የነበሮትን ሀላፊነት ቢነግሩኝ?
5. የአማራ ክልል የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ስታዘጋጁ መሰረት ያደረጋችኋቸውን ሰነዶች ካሉ ቢገልፁልኝ?
6. በመፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች የተመረጡበት መስፈርት ወይም መመሪያ ካለ ቢገልፁልኝ?
7. በመፅሀፍቱ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች የወጡት በመፅሀፎቹ ውስጥ ከቀረቡ ምንባቦች ብቻ ነው ወይስ ከምንባቦቹ ውጭም የቀረቡ ይዘቶች አሉ?
8. የቃላት ትምህርቱን ለማደራጀትና በመልመጃ መልክ ለመቅረፅ የተጠቀማችሁበት መስፈርት ምን ነበር?
9. የቃላት ትምህርቶቹ አቀራረብ የቃላቱን አውዳዊ ፍቺ የተከተለ ነወይ? የቃላቱንስ የፍቺ ዝምድና ከግምት አስገብታችኋል ወይ?
10. በመፅሀፉ ውስጥ ቃላት በአብዛኛው ተጣምረው የቀረቡት ከየትኛው የቋንቋ ክሂል ወይም የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ጋር ነው? ለምን?
11. የቃላዊ ሀረጎች (ፈሊጦች፣ ጥምር ቃላት እና የተለመዱ አገላለፆች) የቀረቡበት ሁኔታ ተማሪዎች እነዚህን ቃላት አፍልቀው እንዲጠቀሙባቸው የሚያበረታታ ነወይ?
12. በመማሪያ መፅሀፉ መልመጃዎች ተቀርፀውላቸው የቀረቡ ቃላት የተውጣጡት በመፅሀፉ ከተካተቱት ምንባቦች ውስጥ ነው ወይስ ከምንባቦች ውጪም የገቡ ቃላት አሉ?
13. ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት?

ጊዜዎን ሰውተው ለሰጡኝ ቃለምልልስ በድጋሜ ከልብ አመሰግናለሁ!!!

ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የኔ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በትክክል የተጠቀምኩ እና የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ምንውየለት ደነቀው

ፊርማ ----------

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሐ ግብር

አዲስ አበባ፣ ሰኔ 2005 ዓ.ም